በፍቅር፤ በሰላም፤ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የማህበራዊ ጉዳይ መጽሔት
በአማርኛ


$2.75

# ላንዳፍታ

<u>የብሔራዊ ዕርቅ ወቅታዊነት</u>

“ደርግ እስከሚወድቅ ድረስ ጠብቆ ካስተላለፈው ብሔራዊ እርቅ ጥሪ ትምህርት በመውሰድ አገርንና ህዝብን ማዳን ይቻላል።”

በሻቢያ ወረራ ምክንያት ኢትዮጵያ የገባችበትን ችግር በተመለከተ ከምሁራን፤ ከድርጅት ሃላፊዎችና ከተለያዩ ግለሰቦች የቀረቡ ግንዛቤዎች — ገፅ 28




መስከረም
፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
፯ኛ ዓመት
ቁጥር ፩

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Magazine in Amharic
*(Amharic is the Official Language of Ethiopia)*
SEPTEMBER 1998
Vol. 7 No.1




# Majestic Flowers & Gift Inc.

# ማጄስቲክ አበባና ስጦታ

ትዕግሥትና መስከረም



እንቁጣጣሽ በያመቱ ያምጣሽ!!



**አበባና እንግጫ ይዘን**
**እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ**
**በሰላም አሸጋገራችሁ እንበል!!**
**አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የደስታ፣ የጤናና**
**የብልፅግና እንዲሆንልዎ እንመኛለን!!**

ለጋብቻ፣ ለ“ሻወር”፣ ለልደት፣ ለእንግዳ መቀበያ፣
ለመታሰቢያ በዓላት፣ ለሚወዱት ፍቅረኛ፣
የሚሰጡ ቆንጆ ቆንጆ አበባዎች እናቀርባለን።
የስጦታ ዕቃዎችም ይኖሩናል።
በቅርቡ አዲስ የከፈትነውን የአበባና የስጦታ
መደብራችንን ይጎብኙ!!

አድራሻችን







Majestic Flowersc& Gift Inc.
2000 Cheshire Bridge rd.
Unite B
Atlanta, GA 30324

(404) 321-5111

# African Travel Consortium

*Offers upto 70% Discount*

## R/T tickets to Addis Ababa From ...

| | | | |
|---|---|---|---|
| Los Angeles | 1148 | Dallas/Houston | 1188 |
| San Diego | 1148 | Portland | 1238 |
| San Francisco | 1148 | Chicago | 1158 |
| Las Vegas | 1238 | New York | 1078 |
| Phoenix | 1148 | Florida | 1118 |
| Seatle | 1148 | Washington | 1098 |

**Restrictions apply - Fares are subject to change without notice.**
**Fares also available to/from other cities.**
**Please, call for Europe, Middle east and africa Fares.**

*Next day delivery service*
*available nationwide*

Ethiopia is our speciality. We offer the best rates in North America. That is why we are the largest travel agency serving Ethiopian community.

## የአፍሪካ ጉዞ ወኪል

## (206) 363-6136

## Toll Free (800)865-5260

We believe in being the best.

# ማ ው ጫ CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አዲስ ዓመት ቡራኬ

6 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

9 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ገብርዬ)

12 "ይድረስ ከዋትሳፖች ለጦራ ጦራ"

13 ደብዳቤዎቻችሁ

17 እንዲህ ሆነ (ከዜና ማህደር)

24 ቅዱስ ፓትርያርኩ በአትላንታ

26 "ብሔራዊ ዕርቅ" (ዮናታን ቡሬ)

28 ሻቢያ በኢትዮጵያ ስላደረገችው ወረራ አስተያየቶች

38 የኢ.ሰ.መ.ጉ. መግለጫ

42 የግጥም ጉባኤ

47 ትምህርት በምሳሌ




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ



ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ካቴድራል


ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1998

ላንዳፍታ
ልዩ እትም
መስከረም ፲፱፻፺፩
፮ኛ ዓመት ቁጥር ፩
LANDAFTA
SEPTEMBER 1998



አዘጋጅና አሳታሚ
መኮንን ገሠሠ
Publisher/Editor
*Mekonnen Gessesse*
Assistant Editor:
*Genet Wolde*
Contributors:
*Workayehu (pen name)*
*Gebrie (Pen Name)*
*Saefu Bishaw*
*Wuhib Tiruneh*
*Kesis Ephrem*
*Rev. Mekbib Atnaw*
Editorial Advisors
*Lisanu Simret*
*Dr. Getachew Metaferia*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Express Food Mart
H & B Shop
Merkato Market
Sweet Auburn Grocery
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery
Denver, CO
Emebet Works
Houston
Queen of Sheba Rest.
Maru Grocery
L.A., CA
Merkato
Coffee Damera
London
St.Gabriel Ethiopian Delicatseen
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Axum Market
San Jose, CA
St. Claire News Stand
Santa Clara, CA
Nathan Graphics
Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Lideta Market (Arlington)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu


# ከአዘጋጁ

## እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን በሰላምና በጤና አሸጋገርዎ! መጪው ዘመን የሰላም የጤናና የብልጽግና እንዲሆንልዎ ምኞታችንን እንገልፃለን!!

"አገራችን በሕዝብ ምርጫና ፍላጎት ሳይሆን ሥልጣን በዘር ውርስ ወይም በመሣሪያ ኃይል ሥልጣን የሚያዝበት በመሆኑ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ክፍሎች ልዩነታቸውን በውይይትና ክርክር የመፍታት፣ የመቻቻልና የመደማመጥ ባህል የለም።ሥልጣን ያዙኩ የሚለው መንግሥት ሕዝብን በኃይል ለመጫን ስለሚፈልግ በዚሁ ምክንያት ሞት፣ ስደትና መታሰር ወዘተ፣ አብረውን የቆዩ የኋላቀርነትምልክቶቻችን ናቸው። የሕዝብን የበላይነት የመቀበል፣ በሕዝብ ድምፅ የመገዛትና የመመራት ባህላችን ምንም ለውጥ አላሰየም። የአመለካከት ልዩነት ያላቸው ኃይሎች ችግሮቻቸውን በውይይትና በክርክር ከመፍታት ይልቅ ከአመለካከት ድህነት የተነሳ እርስ በርስ መጠፋፋት በአገራችን ነባር የፖለቲካ ባህል ሆኖ ቆይቷል። ደርግ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር በሰላምና በውይይት ችግሩን መፍታት ሲችል ወደ ጦርነት መግባቱና በርካታ ዜጎች በየአቅጣጫቸው መርገፋቸው ሲታወሰን ልዩነትን አቻችሎ ለመነጋገርና ለመሥራት ያለመቻል ባህላችን አገራችንን ምን ያህል እንደጐዳትና የኋሊት እንዳስኬዳት ለመገመት ብዙ ምርምር አይጠይቅም። የትላንቶቹም ሆነ የዛሬው መንግሥት መሠረታዊ ችግር የሌሎችን ሀሳብ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን፣ ለውይይትና ለሀሳብ ፍጭት አለመዘጋጀት፣ የእኔ መንገድ ብቻ ትክክል ነው ባይ መሆን፣ የሕዝብን ዳኝነት ለመቀበል አለመፈለግ፣ መቻቻልን አለማወቅ፣ ቅን ልቦና መጥፋትና በሀይል መተማመን፣ ወዘተ፣ ናቸው። የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ዐቢይ ችግር ልዩነቶችን በማቻቻል፣ አብሮና ተባብሮ ለመሥራት አለመቻል መሆኑ በተደጋጋሚ የታየ ድክመት ነው። በሚያስማሙን ሳይሆን በልዩነታችን፣ በሚያቀራርቡን ሳይሆን በሚያራርቁን፣ በሚያፋቅሩን ሳይሆን በሚያጣሉን ላይ ማተኮር ትልቁ የእኛዎቹ የፖለቲካ ሰዎች አስተሳሰብ ሆኖ ቆይቷል። ራስን ፍጹምና ትክክለኛ ማድረግና ሌላውን እንደስህተተኛ መቁጠር፣ የተለያዩ አስተሳሰቦችን ለማስተናገድ ፈቃደኛ አለመሆን እስከዛሬ ያለቀቀን የፖለቲካ ባህላችን ጥቁር ነጥብ ነው። በዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ባህል ቢቀጠል የሚደርሰውን ጥፋት ከወዲሁ መገንዘብ አያዳግትም። ኢህአዴግም በመታየት ላይ ያለውን ጤናማ የሆነና ለወደፊቷ ኢትዮጵያ መኖር ዋስትና ሰጪ የሆነውን ብሔራዊ ዕርቅና ስምምነት ገቢራዊ ለማድረግ ጥርጊያ ሊሆኑ የሚችሉ እርምጃዎችን አለምንም ፍርሃትና ይሉኝታ በአፋጣኝና በድፍረት መውሰድ ይኖርበታል የምንለውም አገሪቷን ከዚህ ከተደቀነባት አደጋ ለማዳን ነው። የፖለቲካ እስረኞችንና የነፃው ፕሬስ አዘጋጆችን አለምንም ቅድመ ሁኔታ መፍታት፣ ተቃዋሚ ሀይሎች ወደ ሀገር ቤት ገብተው እንዲንቀሳቀሱ፣ በሀገር ቤት ያሉትም የተዘጉባቸው ቢሮዎቻቸው እንዲከፈቱ ዋስትና መስጠት፣ የብሔራዊ ዕርቅ ጉባኤን ቅድመ ሁኔታ ማመቻቸትን የመሳሰሉ ቅን ተግባራትን መፈፀም በአሁኑ ጊዜ ከኢህአዴግ ይጠበቃል።"

ይህንኑ አሳሳቢ ጉዳይ በተመለከተ የዚህ እትም ትኩረት በአብዛኛው በአሁኑ ወቅት አገሪቷ ያለችበትን ሁኔታ በተመለከተ የተለያዩ ምሁራንና ድርጅት ሃላፊዎች የሰጡትን አስተያየቶች ይዘን ቀርበናል።


የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- landafta@aol.com
HOME PAGE:
http://www.ethiopic.com/landafta.htm



*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

**ABA MERKORIOS**
**PATRIARCH OF ETHIOPIA**



*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አሜን፤*

ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፥ ካህናትና ምመናን፥ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዙሪያ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤ ችርነቱ የማያልቅበት ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ በረድኤቱም መግቦ እንኳንም ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ በሰላም አሸጋገራችሁ፤

"ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትአወቅ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ በሐልዮ ወበአእምሮ ወከመ ዝ ይትአመር ኃይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም፤" ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታይ የማይመረመር እግዚአብሔር በስነ ፍጥረት በመመርመር ይታወቃል፤ እንዲሁም ከሐሊነቱ የዘለዓለም ጌትነቱ ይታወቃል፤ ይላል ሮሜ ም/1/ቁ/ 20 እግዚአብሔር አምላክ ራሱ ለሁሉ ጥንት መሠረት መገኛ ሁሉን ፈጣሪ ከመሆኑ በቀር ለእርሱ ጥንት መሠረት መገኛ ወይም ፈጣሪ ስለሌለው የሁሉ ጥንት መሠረት እርሱ ነው:: በዚህም የፍጥረታት ፈጣሪ ተብሎ ይጠራል፤ ለሥራውም ሰማይንና ምድርን በውስጣቸውም የሚገኙትን ሁሉ ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ በመፍጠሩ በቂ ምስክር ሆነው፤ ዘፍ ም/ 1 ቁ1-27. እግዚአብሔር አምላክ ከእርሱ በፊት ቀድሞ የተገኘ ሌላ ስለሌለና ከሁሉ በፊት የነበረ ቀዳማዊ እርሱ ብቻ ስለሆነ ከፍጡራን ወገን 1ኛ/ መገኛውን፥ 2ኛ/ የተገኘበትን ዘመን 3ኛ/ የዕድሜውን ልክ መጠን ያወቀ የሚያውቅ የለም፤ እርሱ ብቻውን ዓለም ምድር ሰማይ ሳይፈጠሩ የነበረ ነው፤ ቀዳማዊነቱ አባት ከልጁ፥ ታላቅ ከታናሹ፥ አዳም ከልጆቹ፥ ሰማይና ምድር ከሌላው ፍጥረት እንዳገኙት ቅድሚያ በሰዓትና በዕለት፥ በወራትና በዘመን፥ በዓመት በጥቂትና በብዙ ጊዜያት እነርሱንም በመሳሰሉ መስፈሪያዎችና መለኪያዎች የተለካና የተመጠነ የተሰፈረና የተቆጠረ አይደለም፤ ከእርሱ በቀር ይህ ዛሬ ያለንበት ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረና የነበረውንም የሚያውቅ የለም እንጅ የነበረ ሰው ኖሮ በዚህ ጊዜ ይህ ተደረገ፤ በዚህ ጊዜ ይህ ተሠራ ብሎ ታሪክ የሚነግር ቢገኝ ኖሮ ፍጥረት ያለፈጣሪው ስለማይገኝ ከሁሉ በፊት ራሱ መገኘትና ሌላውንም ማስገኘት የግሉ ስለሆነ ታሪኩ ነበር በማለት ብቻ ይወሰናል:: ስሙም በቅዱሳት መጻሕፍት በሉየ መዋዕል ተብሎ ይጠራል:: በአስተያየትም የፀጉሩ ሽበት የነጭ ሐር መልክ የያዘ መስሎ በታላቅ ሽማግሌ መልክ ለቅዱሳኑ ስለሚታይ፥ ያዩት ሁሉ "ሥዕርተ ርእሱ ፀዓዳ ከመ ፀምር" የራስ ጠጉሩ እንደ ብዝት ግምጃ ማለት እንደ ነጭ ሐር ነው ብለው መስክረዋል፤ዳን ም.7ቁ/9 ይህ ታላቅ ስምና ልዩ መልክ ለእግዚአብሔር ሲሰጥ ዘመኑ የማይቆጠር መሆኑን ባጭሩ ለመረዳት ያህል ነው እንጅ እንደ ሽማግሌወቻችን ወግ ዘመን የሚያልቅበት እርጅና የሚመጣበት ሆኖ አይደለም:: እግዚአብሔርንም በዘመን ያረጀ ሽማግሌ ብሎ ለመጥራት ቅድምናውንም በሺምግልና መልክ በዓይነ ሕሊና ለመመልከት የሚፈልግ ሰው ሁሉ እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ ከፍጡራን ልማድ የሚወረሰውን የሽማግሌዎችን ወግ እንደማይጠብቅ ይወቅ:: ልዑል እግዚአብሔር በጥንትነቱና በቀዳማዊነቱ የማይለይና የማይነሳ፥ የማይከፈል፥ የማይቀነስ፥ ዕውቀት ጥበብም የባሕርዩ ነው:: የፍጡር ሕሊና መርምሮ በማይደርሰው በዚህ ጥልቅ ረቂቅ ጥበቡ የዘመናት ባለቤት እግዚአብሔር አምላካችን ከሁሉ አስቀድሞ ለሁሉ መሥፈሪያ መለኪያ ሚዛን የሆነውን ሰዓት ዕለት ወር ዓመት የሚገኙበትን ጊዜ የተባለውን ታላቅ መሳሪያ ለሥራው መሰናጃ ማዘጋጃና ማደራጃ አድርጎ ፈጥሮ በጊዜ መደብነት ሌላውን ፍጥረት እያከታተለ ፈጠረ::.. ..

## የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ
## ፓትርያርክ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
## የአዲስ ዓመት ቡራኬ

*መዝ/118 ቁ126፥ ለጥንትነቱ ጥንት የሌለው በመሆኑ የጥንትነቱ ታሪክ ነበረ በማለት ብቻ እንዲወሰን፥ ለፍጻሜነቱም ፍጻሜ የሌለው ስለሆነ የፍጻሜነቱ ታሪክ ዘለዓለም ይኖራል፤ በማለት ብቻ ይወሰናል እንጅ ሕሊና መርምሮ አይደርስበትም። መዝ 92/ቁ/2. ስለዚህ ስሙ አልፋ፥ ወአ፥ ቀዳማዊ፤ ደኃራዊ፤ ፊተኛ፥ ኋለኛ፥ መጀመርያ፥ መጨረሻ፥ ተብሉ ይጠራል። ራዕ ም/1 ቁ 17. /2 ቁ 8. 22/ ቁ/ 13.*

*ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፥ ካህናትና ምእመናን፥ እግዚአብሔር አምላክ በከሃሊቱ ካዘጋጀልን ነገሮች ሁሉ ታላቁ ጊዜ ነው ። የሰው ልጅ ቀናትን አውራኅንና ዓመታትን፥ ቆጥሮና ለክቶ፥ መጠቀም ከጀመረበት እንስቶ እያንዳንዱ ደቂቃ የታሪክና የሥራ ጊዜ ነው። ሰው በጊዜው ባይሠራበት ጊዜው በሰው ሕይወት ላይ ሥራ ሠርቶ ታሪክ መዝግቦ ያልፋል። ስለዚህም ያለፈውን ጊዜ መመለስ የሚመጣውንም ወደ ዛሬ መሳብና በስልጣን ስር ማድረግ የሚችል የለም። ዕዝራ ሱቱኤል ም/ 2ቁ3-6 ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከደሙ ጋራ ተዋሕዶ የኖረው ሃይማኖቱ እያስገደደው ከግል ሀብቱና ንብረቱ ይበልጥ ለሃገሩ ለክብሩ ለሃይማኖቱ ለውጥ አድርጎ ሰውነቱን በመሠዋት ያገለግል ነበር። ዛሬም የአንዲት ኢትዮጵያ ልጅ የሆነ ሁሉ እንደቀድሞዎቹ አባቶቻችን ዳር ደንበሯ ተከብሮ ለኖረችው ሃገራችን፥ ለጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያናችን፥ ለተዋሕዶ ሃይማኖታችን፥ ለታሪካዊው ቅርሳችን መልካም ሥራ መሥራት የምንችለው ዛሬ ባለንበት ጊዜ ነው። "ጊዜ ሳለን ለሁሉ ለሰው ሁሉ መልካም ሥራ እንሥራ ይላል ገላ ም/6 ቁ 14." መስከረም 1 ቀን የሚውለውን የዘመን መለወጫ በዓል የምታከብሩ በዓለም ዙሪያ የምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤ ኢትዮጵያ ይህንን በዓል ጥንት መሠረትነቱን አውቃ የምታከብረው መስከረም 1 ቀን ነው። የተጀመረበትም ከጥፋት ውኃ በኋላ በኖኅ ዕድሜ በስድስት መቶ አንድ ዓመተ ዓለም ጀምሮ ሲከበር ኖሮ እነሆ ደርሰንበታል፤ ኖኅም ሲያከብረው ጥንቱን ዓለም የተፈጠረበት ወር እንደ መሆኑና ለመጀመሪያ ጊዜ ከጥፋት ውኃ ወዲህ ክረምትና በጋ መፈራረቅ የጀመሩበት፥ ምድር የፍሬ ጽንስ የአበባ መልክ ያሳየችበት ስለሆነ ነው። ስሙም ርእሰ ዓውደ ዓመት፥ የዘመን መለወጫ፥ ዕንቍጣጣሽ፥ ቅዱስ ዮሐንስ፥ እየተባለ ይጠራል። ስሳቆጣጠሩ ግን በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር መስከረም 1 ቀን የሆነው በዕብራውያን ቁጥር ጥቅምትን ይነካል። "እግዚአብሔር አምላክም በሰባተኛው ወር ከወሩም በመጀመሪያ ቀን ለእግዚአብሔር የተቀደሰች በዓል አድርጉ። በዓሉም ተዝካረ በዓል (መጥቅዕ) ይባላል ሲል ሙሴን ያዘዘው ስለዚሁ ነው።" ይህም በዓል ለዓመት ጥንት እንደመሆኑ መጠን የአውራኅም ጥንታቸው ነውና። በዓመት በመጀመሪያው ቀን ይከበራል። ምክንያቱም ለወር ለዓመት ጥንት መጀመሪያ ስለሆነ ነው። በዓለ መጥቅዕ ተዝካረ መጥቅዕ መባሉም፥ መጥቅዕ ደወል በተደወለ ጊዜ ሁሉን እንዲሰበስብ ይህም ልዑል እግዚአብሔር የሐልዮ የነቢብ ቃሉን ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ዕለትን፥ ሰዓትን ወርን ዓመትን ሰብስቦ የሚያስገኝ በመሆኑ ነው። ሰሳቆጣጠሩ ፊትና ኋላ መሆኑ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት አይሁድ ሚያዝያ 14 ቀን ያከበሩት የፋሲካ በዓል በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር መጋቢት 27 ቀን እንደሆነ መመልከት ብቻ ሊያስረዳን ይችላል። ዘሌ/ ም 23/23-24. ይኸውም በዓለ መጥቅዕ ለፍጡራን ያይደለ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ በዓል መሆኑን አውቀው እንዲጠብቁት በማዘዙ ጥንተ ፍጥረት ጥንተ ወርኅ ጥንተ ዓመት ያው በዕብራውያን አቆጣጠር ጥቅምት በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ግን መስከረም ተብሉ የሚጠራው መሆኑ ግልጥ ነው። ኢትዮጵያ ከጥንት ከአባቶቿ የተቀበለችውና ስታከብረው የምትኖረው መስከረም 1 ቀን የሚውለው ርእሰ ዓውደ ዓመቷ ጥንታዊትነቷን ሲመሰክር የሚኖር የጥንትነቷ ፍሬ ስለሆነ መስከረም 1 ቀን በዓል ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ለክብራችን ለታሪካችን ጥንት መሠረት ነውና አውቀን እንጠቀምበት።*

*እግዚአብሔር አምላካችን በዓሉን የሰላም የጤና በዓል ያድርግልን፤*
*ለዓም ሁሉ ሰላምን ፍቅር አንድነትን ያድልልን አሜን።*

*አባ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ*
*ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## ከወርቃየሁ (ሸገር)

ወንድሜ ገብርዬ፤ ከሁሉ በፊት የናፍቆት ወገናዊ ሰላምታዬ ይድረስህ። የእኔንና የእኛን ጤንነት ሁሌ የምትሰማው ስለሆነ ብዙም አልለፈልፍብህም። ያልታደልን ሆንና ይኸው ለአዲስ ጦርነት ተጋብዘን እንደገና "ስንቄን ጨርቄን" ማለት ከያዝን ሰንበትበት ብለናል። በየጊዜው የሚነሱ አለመግባባቶችን የምንፈታው ሁሌ በጦርነት እየሆነ መሪዎቻችን ባልተግባቡና እልህ በተያያዙ ቁጥር፤ ችግሩን መፍቻ ጦር መማዘዝ ሆኗል። በዚያ የእልህ ጨዋታ ውስጥ እኛ ደግሞ እንገባና ሰለባ እንሆናለን። በቅርቡ በጦቢያ ጋዜጣ ላይ ነቢዩ ሰይፉ የተባሉ ብዕርተኛ ያቀረቡትን ጽሁፍ በጥሞና ብትመለከትልኝ ደስ ይለኛል። ያለንበትን ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ጽሁፍ ነው። ስለዚህም እንዳለ ልኬልሃለሁና እስቲ አንብበው፤ የልቤን ነው ነቢዩ የተናገሩት።

"በእስከዛሬው የመንግሥትነት ታሪካችን በሕዝብ ምርጫና ፍላጐት ሳይሆን ሥልጣን በዘር ውርስ ወይም በመሣሪያ ኃይል የሚያዝበት አገር በመሆኑ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ክፍሎች ልዩነታቸውን በውይይትና ክርክር የመፍታት፣ የመቻቻልና የመደማመጥ ባህል አልነበረም። ሁሉም በየአቅጣጫው የራሱን አመለካከት በሕዝብ ላይ በኃይል ለመጫን ስለሚፈልግ በዚሁ ምክንያት ሞት፣ ስደት፣ መታሰር የንብረትና የታሪክ እሴቶች መጥፋት፣ ወዘተ፣ አብረውን የቆዩ የኋላቀርነት ቅርሶች ናቸው። ዛሬም ቅርፅና ባህሪያቸውን ይቀይሩ እንጂ የሕዝብን የበላይነት የመቀበል፣ በሕዝብ ድምፅ የመገዛትና የመመራት ባህላችን እምብዛም ዕድገትና ለውጥ አላሳየም።

"የፖለቲካ ድርጅት በተደራጀ መልኩ ብቅ ካለበት ከ1966 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጀምሮ ያለውን ሁኔታ እንኳን ብናጤን የአመለካከት ልዩነት ያላቸው ኃይሎች ችግሮቻቸውን በውይይትና በክርክር ከመፍታት ይልቅ እርስ በርስ መጠፋፋት በአገራችን ነባር የፖለቲካ ባህል ሆኖ ቆይቷል። ከዚህ የአመለካከት ድህነት የተነሳ የአንድ ርዕዮተ ዓለም አራማጅ የነበሩት ኢህአፓና መኢሶን ሳይቀሩ መደማመጥ፣ ልዩነታቸውን በውይይት መፍታትና መቻቻል አቅቷቸው እርስ በራሳቸው መጫረሳቸው፣ የተረፉት ኢህአፓዎች በሂደት በውስጣቸው በተፈጠረ አንጃ ለሁለትና ከሁለት በላይ መሰንጠቃቸውና ከወያኔ ጋር በአሲምባና ዞብል ተራራዎች በመዋጋት መመናመናቸው፣ የኢማሌዲህ ልጆች የወንድማቸውን የመኢሶንን መሞቻ መንገድ አመቻችተው ከገደሉት በኋላ በተራቸው እርስ በርሳቸው ተበላልተው ማለቃቸው፣ ደርግ ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር በሰላምና በውይይት ችግሩን መፍታት ሲችል ወደ ጦርነት መግባቱና በርካታ ዜጐች በየአቅጣጫቸው መርገፋቸው ሲታወስ ልዩነትን አቻችሎ ለመነጋገርና ለመሥራት ያለመቻል ባህላችን አገራችንን ምን ያህል እንደጐዳትና የኋሊት እንዳስኬዳት ለመገመት ብዙ ምርምር አይጠይቅም።

"የትላንቶቹም ሆነ የዛሬው መንግሥት መሠረታዊ ችግር የሌሎችን ሀሳብ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን፣ ለውይይትና ለሀሳብ ፍጭት አለመዘጋጀት፣ የእኔ መንገድ ብቻ ትክክል ነው ባይ መሆን፣ ዲዝብን ዳኝነት ለመቀበል አለመፈለግ፣ መቻቻልን አለማወቅ፣ ቅን ልቦና መጥፋትና በሀይል መተማመን፣ ወዘተ፣ ናቸው።

"ውጤቱም የአገርን ዕድገት በመግታት በዓለም ሜብረተሰብ ፊት በሁሉም ዘርፍ አቅመቢስ ሕዝብና አገር ይዞ ዘወትር ልዩነታችንንና ደካማነታችንን ለሚሹ ጠላቶቻችንን ተመቻችተን እንድንቆይ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል።

"<u>የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ዐቢይ ችግር ልዩነቶችን በማቻቻል፣ አብሮና ተባብሮ ለመሥራት አለመቻል መሆኑ በተደጋጋሚ የታየ ድክመት ነው። በሚያስማሙን ሳይሆን በልዩነታችን፣ በሚያቀራርቡን ሳይሆን በሚያራርቁን፣ በሚያፋቅሩን ሳይሆን በሚያጣሉን ላይ ማተኮር ትልቁ የእኛዎቹ የፖለቲካ ሰዎች አስተሳሰብ ሆኖ ቆይቷል</u>። ራስን ፍጹምና ትክክለኛ ማድረግና ሌላውን እንደስህተተኛ መቁጠር፣ የተለያዩ አስተሳሰቦችን ለማስተናገድ ፈቃደኛ አለመሆን እስከዛሬ ያለቀቀን የፖለቲካ ባህላችን ጥቁር ነጥብ ነው። ይህ የአስተሳሰብ ድህነት እስከ መቼ ይዘልቃል? በአለፉት ሰባት ዓመታት በቀላሉ፣ በውይይትና በመደማመጥ ሊፈቱ በሚችሉ የፖለቲካ ልዩነቶች በፈጠረው ጣጣ ስንት ምሁራንና ዜጐች ለስደት በቁ? በዓላማ ፅናት የዚህን መንግሥት አሠራርና አካሄድ በግልፅ የተቃወሙና ለዓለም ህብረተሰብ ያጋለጡ ፖለቲከኞችና የሲቪክ ተቋማት አመራር አባላት ህገ ወጥ የሆነ ድራማ እየተዘጋጀላቸው ስንቶቹ የእስር ሰለባ ሆኑ? ስንቶቹስ ለሞት ተዳረጉ?

"በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በግልፅ እንደሚታየው የአንድ ፓርቲ መንግሥት የተፈጠረ በመሆኑ ሁሉንም (ፖለቲካውን፣ ኢኮኖሚውን፣ ፕሮፓጋንዳውን) በሞኖፖል ይዞ ከፍላጐቱ አንፃር

ሕግ ያወጣል፣ ያስፈፅማል፣ ይዳኛል። ሌሎች ተቃዋሚ ሀይሎች ግን ከሀገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ተገልለው ይገኛሉ።

"የፖለቲካ ልዩነትና የተቃውሞ ድምፅ የዲሞክራሲ አንዱና መሠረታዊ መግለጫ ሲሆን፣ ልዩነትም የዕድገት ምልክት ነው። ልዩነት ከሌለ ትግልም፣ ዕድገትም የለም። የተለያዩ አመለካከቶች ተገቢ መድረክ አግኝተው መስተናገድ፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያ መብቶች መሟላት የሰለጠኑ አገሮች የሚመሩበትና በሥራ ላይ ያዋሉት ትክክለኛና ሐቀኛ መርህ ነው።

" ስለ ዴሞክራሲ ብዙ እየተባለ ብሔራዊ አጀንዳ ያላቸው ተቃዋሚ ኃይሎች በሀገራችን የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳይሳተፉ በሩ ተዘግቶባቸዋል፡፡ እኛ ዜጎች ደግሞ እኛን ለማስተዳደር የሚፈልጉ ሁሉ አጀንዳቸውን አቅርበው እንዲወያዩና በሚያቀርቡት ፕሮግራም ላይ ተወያይተን ለዕድገታችንና ጥንካሬያችን የሚጠቅመውን የመምረጥ ዕድል ማግኘት እንፈልጋለን። በሰለጠኑት ሀገሮች እንደሚታየው የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል ተወዳዳሪዎች በነፃነት በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተዘዋውረው ዓላማቸውንና አጀንዳቸውን ለአባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው የሚያስተዋውቁበትን አሠራርና የምርጫ አፈፃፀም እንሻለን። በሕዝብ የበላይነትና በምርጫ ሳጥን በሚገኝ ውጤት ተገዥ የሚሆን መንግሥት በሀገራችን እንዲቆም እንፈልጋለን።

"ለሕዝብ ነፃ ውሳኔ ተገዥ የሚሆን መንግሥት ለማምጣት ደግሞ ሁኔታዎች መመቻቸት አለባቸው። የግራም ሆነ የቀኝ አመለካከት ያላቸው ፓርቲዎች ዓላማቸውን ለሕዝብ የሚያስተጋቡበት መድረክ መፈጠር ይኖርበታል። ይህ የሀገሪቱ ባለሥልጣናት ለሕግ ተገዥ ሆነው ዘላቂ ሰላም የሚያስገኝ ብቸኛ መንገድ ነው።

"አገራችን የምታራምደው ፖለቲካ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን ሕጉ የሚጠይቀውን ማሟላት አለብን። የጋራ ቤታችን ለሆነችው አገር ሀሳብ አለን የሚሉ ወገኖች፣ በተለይ ህብረ ብሔራዊ የሆነ የፖለቲካ ዓላማ ይዘው የሚታገሉት ወደ ዳር እየተገፉ የሕዝብ መቀራረብን ሳይሆን መለያየትን የሚሰብኩ፣ አገራዊ አጀንዳ ሳይሆን የመንደር (ጎጥ) መፈክር ያነገቡ የፖለቲካውን መድረክ በሚቆጣጠሩበት ሀገር ጤናማ የሆነ ሥርዓት ይገነባል ማለት አይቻልም።

"በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ የሚገኙ ተቃዋሚ ሀይሎች የሀገራችንን ፖለቲካ (አስተዳደር) በተመለከተ የየራሳቸው ራዕይ ያላቸው መሆኑን ለኢትዮጰያ ሕዝብና ለዓለም ሕብረተሰብ ሲያሰሙ ቆይተዋል። ተቃውሞና ቅሬታ የሚያሰሙባቸው ብሔራዊ ጉዳዮች ጠመቅ ተደርገው ሲታዩም በሚከተሉት ነጥቦች ሥር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው።

√ ሀገሪቱ የምትመራበት ሕገ መንግሥት የሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች ተሳትፎ ባካተተ መልኩ የተዘጋጀ ሳይሆን በአንድ ፓርቲ (ቡድን) ፍላጐት የተሠራ ነው።

√ የመንግሥት አደረጃጀትና የሥልጣን ክፍፍል የጐሣ ፖለቲካን መሠረት ማድረጉ ለወደፊቷ ኢትዮጰያ የማይበጅ ነው።

√ የኢኮኖሚ ፖሊሲው ግልፅነት የጐደለው፣ የምዕራቡና ምሥራቁ ዓለም (ካፒታሊዝምና ኮምኒዝም) የተደባለቀበት፣ አቅጣጫውን ያልለየ ነው።

√ ተቃዋሚ ሀይሎች በኢትዮጰያ ውስጥ ተንቀሳቅሰው ለመሥራት የማያስችል አደገኛ የሆነና አምባገነን አሠራር ሰፍኖአል።

√ የምርጫ ሥርዓትና ደንብ አስፈፃሚ ኃይሎች አካሄድ በአንድ ቡድን ፍላጐት የሚመራ በመሆኑ በኢትዮጰያ ፍትሐዊ የምርጫ ሥርዓት የለም።

√ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ አደረጃጀት ቁልፍ ቦታዎች በታማኞች የተያዙና የሚመሩ፣ የጥቂቶች የበላይነት የሚታይበት ነው።

√ በትምህርትና በጤና፣ በአጠቃላይ የልማት ሥርጭትና እንቅስቃሴ ፎዝብ ብዛትንና የገቢ ምንጭን ባጣጣመ መልኩ ሚዛናዊ የሆነ አሠራር የለም። ልማት ወደ አንድ አቅጣጫ ያጋደለ ስለሆነ ለተመጣጠነ ዕድገት ፣ ሰላምና መረጋጋት ፍትሃዊ የሆነ የሲቪል አስተዳደር መፈጠር አለበት፣ ወዘተ፣

የሚሉ አመለካከቶች ሲሆኑ ሕዝቡም የሚጋራቸው አስተሳሰቦች ናቸው።

"በአሳለፍናቸው ሰባት ዓመታት ኢህአዴግ በደርግ ሥርዓት ይታይ እንደነበረው ሁሉ ተቃዋሚ ሀይሎችን በሀይል ለመጨፍለቅ ጦረኛ፣ ነፍጠኛ፣ ጠባብ፣ ፀረ - ሰላም ወዘተ... ከማለት ጀምሮ ተቃዋሚ የሚባል የለም እስከማለትና፣ አልፎ አልፎ ተቀባይነት የሌለው ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ተቃዋሚ ሀይሎችን ሲያሸሽ ቆይቷል። ሲያስፕውም በድብቅ ተደራድሯል። (በጀርመን ከኦነግ ጋር የተደረገውን ድርድር ያጤኗል።)

"ሰኔ 30 ቀን 1990 ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለፓርላማ ባቀረቡት ሪፖርት መንግሥታቸው

ከተቃዋሚ ሀይሎች ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት ፍላጌት እንዳለው ፍንጭ አሳይተው ነበር። የአሁኑ መግለጫቸው ከቀድሞው የኢህአዴግ አቋም የሚለየው ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ አለመደርደሩ ነው።

"በፈታኝና አደገኛ ወቅት ሀገርን ለማዳን የታየው ቀና፣ ራዕይና አስተሳሰብ ገፍቶ የመውጣት ምልክት በመሆኑ ይህን በጐ አዝማሚያ ወግና ሥርዓት በአለው መልኩ ለመጠቀም የመንግሥትን የሀቀኛ ዜጐችንና የምሁራንን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ይጠይቃል።

"ኢህአዴግም በመታየት ላይ ያለውን ጤናማ የሆነና ለወደፊቷ ኢትዮጰያ መኖር ዋስትና ሰጪ የሆነውን ብሔራዊ ዕርቅና ስምምነት ገቢራዊ ለማድረግ ጥርጊያ ሊሆኑ የሚችሉ እርምጃዎችን አለምንም ፍርሃትና ይሉኝታ በአፋጣኝና በድፍረት መውሰድ ይኖርበታል።

ከእነዚህም ጥቂቶቹ፣

√ በሰበብ አስባቡ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞችንና የነፃው ፕሬስ አዘጋጆችን አለምንም ቅድመ ሁኔታ መፍታት፣

√ በውጪ የሚገኙ ተቃዋሚ ሀይሎች ወደ ሀገር ቤት ገብተው እንዲንቀሳቀሱ፣ በሀገር ቤት ያሉትም የተዘጉባቸው ቢሮዎቻቸው እንዲከፈቱ ዋስትና መስጠት፣

√ የብሔራዊ ዕርቅ ጉባኤን ቅድመ ሁኔታ የሚያመቻችና የዲፕሎማሲ ሥራ የሚያከናውን ከታዋቂ ምሁራን፣ ከሀገር ሽማግሌዎችና ከሃይማኖት አባቶች የተውጣጣ ኑየብሔራዊ ዕርቅና ስምምነትዉ አካል እንዲቋቋም መስማማት፣

√ የአገራችንን ችግር ኢህአዴግ ከራሱ ፍላጌት ሳይሆን ከኢትዮጰያ ሜዝብ ፍላጌት አንፃር የማየት፣

√ አገርን ለማዳንና ለመጪው ትውልድ በጐ ነገር ለማስተላለፍ በጠመንጃና በሀይል የሚቋቋም መንግሥት አስቀርተን ሥልጣን ከምርጫ ሳጥን የሚገኝበትን መንገድ ለመቀየስ በሀኃላፊነት ስሜት ግልፅ ሆኖ መቅረብ ናቸው። ኢህአዴግ ብሔራዊ ዕርቁን ከልብ መቀበላቸውን በተግባር ከሚያሳዩባቸው እርምጃዎች እነዚህ ናቸው።

"ተቃዋሚ ኃይሎችም ፍንጭ የታየበት የሰላምና የዕርቅ ስምምነት መልካም ጅምር ለፍሬ እንዲበቃ፣ በቅን ልቦና እና አርቆ አስተዋይነት ሊከተሏቸው (ሊያስከብሯቸው) የሚገቡ ነጥቦች አሉ። ለምሣሌ፣

√ ኢትዮጰያ ወዴት አቅጣጫ ማምራት እንዳለባት የሚያብራራ ግልፅ የሆነ ዓላማና ፕሮግራም ይዞ መቅረብ፣

√ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ዕውቀታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ልምዳቸውን ማዋሃድ ወይንም ግንባር መፍጠር፣

√ የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ጨዋታውን ሜግ በመከተል መቻቻል፣ መቀራረብና ደዝብ ጥያቄና ፍላጌትን ማዕከል ማድረግ፣

√ ሀገሪቱ የጋራ መሆኗን በማወቅ የሌላውንም ዲሞክራሲያዊ መብት የማክበር፣

√ የሕዝባችንን ባህል፣ ወግና ፍላጎት በማወቅ፣ በጨዋነትና በሕጋዊ አካሄድ ለመንቀሳቀስ ራስን በጥልቀት ማወቅና ማዘጋጀት፣

√ ለአስማሚውና አስታራቂው አካል ቅን ሆኖ መቅረብ፤ በጥቃቅንና አነስተኛ ችግሮች ከሰላሙ መድረክ አለማፈንገጥ፣

√ በዕርቁና ስምምነቱ ሂደት ፈተና ሊኖር እንደሚችል ማወቅና ልዩነትን በውይይት በክርክርና፣ በሕዝብ ዳኝነት እንደሚፈታ የማመን፣ ወዘተ፣ ሊተኮርባቸው የሚገቡ፣ ጤናማ የሆኑ አስተሳሰቦች ናቸው።

"በየትኛውም ወገን ለሥልጣን ካልጓጓን፣ ለግል ጥቅምና ዝና ካልተሽቀዳደምን በእውነት ለአገራችን ጉዳይ መላ ማግኘት፣ ችግሮቻችንን በጋራና በምክክር ማስወገድ ያቅተናል? እኛ ኢትዮጰያዊያን የእርቅና የስምምነት ወርቃማ የሆነ የቆየ ባህል የለንም? የውስጥ ችግራችንን እኛው በእኛው፣ በሀገር ልጆች ዳኝነት መፍታት አንችልም? ወይንስ የመሐል ዳኛ ፈረንጅ መሆን አለበት?

"ምዕራባውያን በልዩነታችን እየተጠቀሙ እርስ በርስ ከማናከስ በስተቀር አይጠቅሙንም። ለእኛ ከእኛ በላይ የሚቆረቆርና በችግሩ ተጌጂ የሆነ ስለሌለ ለብሔራዊ እርቅና ስምምነት ለሚቋቋመው አካል ልዩ ግምት ልንሰጠው ይገባል። ካርተር፣ ጆንሰን፣ አልብራይት ሆኑ ክሊንተን አሜሪካዊ ናቸው። ለኢትዮጰያ ያላቸው አጀንዳ አንድ ነው። በቅድሚያ የአሜሪካንን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ። አሜሪካን ትላንት ከሞቡቱ ሲሲኮ ዛሬ ደግሞ ከካቢላ የሚያወዳጃት ጥቅም ብቻ ነው። ከእኛ ጋርስ የተለየ ነገር ይኖራታል ብሎ ማሰብ ይቻላል?

"ለአገራችን ዕድገትና ልማት ብሎ አሳቢ የሆኑ ሀይሎች በተለይ ሥልጣን ያለው ኢህአዴግና ተቃዋሚ ሀይሎች በታሪክና ትውልድ ተወቃሽ ላለመሆን ለብሔራዊ እርቅና ስምምነት እያሳዩት ያለውን በጐ ጅምር ዳር ለማድረስ በሀላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።"

ወዳጄ ገብርዬ፤ ታዲያ ምን አሰብክ አንተ፤ ይህ ነቢዩ ያነሱትን ነገር በቁም ነገር መንግሥትም ሆነ ተቃዋሚ ድርጅቶች በቀና ልቦና ቢያዩት የት በደረስን ነበረ። ወይ ነዶ!!

ወዳጅህ ወርቃየሁ ከሸገር

# ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ

## ከገብርዬ

የኔ ውድ!

የዛሬው ደብዳቤዬ አጭር ነው። ሁኔታዎች ቀድመውን ሲተሙ፣ እኛም ጭራቸውን ለመያዝ ስንሮጥ ባላሰምነው ጥሻ ውስጥ እየገባን ነው። መንገዱን ለመለየት የመደነጋገር ሁኔታ ቢታይብንም የጥሻና የበረሃ አቧራማ መንገድ የሚሰራው በመራመድ እንደሆነ ተረድተን አንድ ታሪከኛ ያለውን እየደገምን ያለን እንመስላለን፦ «መንገደኛው መንገዱ ወደ የት ነው ብለህ አትጠይቅ፣ መንገድ የሚሰራው በመራመድ ነው።» አሁንም የሚታወሰኝ ይህ የጥሻ መንገድ ነው። መድረሻችንን ሊማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም እየተራመድን በጥሻው ውስጥ መንገድ ሠርተናል። እስቲ ትርጉሙ ለየት እንዳይል የእንግሊዝኛውን አባባል ልጥቀስልህ። "TRAVELLER DON'T ASK WHERE THE PATH IS, PATHS ARE MADE BY WALKING" ለማሳየት የፈለግሁትን ለማወቅ ይረዳሃል።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

አዲስ ክስተት በሀገራችን ታየ! ወያኔና ሻቢያ ያልተፋቀሩትን ያህል ተጣሉ፤ ጠቡ ለመከረኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተረፈ። እኛም ተቃዋሚዎችና ደጋፊዎች መልስ ለመስጠት ታከትን – በጥሻ ውስጥ እንደመራመድ ነው። ግማሾቻችን የተፈጠረውን ሁኔታ በራሳችን መነፅር በማየት በሁኔታዎች ላይ የታሰረ ውሱን ድጋፍ ለወያኔ ለመስጠት አሰብን፣ ወያኔ አድርጉት የማያውቀውን ጠየቅነው። የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣ የክልል ፖሊሲዎች ይወገዱ፣ እንዱን ጉሳ በሌላ ላይ የማነሳሳት የጥላቻ መርዝ ይቁም፣ ከተቃዋሚዎች ጋር የበጐ ፈቃደኝነት በር ይከፈት ... ወዘተ አልን። በአንዳንድ ስፍራዎች የወያኔ አምባሳደሮች እጅግ የሚገርም መልስ ሰጡ። በስደት ላይ ያለውና በተቃዋሚ ድርጅቶች ዙሪያ የተሰባሰበው ምራቁን ዋጥ አድርጉና ለስልሶ የአንድነት ተሐድሶን ለማሳደግ እንዲያውም ለትግራይና ለአፋር ሕዝቦች በገንዘብ ሳይቀር ድጋፉን ገለጠ።

የኔ ውድ!

የተፈጠረው ሁኔታ በሕዝቦች መካከል ወያኔ ና ሻቢያ ያመጡትን መቃቃር አስወግዶ የአንድነትን ተሐድሶ ለመመስረት በር ከፈተ፤ መለስ ዜናዊም የኢትዮጵውያንን የኖረ ወኔ እቀሰቅሳለሁ በሚል በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ትናንት የተናገረውን ለውጦ ነፃነትን ለማስከበር የኢትዮጵያ ሕዝብ ከባዕዳን ጋር የተፋለመባቸውን አርአያነት ጠቀሰ።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

ሻቢያና ወያኔ እንደዚሁ በቀላሉ ይጣላሉ ብለን ስላልገመትን፣ ይህ ድንገተኛ ሁኔታ ብዙ ክርክርንና መወዛገብን አስከተለ። የቲፒኤልኤፍም አመራር የተፈጠረውን ሁኔታ ለራሱ ለመጠቀም በተራቀቀ መንገድ ሠራ። በዋሽንግተን ዲሲ «የአንድ ኢትዮጵያ ሬዲዮ» በግብታዊነት የሕዝብን ስሜት ቀስቀሰ፣ ሁኔታዎች አጨቃጨቁ፣ አከራከሩ። ነገሩ እየሰከነ ሲመጣ በርከት ያሉ አዝማሚያዎች ታዩ።

ሀ) «<u>ለወያኔ መንግሥት ድጋፍ መስጠት</u>»– ሻቢያ የፈፀመውን ጥቃት በመረዳት፣ በመቆጣትና በነፃነት አፍቃሪነት አንዳንዶች 180 ዲግሪ ዞሩ። ገንዘብ ለማዋጣትም ሕዝብን አሰባሰቡ። ይህም በዋሽንግተን ዲሲ ለአምባሳደር ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ሃሳቡን በኢትዮጵያውያን ውስጥ እንዲያሰርፅ ዕድል ሰጠው። ይህ መስመር በርካታ ጥያቄን አስከተለ።

ለ) <u>ድጋፍ በገደብ</u> (Conditional support) አንዳንዶችም የወያኔ መንግስት የፖለቲካ እስረኞችን ከፈታ፣ የክልል ፖሊሲን ከቀለበሰና ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር የበጐ ፈቃደኝነት በማሳየት ለመተባበር ዝግጁ ከሆነ የማንተባበርበት ምክንያት አይኖርም ሲሉ ገለፁ።

ሐ) <u>ከትግራይና ከአፋር ሕዝብ ጐን መቆም</u>፣ ከጐናቸው ተሰልፎ ወራሪውን ኃይል ማስወጣት፣ የመቋቋሚያ ገንዘብ በወያኔ በኩል ሳይሆን በሰብዓዊ የዓለም ድርጅቶች (NGO's) በኩል መላክ። ይህም አባባል ራሱን የቻለ ድክመት ነበረው። በመሰረቱ ጦርነቱን የሚያስተባብረው የወያኔ መንግሥት ስለሆነ ከትግራይና ከአፋር ሕዝብ ጐን ስንሰለፍ ለአጠቃላይ ለጦርነቱ ዝግጅት (Effort) ደጋፊዎች ነን። ይህም ማለት በአዝማች ወያኔ ሥር ነው የምንሰለፈው። የተጠቀሱት የውጭ ሰብዓዊ ድርጅቶችም (NGO's) ከዚህ በፊት በተለያየ መንገድ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ሰርተዋል። በአማራጭ ኃይሉም በኩል ይላክ የሚሉም አሉ። አብዛኛው የተቃዋሚ ደጋፊ የሚቀበለው ሃሳብ ነው።

መ) <u>ምንም አይነት ድጋፍ ለወያኔ መስጠት አያስፈልግም</u>። ሁኔታውን የፈጠሩት ወያኔና ሻቢያ በመሆናቸው፣ የኢትዮጵያ ድንበርም እስከ ቀይ ባሕር ስለሆነ ከባድመና ሽራሮ ኢሳያስን ብናስወጣም ኢትዮጵያ የተቆረሰች ሀገር በመሆኗ ነፃነትን ለማስጠበቅ የምንችለው ወያኔን ስናንበረክክ ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብም አለ። ይህ አስተሳሰብ ድንፈኛ ነው የሚሉም አሉ።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

ይህ ውዥንብር በዚህ እንዳለ ተቃዋሚ ኃይሎች በትንተና ደረጃ እነዚህን ነጥቦች አንድ በአንድ በማንሳት የማያሻማና ግልጥ ያለ ፖሊሲ ያወጡ አይመስለኝም። እንዲያውም እነርሱ ያወጡት መግለጫ በአዲስ ዘመንና በኢትዮጵያ ሔራልድ የግልብጥ ፕሮፖጋንዳ መጠቀሚያ ሆኗል። በተለይም ከአንድ ኢትዮጵያ ስብሰባ በኋላ አዲስ በተቋቋመው ግብረ ኃይል (Task Froce) ወደ ሃያ አንድ ድርጅቶችን

ያጠቃለለው መግለጫ ለልዩ ልዩ ትርጉም ስለባ ሆኖ እያጨቃጨቀ ነው። ለጦርነቱ ከሕዝቡ ጐን ተሰልፈን እንቆማለን ስንል ምን ማለታችን ነው? ጦርነቱ ከተከፈተ ወያኔ ስለሚመራው ይህ አባባል «አልሸሹም ዞር አሉ» አያሰኝም ወይ?

የኔ ውድ!

ስለሆነም ወያኔን የሚቃወሙ ድርጅቶችና የሕዝብ ክፍሎች የሕዝብ ተሃድሶንና የሀገርን አንድነት እንደገና ለመመስረት ይህን ሁኔታ በአንክሮና በአስቸኳይ በመመርመር የማያዳግም ምላሽ መስጠት መቻል አለባቸው። «ግርግር ለሌባ ያመቻል» እንዲሉ በዚህ አጋጣሚ የሊቀመንበር ማእንና የቺያንጋሼክን የአንድነት ታሪካዊ ግንባር እንደምላሽ በመስጠት የሚከራከሩ የወያኔ ደጋፊዎችም አልታጡም። ሌላው ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞና አዲስ ድርጅት ፈልፍሎ ስልጣን ቢገኝ «ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት» መስርቶ በቦሌ በኩል ሊገባ ያቆበቆበም እንዳለ ይሰማል። ነባርና አሰባሳቢ ድርጅቶችን ከመርዳት እንደዚሁም ኃይላቸውን ከማስተባበር ይልቅ እነርሱን በማዳከም ምናልባትም ገዋ (Vaccum) ቢፈጠር ከውጭ የስለላ ኃይሎች ጋር እየተጠቃቀሱ ውርውር የሚሉ የ«ዕድል ነጣቂዎች» (Opportunists)ም ተፈጥረዋል።

እያ ወርቃየሁ!

በርግጥም በርካታ ሀገር ወዳጆች የኢትዮጵያ መደፈር አስቆጥቷቸው ከአፋርና ከትግራይ ሕዝብ ጐን እንደሚቆሙ ገልፀዋል። ለወያኔ ግን ድጋፍ ከመስጠት ተቆጥበዋል። ሕዝባችን ጦርነትን ባይደግፍም (ጦርነት የሚደገፍ አይደለምና) ጦርነቱ ከተከፈተ የተቻለውን እንደሚያደርግ ይሰማል። ትልቁ አስቸጋሪ ስሌት (CALCULUS) ደግሞ ትናንት ኢትዮጵያን ሲያፈራርስ ከነበረና ለኤርትራም መገንጠል በአዲስ አበባ የሚኖሩ ኤርትራውያንን እየገፋፋ ለነፃነት ምርጫው (REFERUNDUM) ድምፃችሁን ስጡ እያለ ከቀሰቀሰ አሳፋሪ መንግሥት ጋር መሰለፉ ነው አብዛኛውን በውጪ ያለ ዜጋ የከበደው። በቅርቡ አንዳንድ ስብሰባዎች በኤርትራውያን በአዲስ አበባ ቀበሌዎች ተካሂደው እንደነበረ ታውቃለህ። አብዛኞቹም በግል ሲጠየቁ «ኤርትራ ነፃ የተቋቋመችበትን ውሳኔ ሕዝብ እንዲደግፍ በተለይም ኤርትራውያን ድምፅ እንዲሰጡ የኢሕአዴግ አባላት ቤት ከቤት በመሄድ ቀስቅሰዋል፤ ዛሬ ደግሞ ከሀገር እንድንወጣ ያሸብሩናል፤ ድምፅ የሰጣችሁ እያሉ ይጠቁሙናል፤ ይህ እጅግ አሳዛኝ ድርጊት ነው» ይላሉ።

ይህንንም እያወቁ ነው አንዳንድ በውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለታዋቂነትና የሕዝብን ስሜት አባብሶ በተገኘው አጋጣሚ ድርጅት መስርተው የግለሰባዊ እኩይ ፍላጐት ለማሟላት የተሯሯጡት። አንዳንዶቹም የተረጋገጠ መረጃ ባይቀርብም ምናልባት የወያኔ መንግሥት ቢወድቅ የገዋ መፈጠር የሚያስከትለውንና የምዕራቡን የጥቅም ፖሊሲ የሚጐዱ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር በስለላ ድርጅቶች የሚገፋ እንደሆነ ይደመጣል። ይህም በዚህ እንዳለ «ሀገሬን» ነፃ ለማውጣት እዘምታለሁ የሚልም ረጋ ሠራሽ ታያለህ፣ እንኳን ሽራሮ ሄዶ ሊዋጋ ቀርቶ አርባ ያርድ ሲራመድ ላቦት በላቦት ይሆናል፣ ቁና ቁና ይተነፍሳል። እዚህ ላይ ወያኔ በአሜሪካ በሰፊው እንደሚያራምደው ፕሮፓጋንዳ ያለውን መንግሥት አንደግፍም ማለት እንደአነግ መሆን ወይም ያገር መደፈርን አሳንሶ ማየት አይደለም። ኢሕአዴግ ወይም ወያኔ የተቃዋሚዎችን ልብ ለማግኘት ማድረግ የሚገባው ቅድመ ዝግጅቶች አሉ። እነዚህ ጦርነቱን ለማሸነፍ ከሌሎች የጦርነት ቅድመ ዝግጅቶች ጋር በእኩል ደረጃ የሚታዩ ናቸው። የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣ የክልል ፖሊሲ ይታጠፍ፣ መለስ ዜናዊ ላደረሰው ጥፋት ይቅርታን ይጠይቅ ፣ .. ወዘተ ናቸው። እውነተኛ አንድነት የሚመሰረተው ተሐድሶም ሊመጣ የሚችለው ጐጂ ስህተቱን ሲያምን ነው። አባቶች «የወጋ ቢረሳ፣ የተወጋ አይረሳ» ይላሉ።

ዛሬ የወያኔን ሃገር የማፈራረስ የ7 ዓመት ሂደት ረስቶ ሻቢያን ከባድመ ማስወጣት የኢትዮጵያን ልዑላዊነት ማስከበር ነው የሚል ፖለቲከኛ ቀይ ባሕርን፣ አሰብንና ምፅዋን መርሳት አይኖርበትም። የእርሱ ወያኔን ለመደገፍ ማሽቃበጥ በተቃዋሚዎች ላይ ያለውን ጥላቻ አላበረደውም። በቅርቡ ገብሩ አሥራት የትግራይ ክልል ርዕሰ ብሔር የተናገረውን ታስታውሳለህ «... የትምክህት ጋዜጠኞችና ትምክህተኞች የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማጫረስ ደንታ ስለሌላቸው፣ ለእኛ ኢትዮጵያውያን ድልም ምንም ደንታ ስለሌላቸው ይህን ነገር እንደ ድክመት አድርገው በማቅረብ መንግሥትንና ሕዝብን፣ ኢሕአዴግንና ሕዝብን ለማራራቅ የሚያደርጉትን ሙከራ አለ» ብለዋል። ለገብሩ አሥራት ተቃዋሚ በሚባሉ ኃይሎች ወያኔን መቃወምም መደገፍም አንድ ናቸው። ከጐሳው ውጪ የሚመጣውን ድጋፍ እንኳ ይጠራጠራል፣ ዘረኝነት ማለት ከዚህ የተለየ አይደለም። አሁንም ጦርነቱ ቢከፈት ከአፋርና ከትግራይ ሕዝብ ጐን መሰለፉ ተገቢ ነው። ውጭ ያለነው ማድረግ የሚገባን ከወያኔ ጋር ትስስር በሌላቸው ድርጅቶች ርዳታ መላክ ነው። ሄጄ እዋጋለሁ የሚልም ካለ ጥሩ! ምርጫው ነው። ወያኔ በአሁኑ ደረጃ በአሜሪካ አማራውን እንኳ በመቅረብ «ካንተ በላይ ሀገር ወዳድ ካንተ በላይ ዴሞክራት» ይለዋል፣ ነገሩ ድጋፍን መፈለግ ነው። ትናንት ከሻቢያ ጋር ሆኖ ነፍጠኛ እያለ ይሳደብ ነበር።

ስለሆነም የተቃዋሚ ክፍሎች ይህንን የተወሳሰበና አደገኛ ሁኔታ መዝነውና አጥንተው ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ከዘረኝነት፣ ከጦርነትና ከድህነት ለማላቀቅ የተራቀቀ ታክቲክና ስትራቴጂ መንደፍ ይኖርባቸዋል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ መቻቻልና መደማመጥ ተገቢ ነው። ይህን በሚመለከት እነሆ ትንሽ ግጥም።

# መቻቻል

**መቻቻል**
የዲፕሎማሲ ፍሬ ነው ... የመከባበር ምንባብ
አይደለም የጠንቋይ ድግምት...የደብተራ ባሕረ ሐሳብ፤
ግድፈቱ ባልሰራ ቁጥር ... ፍኖቱ የማይሰምርለት
አይደለም እኮ መቻቻል ... የቲዎሪ አውደ ነገስት

**መቻቻል...**
የራስንም መስጠት ነው ... ሌላንም መዝኖ ማቀፍ
ሚዛኑ እንዳያጋድል ... ታንኳው በውል እንዲቀዘፍ

**መቻቻል...**
ግማሽ መንገድ ተዳርሶ ... አደራውን መቀባበል ነው
እንደምኒሊክ ቦስጠኛ ... የፖኒ ኤክስፕሬስ የኛው
ግብን ለመምታት መኳተን...ለበለጠ ታሪክ መድረስ ነው

**መቻቻል**
የራስን እየሰጡ ... ለማስተባበር በ«ወበራ»
ከሌላም መቀበል ነው ... እየለኩ በየተራ፤
የመደማመጥ ስልት ነው ... መፍትሔውን የሚያጋራ
ወገንን የሚሰበስብ ... በልዩነት የማይኩራራ

**መቻቻል ... አይደለም!**
የዱከመን ጉሬዛ ይመስል ... ቅርንጫፍ ላይ መፎለል
የሌላን ሚዛን መለካት ... በሽኮለሌ መንጠላጠል
ዥዋዥዌ መጫወት ... አይደለም ትግል መቻቻል።


**መቻቻል ... አይደለም!**
ግብታዊ ነገር ሲመጣ ... በስሜት ሳማ መንቆጥቆጥ
የቸኮለ ጅብ ይመስል ... ቀንዱን ከጆሮ መሰቅጠጥ
የቆመበትን ድልድይ ቀርፎ ...ለጠላት ድጋፍ ማሽቃበጥ

ደግሞ ጊዜው ሲለወጥ ... እንደገና መርመጥመጥ
አንድነትን አስታኮ ... ተከፋፍሎ መጋለጥ
የጋራ መሪ ሳይሆኑ ... በጩኸት ስሜት መበለጥ።

**መቻቻል ... አይደለም!**
ማን ቀደመኝ ሳይሉ ... ለዝና ተመሳጥሮ
አብሮ እንዳይጓዙ ... የድርጅት ስም ቀይሮ
ሌላው ተግባር እንደሌለው ... የተግባር ዕዝ ተርትሮ
ስልጣን ቢገኝ ተብሎ ... በትዕቢት ተወጥሮ።

**መቻቻል ... አይደለም!**
«የጠላትን ጠላት መቅረብ»...አፍራሽን ማገዝ አይደለም
ከወገን ጋር መጋጨት ... በሾሌ ቃል መሰጣጠም
እውነት እያደር እንዳይጠራ ... ውሸትን መገጣጠም
በሀገር ወዳድነት ስም...ጉልበታችንን ማድከም
ለጠላት ጥይት መስጠት...ወገንን ጠልፎ ማጣመም
በውጭና በእኛ ሴረኛ...ኢትዮጵያዊነትን ማጨለም።

ቸር ይግጠመን
ገብርዬ አትላንታ ጆርጂያ

# A TO Z
## ELECTRONICS & GIFTS


TV. - VCR. - Cameras - Phones - Stereos - Fax Machines
Watches - Luggage - Toys -Gift Items - Perfumes

**ኤ ቱ ዚ ኤሌክትሮኒክስ**

ከፓል ሲካም ወደ ኤን ቲሲና ከኤን ቲሲ ወደ ል ሲካም ቪዲዎ መገልበጥ
ኢትዮጵያ መሥራት የሚችሉ ባለ 220 ቮልት የኤሌክትሪክ ዕቃዎች
በርካሽ ዋጋ



1713 Church St. Suit A-1
Decatur, GA 30033
(Kroger Shopping Center)
Jayendra Patel & Dipa Patel
Tel/Fax: (404)299-9196



*Hours:*
*Tuesday to Sunday*
*11:00 am - 8:00 pm*
*Monday Closed*

# ከዋትሳፖች
# ይድረስ ለጦራ ጦጦራ

የጦራን ፅሁፍ በላንዳፍታ መፅሄት አነበብኩት፣ ከእንግዲህስ አልቁንጥም! ቁንጡን ለቁንጠኞች።

ሲሆን ለነብሲ፣ ካልሆነ ለስጋዬ ለራሴ፣ ለጉረቤቴ ዘመን ጦጦራ … ጦጦራ … ጦ .. ጦ .. ራ ለጉሳየም አልልም፣ ጦራ እኔ ልሙት የርስዎን እጅ መንከስ ይሆናል። ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው ተብሎ የለ!

ገንዘብ ያቀብጣል፣ ያቅበጠብጣል … ያቁንጣል፣ የገንዘብ ችግሩ ይሄ ነው። አንገት ላለው ግን ዞሮ ማየትም ስለሚያስፈልግ መረን አያስለቅቅም፤ ይህንስ እንተማመን።

በዘመን ጦራ ያለው ችግር ግን የዝንጀሮዋ ዓይነት ነው። ዝንጀሮዋ አግር ጥሏት … የራሷን ቂጥ በመስታወት አይታ በሰው ትስቅ የለ፤ ወይ ጉድ! ምን ይሆን ታሪኩ?

አሉ ጦራ! «ሽገሮች አሜሪካ የሚመጡ ልጆችን ይሽረግጓቸዋል»። ዋትሳፖች እያሉ ይሆን? ወይ ጉድ ከሞቱ አሟሟቱ አሉ። እንደሀብታችንማ ቢሆን አስለቃሽ ገዝተን በገንዘብ እናስለቅስ ነበር።

ይልቅስ ጦራ ጦጦራ ስለእኛችን የተናገሩትን ተቀብየዋለሁ ከራስዎ ስልቻ እንደተገኘው «አባ ገላኔ ልጅዎት ከአሜሪካ ሲመጣ ምን አመጣልዎት ሲባሉ፣ መድኃኒያለምን ያለዋትስአፕ ምንም!» አሉ።

ወርቅ በያዝንበት አመድ አፈስንበት እንዳይሆን ስጋሁ። ውሻ አጥበን፣ ዳይፐር ቀይረን ለምንልካት ገንዘብ እንኳ ምስጋና እንጣባት!! ሰዎች የሚያሙን ደግሞ ሌላ ነው። ለጉራ ስትሉ አይታችሁት የማታውቁትን ቪዲዮ ካሜራና ጌጣጌጥ ለመታየት ብቻ ወዳአገር ቤት ስትሄዱ ትገዛላችሁ፣ ሀብታም ሀብታም ትሸታላችሁ፣ ውሻ የምታጥቡ ሳይሆን አስተዳዳሪ ትመስላላችሁ ይሉናል። አንድ ስም አይበቃንም እንደ! የኢትዮጵያ ሀብታሞች የኛን ግማሽ ለህዝብ ቢያከፋሉ እንዴት ቆንጆ ነበር።

ጦራ ምክር ያውቃሉ መከረውናልም፤ ምክር ደግሞ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሲሆን የበለጠ ነው። የከፋፍለህ ግዛ መደብ የተጀመረው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ብል አልሳሳትም። የጦራ ወንድም! እኔ መደብ ስል የላብአደር፣ የአርሶ አደር፣ ንኡስ ከበርቴ ማለት ሳይሆን፤ የሀብታምና የድሐ፣ የባለስልጣንና ስልጣን የሌለው፣ የተማረና ያልተማረ፣ የሰሪና የአሰሪ የሚባለውን ነው።

የእነ ጦራ ዶክተሮች፣ አንዳንዴ ለበሽተኞች መድኃኒት ሲያዙ በእንግሊዝኛ ቃል «ቱሞሮ» ሲሏቸው የነገውን ቀጠሮ የሀገሬ ባላገር ካስቦዳሌ ቱሞሮ ታዘዘልኝ እያለ ወደፊርማሻ ይሄድና የፊርማሻውን ጌታ ሲጠይቀው እነ ጦራ ደግሞ ለሳምንት መሳቂያቸውን በማግኘታቸው ተደስተው ሌላውም ጦራ እንደነሱ እንዲደሰት የኛው ቱሞሮ ስላለቀ ወደ አራዳ ሂድና ጠይቅ ይሉትና ያ ባላገር ፊርማሻውን በሙሉ ጠይቆ ሳይሳካለት በመቅረቱ ያስኳላን ትምህርት የሰይጣን ትምህርት ነው የሚል ስም አውጥቶለታል። በመጨረሻም አያቶቹ የነገሩትን አረግሬሳ ጨምቆ በመጠጣት ከቤቱ እንደኩራ ይሞታል። – በቱሞሮ ከመዳን ባረግሬሳ መሞት እያለ።

ደግሞ እርጉዞችስ ለመውለድ ሲሄዱ የሚሰጣቸው የምጥ ማስታገሻ ጥፊ ነው፤ ገልብጠሽ እንዳልሰጠሽ አሁን አፍሽን አትክፈቺ፣ እደግምሻለሁ ዋ! ተጠንቀቂ ይባላሉ። ይህን ዋትሳፖች እናውቃለን። ታዲያ ስንተዋወቅ አንተናነቅ ብንል አይገባንም?

ሌላው መደብሳ! እነዚያ ዋልጌ ወንዶች ሚስቶቻቸውን አስቀምጠው ከሰራተኞች ልጅ ይወልዳሉ። ታዲያ የተወለደው ልጅ እንደ ልጅ አይቆጠርም። እነሱ ሲደበደቡ፣ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሲባረሩ፣ ደሞዛቸውን ያለፍርድ ሲቀሙ፣ ራሳቸው የሰሩትን ምግብ እንኳ እንዲበሉ የማይፈቀድላቸው፣ ሲበሉ ማጀት ገብተው እንጂ በአደባባይ እንዲታዩ የማፈቀድላቸው መሆኑን ይህ እውነት አይደለም እንዴ?

ታድያ እንደነጦራ ያለው ድርሰተኛ ያችን የመተረክ ችሎታቸውን በጠቃሚ ነገሮች ማዋሏን ትተው ስለማይጠቅመው ስለእኛ ስለስደተኞች በትችት ሲራቀቁ ይታያሉ። ነገር ግን በአገራችን መሬት የጠገበው የአረብ ዲቃላ ከበርቴ የአገራችንን ህፃናት በጌጥ እያታለለ ጃፓኖች በኮሪያ ሴቶች እንደፈፀሙት ወንጀል የወሲብ መጫወቻ ሲያደርጋቸው እዛው አጠገባቸው እያዩ ሀሲናቸው ዝግ ነው ቀለማቸውም ደረቅ ነው።

ታድያ ያገሬ ሰርቶ አደር አገር ጥሎ ተሰድዶ የሄደው ወገኑን ቢያሙበት ዱባና ቅል አስተዳደጉ ለየቅል ሆኖበት ይህ ቦለቲካ ነው ብሎ አራቱን ይነጥብበታል። ጦራዎች ስለትግል ያውቃሉ(ያቃሉ) በሚገባ ማለቴ ነው። የሚታገሉትም ትግልን ነው። የትግል … ትግል።

ታዲያ የነጦራውን ትግል ከህዝቡ ትግል ለመለየት የመለያ ስም ቢጤ ብናወጣለትስ? ትግል አለማቀፋዊ፣ ትግል ሁለገባዊ፣ ትግል ሰብአዊ፣ ትግል ዘለአለማዊ .. ወዘተ ይህ ትግል ከትግል ትግል ይለያል … ዋትስአፕ! እንግዲያውስ ስለትግል ተብሎ የተወሰደ ማንኛውም ትግል ስህተቱም ትግል ነው። እርፍ!

ለዚያም ነው እየታገሉ የሚሞቱትን የምንዘክር እነአሰፋ ማሩን፣ ዳግማዊ ዘለቀን፣ እነተስፋዬ ታደሰ። እንዴታ! የታሰሩትን እነፕሮፌሰር አስራትን፣ እነአምሀ ኢየሱስን …። ከዚያም አልፎ

ተርፎ የትግል ደጋፊዎችን፣ አጋሮችን፣ ጠላትን አሳፋሪዎችን በእንቁላልም ይሁን በቲማቲም። ቲማቲም ነው ብሎ መዳፈር ከበዛ ደግሞ ዋትሳፖችን መጉብኘት ነው። ጥሬው ቲማቲም ይቀርና አብስለን መረቁን እናጠጣለን። አዎ ጠልተነው የወጣነው ወድዶን ከተከተለን መድረሻ ካሳጣንስ ዝም አንልም። ከዚህ እኮ ባዶ ሽድሽቲ የለም። እከከየ!!

ታዲያ አሉ፣ ታጋዮች «የታጋይ ታጋዮች» ማለቴ ነው። ታጋዮችን ሲገድሉ ይስቃሉ ... አሀሀሀ አንድ ገዳይ ... ሁለት ገዳይ ... አቤት አቤት አቤት! ይህ ቀላል ነው። ችግሩ ግን ለተጉዳው ሕዝብ ተሰልፎ መታየቱ ነው። ቅሬታን ማሰማት መቻሉ ነው። ሳይልከሰከሱ። ያለውን መወርወር – ለትግል። ይህን ስል ከነጦራ ይቅርታ እየጠየቅኩ ነው። ምክንያቱም እኛ አሜሪካ ያለን ታጋዮች ተጋዳላይ የለንም። ሆኖም ግን ጦር ሳንሰብቅ፣ ሳንጃ ሳንወድር፣ ደም ሳናፈስ መታገላችንን እንጦራን ፈርተን አናቆምም። የሀሊና ጦርነት!!

ታዲያ እኛ ስንታገል፣ ድርሰት እየተደረሰብን፣ እንቆቅልሽ ድብብቆሽ ስላንትያ ቁማር ታሪክና ምሳሌ፣ ቅኔ እየተዘረፈብን እየተዘመረብን ብሎም እየተፎከረብን ትግል ከደም መፋሰስ አይከብድም እንዴ ጦራ?

በእርግጥ እንቁላል ወርውሮ ጠላትን መምታት ራስ አይፈነክትም፣ ደም አያስፈስስም። ያን ብቻ ከሆነ ትግል የምንለው አናርኪ መሆን ነው። አዎ ትግል ዘለአለማዊ ነው ተብሎ የለ። በመጀመሪያ የጠላትን ክብር እንደጌሾ ቅጠል ካቀለሉ በኋላ፣ አዋርዶ፣ አሳፍሮ፣ አርበድብዶ እርሟን እንደበላች ድመት እያመነመኑ መፈራረጃ ሳያደርጉት ቢገድሉት ዘለአለማዊ ድልን አያቀዳጅም። እንዲያውም ደካማነት ነው።

ጦራ ሲያሾፉብን እንዲህ አሉን፣ አሜሪካ ውስጥ ለመለስ ዜናዊ የወረወራችሁትን ቲማቲምና እንቁላል ለእኛ ለኢትዮጵያውያኖች ብትልኩልን ይጠቅመናል አሉ። ዋትሳፖች በዚህ ተገርመናል። እነጦራ ራሱ ያገሬው ህዝብ ያመረተውን ለልማት እያላችሁ እየቀማችሁት ከእኛ የተላከለትን ልትምሩለት ነው? በእጁ በልቶ ያልጠገበ በሰው እጅ በልቶ እንደማይጠግብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል። ስለሆነም ለክብሩ ሲሉ የተጋፈጡለትን ሁሌ ሲያመሰግን ይኖራል፣ ለትግል የዋለ ስህተቱም ትግል ነው ተብሎ የለ። አይደለም እንዴ ጦጦራ! ካልሆነ በእኛ ከማዘን እነጦራም ታገሉ እንጂ!!።

ጦርየ ጦጦራ ... እንደፈረስ ጋልባችሁ፣ እንደሰጉን አቀርቅራችሁ፣ እንደ ውሻ አሽትታችሁ፣ እንደ ጭልፊት ጨልፋችሁ፣ እንደጥንብ አንሳ ጉትታችሁ፣ እንደዶሮ ጭራችሁ፣ እንደ ዝንብ ወርራችሁ፣ እንደፍየል ቀንጥባችሁ፣ እንደእባብ ተስለክልካችሁ፣ እንደሙሽራ ኩላችሁ የምትቀርቧት ይችን ቢጣዋን ጋዜጣችሁን ለታሪክ አስቀምጧት። ልጆች ይማሩባታል፣ እውቀት ይቀስሙባታል፣ ጦራ ጦጦራ ። ምርጥ ምርጡን ለህፃናት። ታሪኩ እንዲህ ነው። ከጦራው ፅሁፍ፣ «ሶማሌዎች ያንኪዎችን በድንጋይ ናዳ አባረሩ። ሶማሌ ዳግመኛ ቬትናም ሆነች። – በድንጋይ።» የገረመኝ ግን ጦራ ሶማሌዎች በድንጋይ ናዳ አሜሪካኖችን ሲያባርሩ ለምን ኢትዮጵያን በመድፍና በአይሮፕላን ለመውጋት ሞከሩ? እኔ ልሙት ጦራ ይህስ ቀላል ነበር። ወይ አለማወቅ ደግሞ ብለን ብለን ወደ ድንጋይ ዘመን ልንመለስ ይሆን? ወይ ታሪክ!

ይህን ተመልከቱ– አሜሪካ ውስጥ "I am from Ethiopia" አይባልም ይላል የጦራ ስልቻ። ፍሬን እየለቀቁ፣ ጣቃ እየቀደዱ፣ ፀጉር እየሰነጠቁ ብሎ ወሬ የለም። ታድያ የት ነን ልንል ኖሯል ጦራ? ምን ብቀጥን ጠጅ ነኝ ተብሎ የለ። ብዙ ከመናገር አራቱን መነጠብ ይሻላል።

ጦራ ሴት ይወዳሉ፣ ፍቅር እስከ መቃብር። እናም እንዲህ አሉ «አሜሪካ ውስጥ እንስት እንዴት ታድላለች!?» አጀብ ነው ጦራን ያመነ ሙላው ዳነ።

እችን እችን ተዉ አሉ ዋትሳፖች። አዎ ሴቶችን አታፈይሏቸው፣ አክብሯቸው። ስለ እንስት ሲነሳ ዋትሳፖችን ይከፋቸዋል። መቸስ እናትም ሚስትም እነርሱ አይደሉ።

ይልቅስ ጦራ፣ ስንተዋወቅ እንደባበቅ። ግልፅ አይደለም እንዴ ማምታታት፣ ማወናበድ፣ ማጋጨት፣ ማፋጨት፣ ሽብር መፍጠርና ተንኮል የጦራዎች ስራ ነው። ገዝግዞ – ገዝግዞ ከአገር ያስለቀቀን ይህ በመሆኑ ዋትሳፖች በደምብ እናውቃለን። ስለሆነም ሽረሪቷን ስለምናውቅ በድሯ አንጠለፍም። ንቀን እንዳናልፋት ግን የተገደድንበት ሌላ ሌላ ነገረ አለ፣ ነገሩ እንዲህ ነው። ብዙ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ይህ ምስጢር ካልተገለፀላቸው በእነጦራ እየተለቀሙ ለወዳጃቸው ሳይሆን ለጠላቶቻቸው በመሰለፍ ወገን በወገኑ እንዲዘምት ይሆናል። ብሎም ኢትዮጵያ ዳግም ቬትናም ሶማሌ ብቻ ሳይሆን የጦር አውድማ እንሆንና እንቀራለን።

ስለዚህ ጦራዎች፣ ዋትሳፕ ቋንቋው ከሆነ ችግራችሁ በሳንጃ ወግተን፣ በመቀስ ቆራርጠን፣ በእሳት አቃጥለን አመዱን ለንፋስ እንስጠው። በሌላው በሌላው ግን በትግላችን በህብረታችን፣ በጉሳችን በሀገራችን ቄስ አትሁኑብን ስንተዋወቅ አንተኖነቅ።

ከተስፋ ኮሎምበስ ኦሀዮ

# ደብዳቤዎቻችሁ



## የሕዝቡ ሹክሹክታ፣ ቁጭትና ፍላጐት

*ከተመስገን በላይ – አዲስ አበባ*

የአዲስ አበባ ከተማ ለሹክሹክታና ለመንግስት ችግር ጆሮው ቀዳሚ ነው። አረጋውያን፣ ወጣት፣ ጉልማሳ፣ ምሁራን፣ ሁሉም ለወሬ ጆሮውን ሰጥቶ የሰማውን ላልሰማ በማሰማት በአንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት ችግርና ሳቦታጅ ይወያያል፤ የሚመጣውን ይገምታል መሆን ያለበትን ይናገራል።

ይህ የዓለም እግር ኳስ ጨዋታ አዕምሮውን ባይከፍለው ኖሮ ሁሉም ልቡ ያለው ጦርነቱ ላይ ነው። ሕዝቡ ምን ይላል? አገሪቷ ውስጥ ምን እየተደረገና ሕዝቡን እያስቆጨ ነው?

ጦርነቱ ከተከሰተ ጀምሮ ብዙው ክልል በኤርትራ መንግስት ላይ ተቃውሞውን ያሰማል፣ መግለጫ ይሰጣል፤ እርዳታ ይሰበስባል። በጉሳ የተመሰረተው የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ትክክል ያለመሆኑ የሚታይበት ጊዜ ነው። ስለዚህም የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም በኢኮኖሚ መገንባት እንዳለበት ብዙ ምሁራንና ሕዝቡ በቁጭት ይናገራሉ። እያንዳንዱ ክልል የሚፈለገውን አደርጋለሁ ይላል እንጂ ‘ሀገርህ ተወራለችና ተነስ’ አይልም። ግን ዛሬም እንደትናንቱ ኢትዮጵያዊነት ስሜቱ እየተናነቀው ነው። መዝመትም ጀምሯል።

ነፋሱ በዛ፤ ይህ መንግስት እንጃለት! ከሚለው ጥንታዊ አባባል ተነስቶ የአቶ መለስን መውረድ ከጦርነቱ ጋር የሚናፍቅ ኢትዮጵያዊ ብዙ ነው። በሚኒስትሩ ለዘብተኛነት እጃቸው እንዳለበት ከመተንተን አልፎ የሰላም ኖቤል ተሸላሚ ለመሆን አገሪቱን እያስቀጠቀጡ ነው እስከሚል አስተያየት ይሰነዝራል ሕዝቡ። የትግራይ ሕዝብ በበኩሉ በአቶ መለስ ላይ ከጦርነቱ በፊት የነበረው ጥላቻ አገርሽቶ ዛሬም ከፍተኛ ተቃውሞውን ያሰማል። የደበደበን የኤርትራ መንግስት ሳይሆን መለስ ነው እስከማለት ደርሷል። ይህ በይህ እንዳለ አቶ መለስ ዜናዊ የቁም እስረኛ (ከአገር እንዳይወጡ የተከለከሉ) ሆነው ስራቸውን እየሰሩና ግምገማ ላይ መሆናቸውን የወሬ ሹምሹምታው በከተማው ያስተጋባል። እስር እንደማይቀርላቸውና በትረ ስልጣናቸውን እንደሚለቁ ይገመታል። በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የጦሩ አዛዥ የሆኑት አቶ ተፈራ ዋልዋ እስር ላይ እንደሆኑም ይነገራል። ሰውየው በዚህ ጦርነት ወቅት አንዴም ድምፃቸው አለመሰማቱ ወሬውን የበለጠ ያጉላዋል። ዛሬ በዚህ ጦርነት ምክንያት አቶ መለስ ስልጣናቸውን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን እንዲለቁ ሕዝቡ ይመኛል። ምኞት ብቻ ሳይሆን መሆን አለበትም ነው የሚለው ሕዝቡ። አቶ ስዩም መስፍን ከሰጡት የመጀመሪያው ጋዜጣዊ መግለጫ ተነስቶ እስካሁን ኢትዮጵያዊነት ተሰምቷቸዋል፤ ቁጭት ታይቶባቸዋል የሚለው ግምት በሕዝቡ ስሜት ውስጥ ስለሰረፀ ነው የአቶ ስዩምን መሪነት የሚናፍቀው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የጉሰኝነት ባህሪ የሌለውና ማንም ይሁን ማንም አገሩን እያለማ፣ እያፈቀረ ቢመራው ፈቃደኛ መሆኑ በዚህ ሀሳቡ ያስታውቃል።

ሕዝቡን የሚያንገበግበው የራሱ ሕዝብ ዛሬም እንደቀድሞው ከኤርትራ እየተፈናቀለ በየጠረፉና በየወደቡ መጣሉ ነው። በአንፃሩ እዚህ ካሉ ኤርትራውያን ጋር በሰላም ቆይታው ጥሩ መንፈስ ቢያሳይም ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ይፈልጋል። በተለይ እያሸቋለጡና መሬት እየሳሙ ሪፈረንደሙን ደግፈው መታወቂያ የወሰዱትን በሙሉ። እንደዚህ ሆኖም በሪፈረንደሙ ያልተሳተፉ የኤርትራ ተወላጆች ኢትዮጵያዊ ስለሆኑ እንዳችም ችግር ሊደርስባቸው እንደማይገባ ይናገራል። ሌሎቹ ግን ከስራ ገበታቸው እንዲሰናበቱና እንዲወጡ ይፈልጋል። እዚህ ሆነውም አልተኙልንም የሚል ስሜት ስላለው ነው። ስለሆነም ሕዝቡ የተናገረው ሁሉ እየሆነ ነው ...

ይህ የኢትዮጵያ መንግስት ተብሎ የሚጠራው የኢህአዴግ መንግስት ዛሬም በዚህ ጦርነት ምክንያት የሕዝቡን ስሜት እያቆሰለው ነው። በጦርነቱ የተጐዳው የትግራይ ሕዝብና ትግራይ ብቻ አይደሉም። የአፋር ክልልና ሕዝብም ተጐድቷል። በኤርትራ የሚኖረው ሕዝብ ትግሬው፣ አፋሩ፣ አማራው፣ ጉራጌው፣ ሐረሬው፣ ደቡቡ ወዘተ ከቤት ንብረቱ፣ ከስራው፣ ከኑሮ ገበታው በኤርትራ መንግስት እየተፈናቀለ በቡሬ ጠረፍና በጅቡቲ ወደብ እየተጣለ ነው። የችግሩ ሰለባም ኢትዮጵያ ነች። ይህ ሆኖ ሳለ በጦርነቱ በደረሰ ጉዳት ከሕዝቡ፣ ከመንግስትና ከግል መስሪያ ቤት፣ ከነጋዴው፣ ከየክልሉ የሚሰበሰበው ገንዘብና ንብረት በቀጥታ በትግራይ ልማት ማህበር አካውንትና ቢሮ በኩል ገቢ እንዲሆን ይደረጋል። ለምን? የተጐዳው ብዙው የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከሆነ ድረስ፣ ጦርነቱ ገና ያላበቃና ወዴትና ወዴት እንደሚዘመት እስካልታወቀ ድረስ፣ አንድ ብሔራዊ አገር አቀፍ ኮሚቴ ተቋቁሞ እርዳታው በጦርነቱ ለተጐዱ ወገኖች በሙሉ እንደየሁኔታው መዳረስ አለበት እንጂ በትግራይ ልማት ማህበር በኩል መግባት የለበትም፤ ይህ የሚያሳየው ጉሰኝነትን ነው የሚል ቁጭት በሕዝቡ ውስጥ አለ። ይህ ደሞ አስፈላጊውን ገቢ ለማግኘት እንቅፋት ይሆናል። የትግራይ ልማት የተቋቋመው ትግራይን ለማልማት ሆኖ ሳለ የጦርነት ጉዳተኞች ማገገሚያ መዋጮ በዚህ የልማት ማህበር መግባት የለበትም ይላል ሕዝቡ። መንግስት ግን እስካሁን ይህን

ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎታል።

ይህ በይህ እንዳለ አንዳንድ ክልሎችም ምንም እንቅስቃሴ እንደማያደርጉ ትዝብት ውስጥ ወድቀዋል። ምክንያቱም ጊዜው የበጀት መዝጊያ ጊዜ ሆኖ ሳለ ለበጀት የተመደበው ገንዘብ ለጦርነቱ በሚል ሰበብ ወደ ትግራይ ልማት ማህበር ተመላሹን በጀት እያስገቡ ነው። እንደምሳሌ ከሚቆጠሩት የጋምቤላ ክልል አምስት ሚሊዮን ብር፣ የሱማሌ ክልል አራት ሚሊዮን ብር በትግራይ ልማት ማህበር በኩል ገቢ አድርገዋል። ሌሎችም ክልሎች እንደዛው። ለጦርነቱ!!!

ሕዝብ ምን ይላል፣ ብዙ ይወያያል፣ ብዙም ይቆጫል። በማንኛውም መልኩ ባለው መንግስት ላይ ጥላቻ ቢኖረውም፣ በትግራይ በኩል በኤርትራ መንግስት ሊቀረስ የተዘጋጀውን የኢትዮጵያን ድንበር በተመለከተ ግን 'መንግስት መጥላት ሌላ፣ አገር መጥላት ሌላ' በሚል መልኩ ተነሳስቷል። ሕዝቡ በማንኛውም መልኩ አገሩን እንደማያስደፍር ይናገራል ከጥቂት ጉሰኞች በስተቀር። ጥቂት የጉሰኝነት ሰለባ የሆኑ ግን ጦርነቱ የኤርትራና ትግራይ ስለሚመስላቸው ለማነው የምንዋጋውና የምንዘምተው ይላሉ።

ተመስገን በላይ ከአዲስ አበባ

## አትላንታ ወይስ አትላንታዬ

ምንም እንኳ አትላንታን ለማየት ይህ 15ኛው የእግር ኳስ ጨዋታ ዝግጅት ምክንያት ቢሆነኝም በላንዳፍታ መጽሄት ስለአገሪቱም ሆነ ስለ ህዝቧ በተለይ ስለሀገራችን ሰው አጠቃላይ አኗኗር ስልት በተለያዩ ጊዜያቶች ስንረዳ ቆይተናል።

አትላንታ በተባለ ቁጥር ላንዳፍታ ትዝ ይለኛል። የሆነ ሆኖ እኔም የምኖረው አገር ምንም ሩቅ ቢሆንም አውሮፕላን ፍለጋ አልሄድኩም መኪናዬን ወላውዬ ብቅ ማለቱን መረጥኩኝ። ለምን ብትሉኝ— በመጀመሪያ የአውሮፕላን ትኬቱን ለማግኘት ቀደም ብሎ ሪዘርቭ ካልተደረገ ቀኑ ሲደርስ ቢሯሯጡ ዋጋው ሁለት ሶስት እጥፍ ይጨምራል። ለምን ቀደም ብለህ አልያዝክም ብትሉኝ ደግሞ በምኖርበት ከተማ የእግር ኳስ ቡድን መሪዎች ቁር የማይላቸው ከሆነ ምክንያት አለኝ። ለዚህ ለዳላስ የእግር ኳስ ቡድን አንዱ ተጫዋች በመሆኔ ከስድስት ወር ላላነሰ ጊዜ ለሲዝኑ ጨዋታ ስጫወት ከርሜ በዚህ አጠቃላይ አመታዊ ጨዋታ ላይ በኔ ቦታ የሌላ አገር ሰው (ፈረንጅ) ይመስለኛል በትንሽ ዋጋ ሸምተው ቦታዬ ስለተያዘ እንኳን ዋነኛ ተጫዋች ለመሆን ቀርቶ ለቅያሬም ቦታ ስላላገኘሁ ይቅርታ ለዚች ዓመት ተባልኩኝ። ታዲያ ትንሽ እንደመናደድ ብልም በኋላ ስሰማ ግን ነገርየው በእኔ ብቻ የደረሰ ስላልሆነ ታገስኩኝ። እንዲያውም ባይገርማችሁ ዳላስ ሁለት የእግር ኳስ ቡድኖች አሉት፣ ከሁለቱ ቡድኖች የተባረሩትን የእኔ ቢጤ ተጫዋቾችን አሰባስቤ ቦስተኛ ልፈጥርም አስቤ ጊዜ አጠረኝና ተውኩት። ምን ታረጉታላችሁ!! ታዲያ ይህን ሳስብ ባለፈው አንዱ ወንድሜ ኮሚቴዎች ሲበዙ ኮሚቴዎችን ለመቀነስ ሌላ ኮሚቴ መቋቋም አለበት ያለው የላንዳፍታው ቀልድ ትዝ ብሎኝ በንዴት ፈገግ አልኩኝ።

እና ወደ ጉዳዬ ልመልሳችሁና የአውሮፕላን ትኬት ዋጋ በመናሩና ከእግር ኳስ ተጫዋች ግሩፖቼ ስለተለየሁ በሰጠው መኪናዬ የአትላንታን ጉዞ ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር ጀመርነው። የሚገርመው ከአንዱ አገር ወደ አንዱ አገር የሚያገናኘንን ካርታ ይዘናል እንጂ አትላንታ ከገባን በኋላ የት እንደምንሄድ ባለማወቃችን ሳናቋርጥ አንድ ሙሉ ቀን ስንጓዝ ውለን አይደረስ የለም የኔዋ መኪና ከአምስት እንግዶች ጋር በቀጥታ ጆርጂያ ደረስን። ስቃዩ ግን ከዚህ በኋላ ነበር፣ ስቴዲየሙን ወይም አንድ ሀበሻ እንኳን ለማግኘት ከተማው ውስጥ ስንንከራተት ቆየን። ከአንድ ቴክሳኮ ጠይቀን ወደ ሌላው ቴክሳኮ እየገባን ስንጠይቅ፣ ከመንገድ የቆመውን ፖሊስ ጠይቀን መልስ ስናጣ ፖሊሱን ትተን ባለ ሬስቶራንቶችን ፣ ባለሬትስቶራንቶቹን ትተን መንገደኛውን ብንጠይቅ ብናስጠይቅ አውቃለሁ የሚል ጠፋ። በዚህ ላይ ደግሞ ትልቁ ችግራችን የቦታውን ስም፣ የሆቴሉን ስምም ስልክ ቁጥር እንኳ ስላልነበረን (ስላልተነገረን) በጣም በጣም ደከርንላችሁ። በመጨረሻ ቤንዚናችን ማለቁን ስናይ ከአንድ ጋዝ ስቴንሽ ጠጋ ብለን ጋዛችንን እስከአፍንጫው ሞላንና የራሳችንንም ጥማት በመጠኑ አረካንና እንደገና ጥያቃችን ከዚሁ ጋዝ ስቴሽን ባለቤት ጀመርን። የሚገርማችሁ ለዚህ ሰው ስለዝግጅቱ ሁሉ ነገርነው፣ ኧረ ምን እሱን ብቻ የታዋቂ ተጫዋቾችንም ስም ሁሉ ሳንነግረው የቀረንም አይመስለኝም። ብቻ ምናለፋችሁ ሁሉንም በዝርዝር አስረዳነው። እሱ የመሰለው የአትላንታ ፋት ቦል ተጫዋቾችን ስም የምንነግረው ነው የመሰለው። ብቻ ግን የሚገርማችሁ ነገር ቢኖር ለካ እኛ የነበርነው አትላንታ ጆርጂያ ሳይሆን በርኪንግሃም ከሚባል ሲቲ ውስጥ ነበር ያን ሁሉ ጊዜ የምንከራተተው። አትፍረዱብን ድካሙም ስለነበረና የምናየው ትልቅ ሕንፃ ስለነበረና የመኪና ታርጋ ሁሉ አትላንታ ስለሚል በቃ ሙሉ እምነት ነበረን፡፡ ብቻ ይህ ሰው እግዜር ይስጠውና ተጫዋቾቻችንን ባያውቅልንም የአትላንታን መንገድ እንደገና ትክክለኛ አድራሻ ሰጥቶን ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ በደመቀና በልዩ ልዩ አረንጓዴ ተክሎች ተውባ የአትላንታ ከተማ በተዋበ አቀባበል ስንገባ ደስ አለን። ስቴዲየሙን ያገኘን ያህል ተሰማን። የሀበሾች ግርግርም መስሎ ታየን። ብዙ ሰዓት አልፈጀብንም በደመ ነፍስ ትንሽ እንደዞርን ትዝ አለኝና አንድ ጓደኛዬ ከዚሁ ከዳላስ ሊዝናንበት የሄደውን አዲስ የተከፈተውን የፍላሚንጐ የስልክ አድራሻውን ይዤ ስለነበረ ደወልኩለት፡፡ ወደዛው አመራን፣ ፍላሚንጐ ሬስቶራንት ዙሪያውን በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ስመለከተው "ሊር ዮጉ አትላንታ" የላንዳፍታዎቹ አገር ነው አልኩኝ። ባይገርማችሁ እዛው ልቀር ፈልጌ ነበር። (ደግሞም አይቀርም አገሩን ወድጀዋለሁና እንዲህ አይነት ነገረኛ ሰው አንፈልግም ካላላችሁ በስተቀር፣ ግን 'ነገረኛን ሰው' አንዳንዴ አትጥሉት። በሱ የደረሰበትንም ሳይሆን ለሰው ጠበቃ ይሆናል ለመናገር እና ለማስረዳት አቅም ላጠረው ጠበቃ አጋዥ ይሆናልና።

እና አትላንታ በዚህ ሁኔታ ደረስንና ከጓደኛዬ ጋር ተያይዘን የሆነች ረከስ ያለች ማደሪያ እና የገላ መታጠቢያ ያላት ሞቴሌን ያዝኩ። ልብሴን ቀያይሬ

ስጨርስ ከምሽቱ 10፡00 ይላል። ወደ ጨዋታው ቦታ እንሂድ አልኩት። እንዴ አሁንማ ያልቃል አለኝ። ቢያልቅም እንደው ውጪውንም ቢሆን አይቼው ልምጣ አልኩትና ተያይዘን ሄድን። ከቦታው ስንደርስ እንኳን ጨዋታው ሊያልቅ ገና የተጀመረ ነው የሚመስለው። መግቢያው ላይ ሰው ይንጋጋል፤ ከየአካባቢው የሚመጣው ሰው ይገባል፤ ሌላው ደግሞ ይወጣል። የመግቢያ ክፍያ አልነበረም ይህን አልጠላሁትም፤ ሰዓት እላፊ ለመጡ ይህ አስተያየት ጥሩ ነው ባይ ነኝና። የሆኖ ሆኖ ግርግሩም ጨዋታው ሁሉም ነገር ደስ ይል ነበር። ሌላ ዓለም ውስጥ የገባሁ ነው የመሰለኝ።

ብዙ ኢትዮጵያን የሚያኮራ ስራዎች ተሰርተው አይቻለሁ። ብዙ ኢትዮጵያውያንን የሚያኮሩ ቆንጃጅቶች ከወንድም ከሴትም አሉን (ከእኔ ጀምሮ)። የዛኔ ያሰብኩት ግን ይህ ሁሉ ሰው ኢትዮጵያ ቢመለስና ገንዘቡን ይዞ ማለቴ ነው ብዙ ነገር መፍጠር ይቻላል ብዬ ደምድሚያለሁ ተስፋም አድርጌያለሁ ደግሞ አይቀርም አንድ ቀን መግባታችን።

ስለ ውበት ካነሳሁ ዘንዳ አሻ ለመሆኑ አትላንታ በነበርኩበት ጊዜ አንድ ግለሰብ ለፋሽን ሾውና ለተለያዩ አክቲቪቲዎች ፈቃደኛ የሆናችሁ በማለት ሲጠይቁ በነበረበት ጊዜ ከተመዝጋቢዎቹ አንዱ ሆኜ ነበርና ይህን ኢትዮጵያዊ አለባበሴን ከዘመናዊ የአለባበስ ስርአት ጋር ለብሼ እንዳሳይ ለቅዳሜ የቀጠረኝ ልጅ በዕለቱ ስቴዲዩም ውስጥ አልነበረም። ዝግጅቱም አልታየም። እስኪ ስለዚህ ነገር የምታውቁት ሰዎች ካላችሁ ፃፉልኝ ወይም ጠይቁልኝ። እርግጠኛ ነኝ መዝጋቢዎቹ የዳላስ ነዋሪዎች እንደሆኑ ሰምቻለሁ፣ ነገሩ ጥሩ አጀማመር ነው። ካሜራ ቀራጮችም የዲሲ ሰዎች እንደነበሩ ከእነሱው ተረድቻለሁ። በእውነቱ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ጥሩ ነው ኢትዮጵያዊውን በተለያየ ተሳትፎዎች ላይ ወደፊት እንድንጓዝ ይረዳል ባይ ነኝ። ግን ጀምራችሁ አትተዉ።

ምስጋናውን ከመጨረሴ በፊት ዓርብ ዕለት (የኢትዮጵያ ቀን) በአባይ ኢንሴምብል የተዘጋጀው የአገር ባህል ዝግጅት እጅግ የሚያኮራ ነው። የምናለ ክራር፣ የሰለሞን ተካልኝ አገራዊ ቀስቃሽነት የነበረው ዘፈን፣ የዶክተር መላኩ ድርጅታዊ ንግግር፣ ስሙን ረሳሁት እንጂ ስለ አስቴር አወቀና ስለሌሎች ነገሮች ነካ ነካ አድርጉ ለሄደውና ለሁላችሁም ምስጋና ይግባችሁ እላለሁ። ለአገር መቆርቆር ቀላል ነገር አይምሰላችሁ የሁላችንም ኃላፊነት መሆን ያለበት ነው። ከዛ በመቀጠል አንዱ እንግዳችን ይመስለኛል አማርኛ በደንብ አልችልም እዚህ አገር ብዙ ስለቆየሁ በማለት እንግሊዝኛውንና አማርኛውን እያደበላለቀ ንግግር አድርጎ ሳይጨርስ በመሀል ላይ በሰው ጩኸት ላቋረጠው ወገኔ የምለው ነገር ቢኖር አማርኛ ማንበብ የምትችል ከሆነ በአማርኛ ፅፈው ይስጡህ፤ የሚፅፍልህ ካጣህ ለማለት የምትፈልገውን ለእንደኛ ላለው በላንዳፍታ በኩል ጠይቀህ ማፃፉ ይሻላል እንጂ እንደዚህ ደባልቄ እናገራለሁ ብትል ግን በተለይ እንደዚህ ባለው ስብሰብ ላይ ትልቅ ተቃውሞ ያስከትላልና ተጠንቀቅ። እርግጠኛ ነኝ አንተ ልትል የፈለግከው መልካምና ጠቃሚ እንደሆነ ከአጀማመርህ ተረድቻለሁ። ግን ለዛ ቦታ አይሰራም። ያ የኢትዮጵያ ቋንቋ መነገር ያለበት ቦታ ነውና። ይህን በተመለከተ ለፌዴሬሽኑ የምለው እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዳይፈጠር የእንግዳችሁን ማንነት ቀደም ብላችሁ እጥኑ እያልኩኝ፤ እስቲ ወደ ዋናው ጥያቄ መልስ ካገኘሁ ልግባ። ይህ ከተለያየ ከተማ ተጉዞ ለሚመጣው ተጋባዥ ከዚህ ከምናውቀው ውጭ ምን አይነት ትምህርት ትሰጡታላችሁ? ከዚህ ስብስብ (ህዝብ) እናንተስ ምን ትጠብቃላችሁ?

እኔ እንደምለው ፌዴሬሽኑ ድርጅት ስለሆነ ብዙ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፤ የተለያየ ወጪም ይኖረዋል። እንደዛ ስል ደግሞ በደንብ ነግዱብን ለማለት ሳይሆን ሰው ከተለያየ አገር ሲመጣ የሚያወጣውን ወጭ አትዘንጉት ለመጓጓዣ፣ ለሆቴል፣ ለምግብ፣ ለመዝናኛ፣ እንዲሁም ብዙ ብዙ ላልታሰቡ ነገሮች ያጠፋል። በዛ ላይ ስራውን ጥሎ ነው የሚመጣው፣ ለምሳሌ ያህል ብጠቅስ አርብ ለት (የኢትዮጵያ ቀን) ያስከፈላችሁት $10 ብዙውን ሰው አንገብግቦት እንደነበር እኔ ለትዝብት እውጭ ቁሜ ስመለከት ነበር። ብዙው ሰው አንገቱን እየነቀነቀ ሌላ መዋያ ስለሌለው ከፍሎ ሲገባ፤ አንዳንዱ ደግሞ እያማረረ የብራዚልንና የዴንማርክ ጨዋታ እያለ በማለት ሰበብ እየፈለገ ተመልሶ መሄዱን አስተውያለሁ። ለወደፊቱ ግን እኔ የምመክራችሁ የመጨረሻውን ቀን ብቻ ከመጀመሪያው ብዙ ባልተለየ ዋጋ ለምሳሌ አምስት ብር የነበረውን ሰባት ብር አድርጋችሁ ተሸጋገሩ እላለሁ።

ውድ አንባብያን፣ ከመጀመሪያው አንቀፅ ላይ ልገልፀው ያልኩትን ከመጨረሻው ላይ ላስቀምጠው የወሰንኩበት ምክንያት ለሁሉም ሰው ግልፅ ነው እላለሁ።

ከአሁን በኋላ እድሜዩ እየገፉ ነውና አንጠልጥላችሁ አትጥሩኝ ከቻላችሁ ወ/ሮ አስቴር በሉኝ ይህ በየአደባባዩ የምታዘፍኑኝን ሰቁሙ ከተቻለ በግል ካልተቻለ ደግሞ ሌላ ለየት ያለ ነገር ፍጠሩ ምን ዓይት ህዝብ ነው እባካችሁ!! በማለት እኒህ ወ/ሮ አስቴር ምሬታቸውን ሲገልፁ በገደል ማሚቶ ስለተሰማኝ እናንተ ሰዎች እባካችሁ አንድ በሉ እላለሁ።

ይህች (እኒህ) ወ/ሮ አስቴር እኮ በአሜሪካ ማዶና ወይም ዊትኒ ማለት ነች እንደምንም ብለን ወደ እነሱ የምንጨምርበትን እናስብ — ያለበለዚያ ግን ዋ የጉድ ጉድ ነው የምታሳየን። ይኼው አሁን ተጀምሯል ...

እስኪ እናንተም ስለ አስቴር አስቡ። ምን ያህል አገሯን እንደምትወድ እሷን ትታችሁ እንጉርጉሮዋን አድምጡ። አስቴር ገንዘብ ትፈልጋለች፣ በጣም ነው የሚያስፈልጋት በአሁኑ ሰዓት አንድ የአንገት ሀብል $75,000 ዶላር በገባበት ሰዓት $20,000 ዶላር ብቻ በአንድ ምሽት በምታገኝበት ምሽት ላይ በነፃ ለእኛ ተጫወቺ አንቺ ካሳየሽ ሰው ወደ አንቺ ግልብጥ ብሎ ወደ አንቺ ነው የሚመጣው ብሎ ነገር አለ! ይሄ እኮ ቢዝነስ ነው ሆሆ!! አለች አስቴ ይቅርታ ወይዘሮ አስቴ።

ወ/ሮ አስቴር ብሪቱ የሚለው የንዋይን ዘፈን ለየት ባለ መልኩ አቀነባብራ ሳታቀርበው የቀረች እንደሆነ ኑር ሁሴን ምናለ በሉኝ። እስኪ ለማንኛውም ተወያዩበት። እኔ እንደሆን አስቴርን ሳውቃት አገሯን ትወዳለች ለስፖንሰሮቿም ያልኩት ቢኖረኝ «ራስሽን ምሰይ ወይም ሁኚ» በሏት ነው።

በሉ እንግዲህ በዚህ ይብቃኝ የሚቀር ካለ በሚቀጥለው እትም እመለስበታለሁ።

የናንተው ኑር ሁሴን (ዳላስ — ቴክሳስ)

# ከዜና ማኅደር

# እንዲህ ሆነ!

ውድ አንባብያን፤ የዜና ማህደር አቀራረባችንን በተመለከተ አንዳንድ ያደረግነው ለውጥ አለ። ያለነው ወጭ አገር በመሆኑና ድርጊቶች በሚከናወኑበት አካባቢዎች ባለመኖራችን የምናቀርባቸው ዜናዎች ከሌሎች የዜና ምንጮችና ጋዜጦች እያጠናቀርን መሆኑን እየገለጽን ዜናዎቹን ያገኘንባቸውን ምንጮች ከዜና ርዕሶቹ አጠገብ አስቀምጠናል። በሌላ በኩል ደግሞ መጽሔታችን የምትዘጋጀው በየሁለት ወሩ በመሆኑ በአብዛኛው የምናተኩርባቸው ዜናዎች መጽሔቷ በምትወጣበት አካባቢ ያሉትን እንደሆነ ለመግለጽ እንወዳለን። ስለአቀራረባችን የተሻለ አስተያየት ልትሰጡን የምትፈልጉ እባካችሁ አነጋግሩን።

## የተቃዋሚዎች ጉባዔ ፓሪስ ሊካሄድ ነው።

(ጦቢያ ጋዜጣ)

የኢትዮጵያ ሉአላዊነት በሻዕቢያ በተደፈረበትና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችም ውስብስብ በሆኑበት በአሁኑ ወቅት ስለአገሪቱ ሁኔታ ለመወያየት ታዋቂ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ፓሪስ ከተማ መስከረም 1 ቀን 1991 ዓ.ም ጉባዔ ይቀመጣሉ። በዚሁ ጉባዔ በ1985 ዓ.ም በፓሪስ የተሰባሰቡት ሰባት የፖለቲካ ድርጅቶችና በአሁኑ ጊዜ ጉልህ ሚና ያላቸው፣ በውጭ የሚገኙና በአገር ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎች የሚሳተፉ ሲሆን መወያያ አጀንዳቸውም በአገሪቱ የተጨናገፈው የዴሞክራሲያዊ ሂደት እንዲስተካከል፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች የጋራ ኅብረት ስለሚጠናከርበትና የአገሪቱ ሉአላዊነት መደፈርን በተመለከተ አንድ አቋም ላይ ለመድረስ በሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ እንደሆነ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ለማወቅ ተችሏል።

አገር ውስጥ ከሚንቀሳቀሱት የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት፣ የደቡብ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረትና የመላ አማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐድ) በጉባኤው የሚገኙ ሲሆን በ1985 ዓ.ም። በፓሪሱ ጉባዔ ተሳታፊ የነበረውና አሁን በውስጡ ባለው መከፋፈል ችግር ላይ የወደቀው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) የተጋበዘ ቢሆንም በጉባዔው ላይ ስለመሳተፉ እስከአሁን መልስ እንዳልሰጠ ይነገራል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ዋና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማግለል የሽግግሩን መንግሥት ሥልጣን ለብቻው በጠቀለለበት ወቅት ፓሪስ ላይ የተሰባሰቡት ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ ያለው የዴሞክራሲ ሁኔታ አደጋ ላይ እንደሆነ ጠቁመው ኢህአዴግን ጨምሮ ሁሉም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና ታዋቂ የአገር ሽማግሌዎች የሚሳተፉበት የሰላምና የእርቅ ጉባዔ በአዲስ አበባ ውስጥ እንዲካሄድ ወስነው ነበር።

የፓሪሱን ጉባዔና የተላለፈውንም ውሳኔ አጥብቆ የኮነነው የኢህአዴግ መንግሥት ለስሙ ትንሽ መቀመጫ ሰጥቷቸው የነበሩትን በጉባዔው የተካፈሉትን የደቡብ ኅብረት አባላት ጉባዔውን ካላወገዛችሁ ብሎ ከተወካዮች ምክር ቤት ማባረሩ ይታወሳል። በዚህም ምክንያት 1. የወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ዊዴግ) 2. የሃድያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት 3. የከምባታ ሕዝቦች ኮንግሬስ ) 4. የጌዴኦ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት 6. የጉራጌ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር 7. የከፋ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት እና 8. የአም ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግንባር ጉባዔውን እናወግዝም ብለው ከምክር ቤቱ ሲወጡ በዚህ የተደናገጠው ኢህአዴግ ከወላይታ አቶ ወልደሚካኤልን፣ ከከምባታ አቶ ተስፋዬ ሀቢሶን፣ ከየም አቶ ኃይለየሱስ ሉሬን፣ ከጉራጌ ዶ/ር ኃይሌ ወልደሚካኤለንና ዶ/ር ፈቃደ ገዳሙን፣ ከከፋ ፊታውራሪ ዘውዴ አቶሮን ከድርጅቶቻቸው ነጥሎ በማስቀረት በሽግግሩ ወቅት እንዲያጅቡት አድርጓል።

በፓሪሱ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት ከታህሣሥ 9 – 13/ 1986 ዓ.ም. በግዮን ሆቴል የተጠራውን የሰላምና እርቅ በኢትዮጵያዉ አገር አቀፍ ጉባዔ ለማስቀረት የተንቀሳቀሰው ኢአዴግ ዲፕሎማሲያዊ ግፊቱ በማየሉ ባይሳካለትም በውጭ የሚገኙ ተቃዋሚዎች በስብሰባው እንዳይገኙ አገር ውስጥ የገቡ አባላትንም ከቦሌ እየተቀበለ ማሰር በመጀመሩ በኢዲኃቅ ዙሪያ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና ኦነግ ሳይከፈሉ ቀርተው ችግሩን በሰላም ለመፍታት የነበረውን ተስፋ አጨልሞታል። በጊዜው ከታሰሩት የተቃዋሚ ድርጅት አባላት አቶ አበራ የማነአብ አሁንም በእስር እየማቀቁ ናቸው።

እንቅፋት ቢፈጠርም ጉባዔው አገር ውስጥ ባሉ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ተቋማት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የአገር ሽማግሌዎች ተሳትፎ ሽግግሩና ዴሞክራሲያዊ ሂደቱ፣ የሽግግሩ ወቅት የኢኮኖሚና ማኀበራዊ ጉዳዮች፣ የብሔሮች መብትና የኢትዮጵያ አንድነት ልዕልና ጉዳይ፣ ሽግግሩና ሜገ መንግሥታዊ ጥያቄ እንዲሁም የሰላምና ዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች የትግል ትብብር ጥያቄ በሚሉ ርዕሶች በመወያየት ጠቃሚ ውሳኔዎችን አሳልፎ ተጠናቋል።

የዚህ ጉባዔ ውጤት የሆነው የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትም ታህሣሥ 21 ቀን 1986 ዓ.ም. 35 አባል ድርጅቶችን በመያዝ ሊመሰረት ችሏል። ምክር ቤቱ የአገሪቱን ችግር በሰላም ለመፍታት በርካታ ተቃዋሚዎችን በአንድ ጥላ በማሰባሰብ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል የሚል በሕዝብ ዘንድ የማይናቅ ተስፋ ተጥሎበት የነበረ ቢሆንም በኢህአዴግ መንግሥት ጫናና በተለይ ደግሞ በውጪና በአገር ውስጥ ባሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች ድክመት ምክንያት የታሰበውን ያህል ሊጎለብት እንዳልቻለ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

የታህሣሡን ጉባዔ ለማሳካትና ምክር ቤቱን ለማቋቋም ጠንካራ ጥረት ያደረጉት በውጭና በአገር ውስጥ ያሉ ድርጅቶች መደገፉን በማቆም እንዲያውም አትላንታና ዋሽንግተን ተዘጋጅተው ከኢአዴግ ጋር በተሞከሩ ድርድሮች እንዲሁም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ጠንካራ የጋራ አቋም ሳይይዙ በየፊናቸው መቅረብና እርስ በርስ ለመጠላለፍ መሞከራቸው ብዙውን አገር ወዳድ አሳዝና ቆይቷል የአሁኑ ጉባዔ የተቃዋሚ ኃይሎችን ኅብረት አንድ እርምጃ ወደፊት ያራምዳል ተብሎ ይጠበቃል። ምክር ቤቱ ውስጥ የነበሩ አንዳንድ የተቃዋሚ ድርጅቶች አባላትና ማኅበራትም ምክር ቤቱን ውስጡ ሆኖ ታግሎ ማጠናከሩን በመተው የተሻለ አማራጭ ሳያቀርቡ በሰበብ አስባብ ራሳቸውን ሲያገሉ ቀሪዎቹም ተጠናክሮ ለመውጣት ያደረጉት ጥረት የጎላ አለመሆኑን ታዛቢዎቹ ይናገራሉ።

የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት አለመጠናከርን ምክንያት የፖለቲካ ታዛቢዎች በሁለት ከፍለው ያዩአቸዋል። የመጀመሪያው ራሳቸውን አንጋፋ አድርገው የሚቆጥሩ የአገር ውስጥና የውጭ የፖለቲካ ድርጅቶች ራሳቸው ሙሉ በሙሉ በማይቆጣጠሩት መድረክ ማንነታቸው ተውጦ እንዳይቀር በመስጋት ለእውቅናቸው ብቻ መታገላቸውንና ተዘዋዋሪ እንቅፋት ሲፈጥሩ መቆየታቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ የምክር ቤቱ አመራር ገንቢ የሆኑ ኃሳቦችን እያቀረበ በግንባር ቀደምትነት ከመታገል ተቆጥቦ ኢአዴግን የማያስቆጣ ዲዝብንም ስሜት በግልፅ የማይጎዳ ለስላሳና አዘናጊ መንገድ እየመረጠ ማዝገሙ ዋናው ምክንያት ነው ይላሉ።

በመስከረም መጀመሪያ ፓሪስ ሊካሄድ የታቀደው ጉባዔ ባለፉት ዓመታት በተቃዋሚዎች ዘንድ በታዩት ድክመቶች ላይ በግልፅ ተነጋግሮ ሕዝቡ ደጋግሞ ላቀረበው የተጠናከረ ግንባር ጥያቄ ተገቢ መልስ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል።

## ኤርትራ 385 ሚሊዮን ዶላር ሰበሰበች ይባላል

(ጦቢያ ጋዜጣ)

ኤርትራ በኢትዮጵያ ላይ የከፈተችው ወረራና የገንዘብ ለውጥ ባስከተለባት ከባድ ቀውስ፣ ከኢትዮጵያ ወስዳ ለዓለም የምታቀርበው የቡናና የሌጦ ምንጭ በመድረቁ፣ ለዕለት ጉርስና ማጣፈጫ ከኢትዮጵያ የሚጫነው እህልና ቅመማ ቅመም በመቋረጡ፣ ከኢትዮጵያ አየር መንገድና ከአሰብ ወደብ ታገኝ የነበረው ገቢ በመቅረቱና ሌሎችም አያሌ የገቢ መንገዶች በመዘጋታቸው በትልቅ የኢኮኖሚ መናጋት ውስጥ የምትገኘው ኤርትራ በውጭ የሚገኙ ግለሰብ ኤርትራውያን በሚያዋጡት ገንዘብ በጀትዋን ለማስተካከል መገደድዋን ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ኤክስፐርቶች አረጋገጡ።

በኤክስፐርቶቹ አመለካከትና ይልቁንም በቅርቡ በተደረጉ ተከታታይ የኤርትራውያን እንቅስቃሴዎች መሠረት በአሜሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅና በአውሮፓ የሚገኙት ኤርትራውያን የጦርነት ወረፋ ከተሰማ ወዲህ ብቻ ሦስት ሦስት ጊዜ የገንዘብ መዋጮ ማድረጋቸው ተረጋግጦአል።

ዜናውን በተከታተሉ ወገኖች መረጃ መሠረት በዋሽንግተን፣ በቦስተን፣ በሒዩስተን፣ በሎስ አንጀለስና በኒውዮርክ የሚገኙ ኤርትራውያን ብቻ ሁለትና ሦስት ጊዜ ያዋጡት ገንዘብ ከ200 ሚሊዮን ዶላር በላይ ደርሷል ይባላ። እንደዚሁም ከመካከለኛው ምሥራቅ ብቻ ተጠብቆ የነበረው 150 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን መዋጮው የሞትና የሽረት ጥያቄ ነዉ ተብሎ በመነገሩ 385 ሚሊዮን ዶላር እስካሁን መሰብሰቡ ይነገራል።

## ኤርትራ ወጣቶቿ ሽሽት ይዘዋል

(ጦቢያ ጋዜጣ)

ለሀገር ደህንነት አስጊ በመሆናቸው በቁጥጥር ስር ውለው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የተወሰነባቸው ኤርትራውያን ወጣቶች ወደሀገራቸው ለመመለስ እንደማይፈልጉ ታውቋል። ወጣቶቹ ወደ ሀገራቸው መመለስ የማይፈልጉት የሻዕቢያ መንግሥት መልሶ ወደ ጦርነት እንዳይማግዳቸውና በሥራ እጥነት እንዳይቸገሩ በመስጋት እንደሆነ ተደርሶበታል።

ስለጉዳዩ በተደረገው ክትትል አብዛኛዎቹ ወጣቶች ወደ ኤርትራ ላለመመለስ የወሰኑት ቀደም ሲል አሥመራ የገቡት ዜጎች እዚህ ለቀሩት ዜጎቻቸው ባስተላለፉት የስልክ መልዕክት መሠረት ነው። የቀሩት ደግሞ ቀድሞውኑ የሀገሪቱ ኢኮኖሚና ፖለቲካ ሁኔታ ተስፋ አስቆርጦአቸው ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በአዲስ አበባ፣ በፍቼና በብላቴን በቁጥጥር ስር ያዋላቸው እነዚህ የኤርትራ ወጣቶች የሻዕቢያ ሠራዊት አባላት የነበሩ፣ በሳዋ የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ሥልጠና የወሰዱና የሻዕቢያ ስለላ ድርጅት አባላት የነበሩ መሆናቸው ተደርሶበታል። ወጣቶቹ ከኤርትራ ይልቅ ወደ ሌሎች ሀገሮች መሄድ እንደሚፈልጉም ታውቋል።

## ከኢትዮጵያ 17000 ኤርትራውያን እስካሁን ወጥተዋል።

(ጦቢያ ጋዜጣ)

እስካሁን ድረስ ከሀገር እንዲወጡ የተደረጉት ኤርትራውያን ብዛት 17ሺህ እንደደረሰ ተዘግቧል። የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያና በኤርትራ ግጭት ሲቪሎች ሰለባ መሆናቸውን እየገለፀ ከኤርትራ ስለሚባረሩት ኢትዮጵያውያን ምንም ሳይል በኢትዮጵያ በኩል የሚወሰደው እርምጃ አሳስቦኛል ብሏል። የአሜሪካ መንግሥት ስጋቱን በአሜሪካ ራዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም አማካይነት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሁለቴ ያስታወቀ ሲሆን ሁለተኛው ባለፈው ነሐሴ 11 ቀን 1990 ዓ.ም ተደምጧል።

የአሜሪካ መንግሥት የኤርትራና የኢትዮጵያ ግጭት የአፍሪካ ቀንድንና የምሥራቅ አፍሪካን ሰላም እንደማያናጋ አመልክቶ የኤርትራውያን ከኢትዮጵያ መባረር ገደብ የጣሰና ቤተሰብን የበታተነ እርምጃ ነው በማለት አጣጥሎታል። በመቀጠልም ከሀገር ለተባረሩት ኤርትራውያን ካሣ እንዲከፈል፣ የተበታተኑ ቤተሰቦች የሚዋሃዱበት መንገድ እንዲቀየስ ጠይቋል። ከትምህርት ቤቶች ተወስደው የታሠሩትም መፈታት እንዳለባቸው አሳስቧል።

ይሁን እንጂ ይህ የአሜሪካ አቋም ብዙዎቹን አስገርሟል። ለነዑሃን ዜጎች ከብካቤ የማድረጉ አስፈላጊነት አጠያያቂ ባይሆንም ከ1983 ጀምሮ ግፍ እየተፈፀመባቸው ከኤርትራ ሲባረሩ ስለቆዩት፣ ዛሬም በኤርትራ ስለሚረሸኑትና የቁም ስቃይ በማየት ላይ ስለሚገኙት ኢትዮጵያውያን ምንም ሳይል ከኢትዮጵያ ስለሚባረሩት የሻዕቢያ ወኪሎች መቆርቆሩ ሚዛናዊነት ያጣ ስጋት አሰኝቷል።

ይህ በዚህ እንዳለ በፀጥታ ኃይሎች ያልተያዙና ከሀገር መውጣቱ ጨርሶ የማይመለከታቸው ኤርትራውያን በስጋት ብቻ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ከሀገር በመውጣት ላይ ናቸው። እነዚህም ዜጎች ወደ ምሥራቅ አፍሪካ፣ መካከለኛው ምሥራቅ፣ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ እንደሚሄዱ ለመረዳት ተችሏል።

በቦሌ በኩል እየወጡ ያሉት ኤርትራውያን በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ሶስት ቦታ የሚመደቡ ናቸው። እነዚህም ከሀገር እንዲወጡ ሳይጠየቁ ፍርሃት ያደረባቸው፣ የቤተሰቦቻቸው አባላት ከሀገር የተባረሩባቸው እና የኋላ ኋላ መባረሩ የማይቀርላቸው ግለሰቦች ናቸው።

ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሆኑት አንዳንድ ኤምባሲዎች ወደሀገሮቻቸው የሚያስገባ ቪዛ የሚሰጡት ኑበሰብአዊ አመለካከትዉ ሽፋን እንደሆነም ታውቋል። በዚህ መልክ እስከ አሁን ከሀገር የወጡት ኤርትራውያን ብዛት ባይታወቅም ቁጥሩ አነስተኛ እንዳልሆነ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል። በሌላም በኩል ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ከተደረጉት ኤርትራውያን ጋር ግንኙነቶች የነበሯቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ኪሣራ እየደረሰባቸው መሆኑ ታውቋል።

የኪሣራው ሰለባ ከሆኑት ተቋሞች መካከል ኤርትራውያን አስቀድመው የበሉባቸው ወይም ተጠቃሚ የሆኑባቸው ዕቁቦች የሚገኙ ሲሆን ጉዳዩ

በቀሪ አባላት ላይ ድንጋጤን እንደፈጠረ ለማወቅ ተችሏል። ሌሎች የችግሩ ገፈት ቀማሾች ደግሞ ለኤርትራውያን ብድር የሰጡ ድርጅቶችና ግለሰቦች ናቸው። ከእነዚህም መካከል ባንኮች እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። እንደዚሁም ለኤርትራውያን ዕቃ በዱቤ የሸጡና ቤት አከራይተው ኪራዩን አስቀድመው ያልተቀበሉ ኢትዮጵያውያንም ጉዳት ደርሶባቸዋል። እነዚህ ከሀገር በወጡት ኤርትራውያን ባለዕዳ የሆኑት ኢትዮጵያውያን ጉዳዩ የሚመለከቸውን ኤርትራውያን ንብረቶች በፍ/ቤት ለማስከበር እንቅስቃሴ ጀምረዋል። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለኤርትራውያን የሰጠው ብድር ካልተመለሰለት የተበዳሪዎቹን ንብረት በሀራጅ እንደሚሸጥ አስታውቋል። የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኮርፖሬሽን ደግሞ ለጥገና የሰጣቸውን ተሽከርካሪዎች ከኤርትራውያን ጋራዦች ሰብስቦ ወስዷል።

## የኢመማ ጽ/ቤት ታሸገ

(ጦቢያ ጋዜጣ)

አንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር (ኢመማ) የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዘናል በሚሉ ፖሊሶች ነሐሴ 7 ቀን 1990 ዓ.ም መታሸጉን የተለያዩ የግል ጋዜጦች ዘገቡ። በተለይ ነሐሴ 10 ቀን 1990 ዓ.ም ታትሞ በወጣው ኢትዮ – ታይም የግል ጋዜጣ ላይ እንደተገለጸው ማኅበሩ በይግባኝ የያዘው ክርክር ውሳኔ ሳይሰጥበት በአንድ የኢህአዴግ ካድሬ የተመራና በ10 ፖሊሶች የታገዘ ኃይል ጽ/ቤቱን አሽጓል።

ጋዜጣው የማኅበሩን አመራር አባላት ጠቅሶ እንደዘገበው የማኅበሩ አመራሮች እኛ ነን የሚሉት ወገኖች ሐምሌ 19 ቀን 1990 የይግባኛል ጥያቄ በማመልከቻ ማቅረባቸውንና ፍርድ ቤቱም ሐምሌ 28 ቀን 1990 ዓ.ም በዋለው ችሎት ኑንብረቱ እንዲታገድና ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍዉ ትዕዛዝ ሰጥቶአል። የዚህ ትዕዛዝ ግልባጭ ለሚመለከተው ሁሉ እንዲደርስ ብለናል ሲል ትእዛዝ ሰጥቷል ቢባልም ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ የሰጠበት ግልባጭ ለአንጋፋው ኢመማ ጽ/ቤት አለመድረሱ ተብራርቷል።

እነዚህ ወገኖች ነሐሴ 7 ቀን 1990 ዓ.ም ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠበትን ደብዳቤ ይዘው ንብረቱን እንዲያስረክቡ የማኅበሩን አመራር አባላት ጠይቀዋል። የማኅበሩ አመራር አባላት ደግሞ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለእኛ አልደረሰም። ይህ ትዕዛዝ እስኪመጣ ድረስ ንብረት አናስረክብም ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል። በዚህ ጊዜ የተለጣፊው ማኅበር አመራር አባል የሆኑ አንድ ግለሰብ ባሉበት የወረዳ 3 ቀበሌ 53 መስተዳድር አባላትና በግምት ከአሥር በላይ የሆኑ ፖሊሶች በተገኙበት በቀበሌው መስተዳድር ማኅተም ጽ/ቤቱ መታሸጉን ኢትዮ – ታይም ጋዜጣ አስረድቷል።

የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር እና አመራሩ ይገባኛል በሚለው ተለጣፊ ወገን መካከል ጉዳዩ ተይዞ ክርክር ላይ ይገኛል። ጉዳዩን የያዘው ጠቅላይ ፍ/ቤት በተለጣፊው ወገን የቀረበለትን የይግባኝ ጥያቄ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት ለመጋቢት 19 ቀን 1991 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል።

## የ1991 በጀት ከ11 ቢሊዮን ብር በላይ ሆነ

የኢህአዴግ መንግሥት የ1991 በጀት ከ11 ቢሊዮን በላይ ሆነ። ከዚህም ውስጥ 4.1 ቢሊዮን ያህል ለመደበኛ 2.9 ቢሊዮን ያህል ብር ለካፒታል፣ 4.1 ቢሊዮን ያህል ብር ደግሞ ለክልሎች መደጐሚያ እንደሚውል ተጠቁሟል። የፌዴራል ካፒታል በጀት ድልድሉም 49.8% ለመንገድ፣ 6.9% ለትምህርት፣ 10.1% ለግብርና፣ 13.7% ለትራንስፖርትና መገናኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ አሀዞች ከድጐማ በስተቀር የክልል መንግሥታትን በጀቶች እንደማይጨምሩ ተጠቁሟል። በዚህም መሠረት የ1991 የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በጀት 1.4 ቢሊዮን ያህል ብር፣ የአማራ ክልላዊ መንግሥት ደግሞ 1.3 ቢሊዮን ያህል ብር፣ የደርግ ዘመን ከፍተኛው ዓመታዊ በጀት ወደ 3.5 ቢሊዮን ብር ገደማ እንደነበር ይታወሳል።

## ከፍተኛ የኢትዮጵያ ንብረት በአሰብና በምፅዋ ታግቷል

በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል በተነሳው ግጭት ሰበብ 135 000 ቶን ደረቅ ጭነት፣ 46,741 ሜትሪክ ኪዩብ ፈሳሽ ጭነት፣ 53,000 ሜትሪክ ቶን አስፋልት በአሰብና ምፅዋ ወደቦች ታግተዋል። ከዚህ ውስጥ ከፍተኛ የዕርዳታ እህል ክምችት እንደሚገኝበትና ይህንንም ሻዕቢያ ለሠራዊቱና ሲዝቡ ሳያውለው እንዳልቀረ ይነገራል። የአንዳንድ ድርጅቶችም ኪሣራ እንደሚከተለው መሆኑን የገዢው ፓርቲ ልሣን የሆነው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ገልጿል።

## ዜጎችን የማባረሩ ዘመቻ ቀጥሏል

የሻዕቢያ መንግሥት ኢትዮጵያውያንን ከኤርትራ የማበረሩን ዘመቻ እየገፋበት ነው። በዘመቻው የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ከኤርትራ እንዲወጡ ይደረግ የነበረው በዛላ አንበሣ በኩል ሲሆን ዛሬ ግን የመውጫ ኬላዎቹ ቡሬና ጂቡቲ ሆነዋል። በሁለቱ ሀገሮች መካከል ግጭት ከተጀመረ አንስቶ እስካሁን ባለው ጊዜ ወደ 5000 ኢትዮጵያውያን ንብረታቸውን እየተቀሙ፣ ሴቶች ደግሞ እየተደፈሩ ከኤርትራ ተባረዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥትም ተመሣሣይ ዕርምጃ ሲወስድ ሰንብቷል። በዚህም መሠረት ከ6000 የማያንሱ የሻዕቢያ ሠራዊት አባላት፣ ሰላዮችና የጦርነት ደጓሚዎች ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በቁጥጥር ሥር ውለዋል። የፅዳት ዘመቻው ዒላማ የሆኑት የመጀመሪያዎቹ ኤርትራውያን ከሀገር የተባረሩት በዛላ አንበሣ በኩል እንደነበር ሲታወስ ከጊዜ በኋላ ግን ሁመራና ቡሬ ተጨማሪ የመውጫ ኬላዎች እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል።

## የኤርትራ ዓመታዊ ገቢ ግማሽ ምንጭ ኢትዮጵያ ነበረች

ባለፉት ሰባት ዓመታት የኤርትራ ዓመታዊ ገቢ ግማሽ ምንጭ ኢትዮጵያ እንደነበረች ተገለፀ። ይህም ሊሆን የቻለው ኤርትራ ምርቶችዋን እንደልብ ወደ ኢትዮጵያ እንድትልክ አመቺ ሁኔታ በመፈጠሩና ለአሰብ አገልግሎት በዓመት አንድ ቢሊዮን ብር ያህል ሲከፈላት በመቆየቱ እንደሆነ ውስጠ ዐዋቂዎች አመልክተዋል። እነዚሁ ምንጮች እንደገለፁት 10% የሚሆነው የኢትዮጵያ ወጪ ንግድ ይሄድ የነበረው ወደ ኤርትራ ሲሆን አብዛኛው የእርሻ ምርት እንደነበር ታውቋል።

## 2500 የጭነት መኪናዎች በጅቡቲ መስመር ተሰማርተዋል

ከ30 በላይ የሚሆኑ ድርጅቶች 2500 ያህል ከባድ የጭነት መኪናዎችን በጂቡቲ መስመር አሠማርተዋል። የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የመሸከም አቅም ከ220 እስከ 400 ኩንታል እንደሚደርስ ታውቋል። በዚህ ተግባር ላይ ለሚሠማሩ 550 አሽከርካሪዎችና 360 ረዳቶች የጂቡቲ መግቢያ ፈቃድ ተሰጥቶአቸዋል። ኢትዮጵያ በአሰብና በምፅዋ ወደቦች መጠቀሟን ያቆመችው በሚያዝያ ወር/90 ሲሆን በጂቡቲ ወደብ መጠቀሙ በብዙ መልኩ እንደሚመረጥ ታውቋል።

## <u>በደቡብ ኢትዮጵያ በተነሣ የጐሣ ግጭት ብዙ ሕዝብ አለቀ። መንግሥት ጸጥ ብሏል።</u>

በሐምሌ ወር አጋማሽ በ1990 ዓ.ም. በጌዴኦና በጉጂ ብሔረሰቦች መካከል በተነሳው ግጭት ከሁለቱም ብሔረሰቦች ከ2500 እስከ 3000 የሚደርስ ሰው ሞቶ፤ በርካታ ንብረት ከመውደሙም በላይ በአስርሺዎች የሚገመት ሕዝብ መፈናቀሉን የጦቢያ ጋዜጣ ባልደረባ በየቦታዎቹ ተዘዋውሮ የአደጋውን ሰለባዎች በማነጋገር አረጋግጧል።

ኤላፈርዳ፣ ዲቢሣ፣ ቂሌንሶ፣ ሶኬ፤ ጋሊስና ሌሎችም ቦታዎች ላይ ከሚገኙት መኖሪያዎች ተፈናቅለው በአሁኑ ጊዜ በዲላ፤ በጭጩ፤ በወናጎ፣ በይርጋጨፌ፣ በፍስሐ ገነትና በገደብ ከተሞች በድንኳን፣ በትምህርት ቤቶች፣ በቀበሌ አዳራሾች፣ በሐዋዕለ ሕፃናትና በየዘመዶቻቸው ተጠልለው የሚገኙ ተፈናቃዮች ከ75,000 በላይ እንደሚሆኑ በነዚህ ሥፍራዎች ሪፖርተሩ ያነጋገራቸው አረጋውያን ገልጠዋል።

ከኋላው ያለውን የፀቡን መንሥኤ በትክክል ለማወቅ ባይቻልም ጌዴኦዎች ይዘን የምንጠቀምበት መሬት የኛ ነው፣ እስካሁን ግብር ለክልል 4 መክፈላችን መቅረት አለበት ሲሉ ጉጂዎች ደግሞ በነዚህ ቦታዎች መጥታችሁ የሰፈራችሁት የዛሬ 38 ዓመት በመሆኑ መሬቱ የጉጂ ነው። ወደ ጌዴኦ ዞን (ወደ ክልል) ልትወስዱብን አይገባም በሚል ንትርክ ላይ ባሉበት ወቅት በጌዴኦ ዞን ስር የሚገኘው የይርጋጨፌ ወረዳ አስተዳደር የፍትሕ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አወል ሀሰን ኤላ ፈርዳ ላይ ሲደርሱ ፀብ ተነስቶ በገጀራ (ጎራዴ) ተጨፍጭፈው ሕይወታቸው ማለፉ ለፀቡ መጀመር ሰበብ መሆኑን በዲላ ከተማ ያሉ ተፈናቃዮች አስረድተዋል።

የወረዳ አስተዳዳሪው አስከሬን ወደ ዲላ ሆስፒታል ተልኮ ምርመራ ከተደረገ በኋላ ይርጋጨፌ ከተማ ወደሚገኙት ቤተሰቦቻቸው ተመልሶ እስከተቀበረበት ድረስ መንግሥት አፋጣኝ እርምጃ ባለመውሰዱ አደጋው በሌሎች ከተሞችና በገጠሮችም ተስፋፍቶ በአሰቃቂ ሁኔታ የጠፋው የሰው ህይወት በጣም ብዙ ከመሆኑም በላይ ቀሪዎቹ ከልጅነት እስከ እውቀት ያለው ንብረታቸው ወድሞ በአሁኑ ጊዜ በሰው እጅ ገብተው መረዳታቸው ከሞት ያላነሰ ጉዳት መሆኑን በምሬት ገልፀዋል።

አመጸና የተኩስ ልውውጡ የጀመረበት የኤላፈርዳ ከተማ ነዋሪዎች በከተማዋ የሚገኘውን በርካታ ሸቀጣ ሸቀጥ፣ ቡና ቤቶች፤ አልቤርጎዎችና ንብረት ከዘረፋ ለማስጣል በርትተው ቢታኮሱም የሚደርስላቸው አጥተው በ3ኛው ቀን ወደ ኋላ ሲያፈገፍጉ ከዘረፋው በተጨማሪ መተራረዱ በስፋው መቀጠሉን ከሞት አምልጠው ወደ ዲላ የሸሹት ሰዎች አረጋግጠዋል።

የጌዴኦ ሰዎች በነዚህ አካባቢዎች ከሠሩአቸው በርካታ የቆርቆሮ ቤቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ፈራርሰው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል። ሌሎችም ተነቃቅለው ተወስደዋል። ሣር ቤቶች በሙሉ ተቃጥለዋል። ሸቀጣ ሸቀጦች በሙሉ ተዘርፈዋል። ሕፃናት፣ ነፍሰጡሮች፣ ሽማግሌዎችና ጎልማሶች በጦር፣ በስለት፣ በጥይት እየታረዱና እየተመቱ ማለቃቸውን በሕይወት የተረፉት በብርቱ ኃዘን ይናገራሉ። መንግሥት ሊታደጋቸው ባለመቻሉም አጥብቀውም ያማርራሉ። በዚህ የጅምላ ጭፍጨፋ ከ2,500 – 3,000 ሰዎች አልቀዋል የሚለው ክፍል ቢበዛም ከ4,500 – 5,500 ሞቶአል የሚሉም ጥቂቶች አይደሉም። ከሁሉም በላይ ይህ እልቂት ሲፈፀም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት እንዲረዳን የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ዝምታን መምረጣቸው አሳዝኖናል የሚሉትም ብዙዎች ናቸው። ቤቱን እየተወ የተሰደደውን ሕዝብ ሕይወት ሊማዳን የይርጋጨፌ ወረዳ አስተዳዳሪና የጌዴኦ ዞን ያገኙትን የጭነትም ሆነ የሕዝብ ማመላለሻ መኪናዎች እያስገደዱና ሌላውንም በማስተባበር እያሠማሩ ሕዝቡን ከአካባቢው እንዲነሳ ባያደርጉት ኖሮ የሚደርሰው ጉዳት ከዚህ እጥፍ ይሆን እንደነበር የዓይን ምስክሮች ይናገራሉ። በአሁኑ ጊዜ በዲላ፣ በጭጩ፤ በወናጎ፤ በይርጋጨፌ፤ በፍስሐ ገነትና በገደብ ለሚገኙት ተፈናቃዮች የየከተማው ሕዝብ ምግብ በማቅረብ፣ ልብስ በመለገስ የተቻለውን እርዳታ በማድረግ ላይ ቢሆንም ሽማግሌዎች፣ ሕፃናት፣ ነፍሰጡሮች በሌሎችም የእድሜ ክልሎች የሚገኙ ሁሉ ከአሁኑ የተሻለ እርዳታ ከአልተደረገላቸው በክረምቱ ብርድና በልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታ ሊጎዱ ይችላሉ የሚሉ ሰዎች አጋጥመውኛል። የመታከሚያ ቦታ በማጣት በየዘመዶቻቸው ተጠግተው የሚገኙ ቁስለኞች

ቁጥራቸው ቀላል አለመሆኑን ይርጋጨፌ ከተማ ውስጥ በዘመዱ ቤት ተኝቶ በመረዳት ላይ ያለ ጎልማሳ አስረድቶአል።

የጉጂ ብሔረሰብ አባላት ሰው እየገደሉ፣ ቤት እያቃጠሉ ሲደርሱብኝ ሸሽቼ ለማምለጥ ስሞክር በጦር ተወጋሁ። ደሜን እያዘራሁ ሮጬ ሚይወቴን አተረፍኩ። ባለቤቴና 7 ልጆቼ የት እንደደረሱ እስካሁን የሰማሁት ነገር የለምዉ ሲል አንዱ ቁስለኛ ገልጿል። ሌላውም ቁስለኛ አንዷ ልጄ በጥይት ታፋዋን ተመትታ ዲላ ሆስፒታል መጥተን ጥይቱን በኦፕራሲዮን አወጡላት። እኔ በተአምር ብተርፍም ሌሎች ቤተሰቦቼን እስካሁን አላገኘኋቸውምዉ ብሏል ምርር ብሎ እያለቀሰ። ይርጋጨፌ ከተማ ውስጥ በይርጋጨፌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በሐምሌ 19 አዳራሽ፣ በቀበሌ 02 አዳራሽና በይርጋጨፌ ከተማ መዋዕለ ሕፃናት ውስጥ ያሉትን ለቁጥር የሚያታክቱ ተፈናቃዮች ከማየቴም በላይ ያሉበት ሁኔታ ግን የሚያሳስብ መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ። ሐምሌ 19 አዳራሽ ለመግባት ሞክሬ ተከልክያለሁ። በይርጋጨፌ መጠለያዎችና በአካባቢው እስከ 30,000 ተፈናቃዮች ይገኛሉ ይባላል።

ሰው ወስዶ ያገናኘኝ ይርጋጨፌ ከተማ ውስጥ ቆስሉ የተኛ አንድ ጎልማሳ ሲናገር ኑመቼም በጌዴኦ ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር መዓት ነው ያወረደበት። በኤላፈርዳ ከተማ በነበሩት ትላልቅ ሱቆቻችን ውስጥ እጅግ በርካታ ሸቀጥ፣ እንዲሁም ጥሬ ገንዘብ ነበረን። የቡና መፈልፈያ ማቢያዎች ሣይቀሩ ወደሙ። ያሸተ ቡናችን በገጀራ ተጨፈጨፈ። እንስታችን፣ አትክልታችን ተመነጠረ። ከልጅነት እስከ እውቀት ያፈራነው ንብረታችን ተዘረፈ። ያለቀው ሚዝብ ልክ የለውም። አባቴ፣ እናቴ፣ ወንድሜ ከፊቴ ሲታረዱ ለመከላከል ሲሞክር ከኋላዬ በገጀራ ተመታሁ። ከዚያ በምችለው ዓቅሜ ሮጬ አመለጥኩ። ማካ አድሬ በማግሥቱ ከሰው ተደባልቄ ወደዘመድ ቤት አመጡኝዉ ብሏል።

## በኤርትራ ኤምባሲዎች አማካይነት የብር ሽያጭ ገበያ ጦፎአል

በዋሽንግተን ዲሲና በኒውዮርክ የሚገኙት የኤርትራ ዲፕሎማቶች በደላሎችና በመሳሰሉት ግለሰቦች አማካይነት ትልቅ የገንዘብ ለውጥ ገበያ እያጧጧፉ መሆኑ ታውቋል።

ከዚህ ቀደምም ዶላር በኤምባሲው በኩል እየተወሰደ በሰባት ብር ሂሳብ አዲስ አበባ ላይ ለተወሰነው ተቀባይ ይሰጥ እንደነበረ ሲገለጥ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ የሚደረጉ ሰዎች ገንዘቡ በዶላር በዩናይትድ ስቴትስ እንዲቀመጥላቸው እየተደረገ እነሱ አዲስ አበባ ለሚገኙ ተቀባዮችና ቤተሰቦች የኢትዮጵያ ብር እንደሚያስረክቡ ተረጋግጦአል። በኤርትራ ኤምባሲዎች አማካይነት በግልጽ ይካሄድ የነበረው ይህ የገንዘብ ልውውጥ ገበያ ለተወሰነ ጊዜ ጋብ ብሎ ቆይቶ እንደነበርና አሁን ግን እየተከናወነ መሆኑ ይወሳል።

ለኤርትራ ኤምባሲ ቅርብ የሆኑ ምንጮች እንዳብራሩት ባንድ ወቅት በአንደኛው ቀን ብቻ በዚህ ዓይነት ከዋሽንግተን ዲሲ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ለመለወጥ ተችሉአል። እነዚሁ ምንጮች እንደሚሉት የኢትዮጵያ ብር ግዥ ጉዳይ በአንድ ወቅት አሥመራ ላይ በዶላር ዘጠኝ ብር ገብቶ ነበር። ያ እያዘቀዘቀ መጥቶ ለጊዜውም ቢሆን ልውውጡ ተቋርጦ ነበር። አሁን ግን የሀብታሞችን ንብረት እንዳለ ወደ ውጭ ለማሻገር ይቻል ዘንድ የገንዘብ ልውውጡ ገበያ እየደራ መሆኑ ተረጋግጦአል። ይህም ተግባር በአሜሪካ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በሌሎችም የኤርትራ ኤምባሲዎች እየተከናወነ መሆኑ ታውቃአል።

ተመልካቾችም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ማንኮታኮቻ የሆነውና በአገሪቱ ላይ የሚያካሄዱት ዘመቻ አንድ አካል የሆነውን ይህን እንቅስቃሴ ኢትዮጵያውያን መረዳት አለባቸው ይላሉ።

## አራት ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ምግብ ይፈልጋሉ (ጦማር)

በአሁኑ ወቅት አራት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው አንድ የመንግሥት እርዳታ ባለሥልጣን ገልጠዋል።

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የእርዳታ አሰባሰብ ቡድን መሪ አቶ ጌታቸው ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እንደገለጡት ለእነዚህ ኢትዮጵያውያን አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልግ መግለጣቸው ተዘግቧል። በአሁኑ ሰዓት የመንግሥት ትኩረት በጦርነቱ ላይ በመሆኑ የተራበው ሕዝብ ሕይወት ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ የእርዳታ ባለሥልጣናት ማሳሰቢያ እየሰጡ ይገኛሉ ተብሏል።

## 237 የአየር ኃይል አባላት እንደገና ተጠሩ (ጦማር)

የቀድሞ አባላቱን በማሰባሰብ ላይ ያለው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ለሦስተኛ ጊዜ ለ237 የቀድሞ አባላቱ ከነሐሴ 18 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ በስም ዝርዝር ጥሪ አቅርቧል። እነዚህ የትምህርት ማስረጃቸውን ይዘው እንዲቀርቡ የተጠሩ የአየር ኃይል አባላት፤ ቀደም ሲል በነበረው ጥሪ የደህንነት አባላት ናቸው ተብለው የተተው ናቸው ተብሏል። ጥሪ ከተደረገላቸው መሐከል ወደ ውትድርና ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆኑ እንደሚገኙበት የታወቀ ሲሆን፤ በጥሪው መሰረት የማይመለሱት የአየር ኃይሉ አባላት ዕጣ ምን ሊሆን እንደሚችል አልታወቀም።

## ከ250 በላይ የቀድሞ መኮንኖች ሳዋ ይገኛሉ (ጦማር)

በኤርትራ መንግሥት ትልቁ የብሔራዊ ውትድርና ማሠልጠኛ ማዕከል ውስጥ ከ50 በላይ የቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር መኮንኖች በአሠልጣኝነት ተቀጥረው እንደሚሰሩ ተገለጠ። ለዓመታት ኤርትራ ውስጥ የነበሩና በጦርነቱ ፍንዳታ ማግስት ከኤርትራ የወጡ የዓይን ምስክሮች ለጦማር ጋዜጣ እንደገለጡት ከሆነ በሳዋ የሚገኙት መኮንኖች ኤርትራውያን ቢሆኑም የአየር ኃይሉን ከእስራኤሎች ጋር በመሆን በማሠልጠን ላይ የሚገኙ የቀድሞው የአየር ኃይል

አባላትም እንዳሉ ተገልጧል። በተያያዘ ዜና የተማረኩ በርካታ መኮንኖች በናቅፋ ውስጥ ታጉረው የሻዕቢያ መንግሥት በሚያሰራቸው ሕንፃዎች በነፃ ጉልበት እየገነቡ መሆኑ ታውቋል።

## ከአራት ሺ በላይ ኢትዮጵውያን መውጫ አጥተዋል ተባለ (ጦማር)

ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የሚፈልጉ ከ4000 በላይ የሆኑ ኢትዮጰያውያን በኤርትራ መንግሥት እምቢተኝነት የተነሳ በአሥመራ ውስጥ መከማቸታቸውን የመንግሥት ቃል አቀባይ ዘገባ አመልክቷል በቃል አቀባዩ ዘገባ መሠረት ከእነዚህ ኢትዮጰያውይን መሀከል 2100 የሚሆኑት በቀይ መስቀል ተመዝግበው እንዳይወጡ የተከለከሉ ሲሆኑ 2000 የሚሆኑት ደግሞ የመመዝገብ ዕድል እንዳልተሰጣቸው ታውቋል። የኤርትራ መንግሥት እነዚህን ኢትዮጰያውያን የማይለቃቸው ከሆነ የኢህአዴግ መንግሥት እርምጃ ምን ሊሆን እንደሚችል አልታወቀም።

## የኤርትራ መምህራንና ተማሪዎች በግዳጅ ላይ ናቸው (ጦማር)

የሻዕቢያ ባለሥልጣናት ለጦርነት እራሳቸውን ይበልጥ እያዘጋጁ ባሉበት በአሁኑ ወቅት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ከ30ሺ በላይ ተማሪዎች ከአራት ሺህ በላይ መምህራንና ሰራተኞች በግዳጅ በየበረሃው ዘምተው ሻዕቢያን በማገልገል ላይ ይገኛሉ ተብሏል። የልማት ዘመቻዉ በተባለው ለዚህ የግዲታ ዘመቻ ላይ ላለመሳተፍ ፍቃደኛ ያልሆኑ በርካታ ወጣቶች በእስር ላይ እንደሚገኙ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ገልጠዋል።

## አባ ጳውሎስና የትግራይ ሕዝብ ፊት ለፊት ሊፋጠጡ ነው!

(ፈያሚታ)

የትግራይ ካህናትና ምዕመናን በአባ ጳውሎስ ላይ ግልፅ የተቃውሞ እርምጃቸውን በሰላማዊ ሰልፍ የገለፁት ሚያዝያ 21 ቀን 1990 ሲሆን ከዚያች ዕለት ጀምሮ በዚያው አካባቢ ድርሽ ያላሉት አባ ጳውሎስ ሰሞኑን ወደ ትግራይ እንደሚያቀኑ ተጠቆመ።

ውስጥ አዋቂዮችና የነገሩን ቅድመ ዝግጅት የተረዱት ወገኖች እንዳሉት ከሆነ፡ ለተፈናቀሉት ወገኖች የብርድ ልብስ ስጦታ ለማበርከት እፈልጋለሁ በሚል፣ አንቅሮ ወደተፋቸው ሜዝብ በማምራት ፊት ለፊት ሊፋጠጡ መሆናቸውን አውስተዋል።

የፓትርያርኩን አስተዳደር በተቃወመ ማግስት ጀምሮ አባ ጳውሎስ የሚለውን ስም ቄምር በማንኛውም የፀሎት ሥነ ሥርዓት ላይ መጥራት ካቆመ አምስተኛ ወሩን በማገባደድ ላይ ያለው ትግራይ የሰውየውን ፊት ለማየት ፍላጌት እንደሌለው ከአካባቢው የሚደርሱን አስተያየቶች እያስታወቁ ነው።

በትግራይ በሕፃናትና አዛውንት ላይ ስለደረሰው ዘግናኝና አሰቃቂ ጭፍጨፋ አስመልክተው በሃይማኖት አባትነታቸው ወዲያውኑ በመሄድ ማፅናናት መርዳት ሲገባቸው 'ድብ ከሄደ ውሻ ጮኸ' ዓይነት በአራተኛ ወራቸው ለመሄድ መነሳታቸው እንቆቅልሽ ነው ቢሉ ውስጥ አዋቂዎች እየተቹ ናቸው። ወደተፈናቀሉት ወገኖች ይሄዳል የተባለው ዕርዳታም ቢሆን በተወካይ ተልኮ መስጠት የሚቻል ነው፣ ያሉት ውስጥ አዋቂዮች በዚህ አጋጣሚ የጠላቸው ሜዝብ ጋር ለመቀላቀል እንዲችሉ በአማካሪዎቻቸው የተለገሰ ሃሳብ ሳይሆን አይቀርም ብለዋል። ፓትርያርኩም ጸመ ፍልሰታን እንደነገሩ ከአንድ ሁለት ጳጳሳት ጋር ማለትም ከአባ ገሪማና ከአባ ኒቆዲሞስ በመሆን በሁለቱ አጃቢነት ቅ/ማርያም በማስቀደስ ከምንጊዜም በተለየ መልኩ የብቸኝነት ጊዜ ያሳለፉ መሆናቸውን የገለፁት ውስጥ አዋቂዮች ከትግራይ መለስ ደግሞ ወደ ውጭ ዓለም (ሮማንያ) እንደሚያመሩ ጠቁመው፣ አዲሱን ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስን ሳያስከትሏቸው እንደማይቀሩ ግምታዊ ትንበት እየተናገሩ ነው።

## አረጋዊ በርሄ የሕወሐትን የወሰን አከላለል አጋለጡ

የጀርመን ከተማ በሆነችው ፍራንክፈርት ላይ በተደረገ ኢትዮያዊ ስብሰባ ላይ ኢትዮጰያውያን ስለ ሃገራቸው ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ሰፋ ያለ ጉባኤ ማካሄዳቸውን ከትናንት በስቲያ የተሰራጨው የጀርመን ድምፅ ሬዲዮ ሃተታ ይፋ አድርጓል።

የስብሰባው መሪ በሆኑት በአቶ ዳዊ ኢብራሂም በእለቱ የተመራው የኢትዮጰያውያኑ ስብሰባ በተለያዩ ርእሶች ላይ ያተኮረ መሆኑ ሲገለጽ ዶ/ር ነገደ ጌበዜ ኑየተቃዋሚ ኃይሎች የትግል አንድነት ግንባታ ከፓሪሱ ጉባዔ ጀምሮ እስከ መጪው ምርጫ የተስፋው ቂላንቂል በድኅረ ወያኔ ሻዕቢያ ጦርነትዉ በአቶ ከፍ ያለ ማሞ የነፃው ፕሬስ ሚና ቢዝቡ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ውስጥዉ በአቶ መሃመድ ሃሰን እስላማዊነትና ኢትዮጰያዊነትዉ በሚሉ ሰፋፊ ርዕሶች ላይ ሰፋፊ ማብራሪያ መስጠቱን ጋዜጠኛ ሰብለ ቢሆን ገልፃለች።

በሰሚናሩ ላይ አብዛኛው ተሳትፎ ያደረጉት ሴቶች ሲሆኑ የጦርነቱ ሁኔታ እንዳንገበገባቸው ጋዜጠኛዋ ገልፃ የኅብረት ትግል የሚሉ ወገኖች አይለው መታየታቸውን ጨምራ ገልፃለች። ጋዜጠኛዋ በመቀጠልም የኢትዮጰያ መንግሥት በአዛውንቱ ሚበር አደረሰ የተባለው በደል እንዲያቆም ጠንከር ባለ አቋም መጠየቁ ተዘግቧል።

በነፃው የፍርድ አደባባይ ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት እጃቸው በሰንሰለት መታሰሩ ተሰብሳቢዎችን ክፉኛ ማስቆጣቱ ይፋ ሆኗል። በስነ–ምግባሩ ምሉዕ፣ በቢሪው ጨዋ የሆነው የኢትዮጰያ ሜዝብ ይህን ድርጊት ያገናዘበው የቀደምቶችን አርበኞች ታሪክ ያጣቀሰ ማጠናከሪያ በተሰብሳቢዎች የቀረበ ሲሆን እስላማዊና ኢትዮጰያዊነት በሚለው ርዕስ ላይ ተከባብረው የኖሩት የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮች ባላቸው ጤናማ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል በአሉት ሃሣብ ላይም የማስተካከያ አስተያየቶች መስጠታቸው ተገልጧል። እንዲሁም በሁለቱ ሃይማኖቶች በዓል ላይ የመተሳሰብ ስሜት ለአለም ኅብረተሰብ በአርአያነቱ መውጣቱ ይፋ ሆኗል።የኤርትራን መገንጠል ባልደገፉት ወገኖች ድንበራችን ባድመ ሳይሆን ቀይ ባህር የሚል አቋም ተንፀባርቋል። ከዚህ ጋርም በተዛመደ የወሰን ጉዳይ በጌንደር ክ/ሃገር ይሁንታዊ ፈቃድ ሳያገኝ የወልቃይት የሰቲት ሁመራ ለም መሬት

የትግራይ ክ/ሃገር እንዲሆን መከለሉ አግባብነቱ እንዴት ታየ ለሚለው ጥያቄ አቶ አረጋዊ በርሄ ማካ በነበሩበት ጊዜ የተሰራ ስህተት መሆኑን በግልጽ መስክረዋል። ኢትዮጰያውያኑ ተሰብሳቢዎች የቀኑ ሙቀት ሳይበግራቸው እኩለ ቀን ላይ የጀመሩትን ስብሰባ እስከ ሌሊቱ 6 ሰዓት ድረስ ማካሄዳቸውን ጋዜጠኛ ሰብለ ቢሆን ገልፃ በመጨረሻም ባለ አምስት ነጥብ መግለጫ መውጣቱን አስደምጣለች። ስልጣን ያለው የኢአዴግ መንግሥት በበጐ እንቅስቃሴዎች ላይ እንደበቱ እንደሚሰላ ሁሉ በየስብሰባው የሚነሱ ስሞታዎችን ለማድመጥም ሆነ ለማስተናገድ ደፋር ጆሮ ቢኖረው እርምጃዎችን ለማርገብ ቢሞክር፣ ተቃዋሚ ኃይሎችንም የሃገርን ዳር ድንበር በማስከበሩ ሂደት ልዩነቶቻቸውን ለጊዜው አቻችለው ከኢትዮጵያ ሜዝብ ጋር በተግባር ቢቆዩም የተሻለ መንገድ ይሆናል መባሉ የተወሳ ሲሆንለዚህ በመጠናከሪያነት የቀረበው ኢትዮጰያ አገራችን በዚያድባሬ ጦር ድል ተነስታ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ታድገናታል በሚሉ ወገኖች ይሁን፣ ወደባሰበት አዘቅት ትወርዳለች ማዳን አለብን በሚሉት መካከል ያለው እሰጥ አገባ በሌሎች ሃገር ላይ በሆን ነበር፣ የሃገራችን ሜልውና፣ እስትንፋስ እንዲቀጥል፣ ሉዓላዊነቷ እንዲፀድቅ ከተፈለገ ከበቀል የፀዳ ህብረት ያስፈልጋል ብሎ ጉባኤው ማጽደቁን ጋዜጠኛዋ በማብራራት ዘገባዋን አጠቃላለች።

## እስራኤል የኢትዮጰያን ተዋጊ ጄቶች ልታድስ ነው
## 13 ሚሊዮን ዶላር ጠይቃለች

11 የኢትዮጰያ አየር ኃይል ተዋጊ ሚግ ጄቶችን ለማደስ ተዋውላ የነበረችው እስራኤል የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር ውሏን ማፍረሷ ከተዘገበ ከሁለት ሳምንት በኋላ የዕደሳ ዘመቻዋን ለመቀጠል የሚያስችላት ቅድመ ሁኔታዎች መዘጋጀታቸውን ኑአል–ቀዱስዉ የተባለ መጽሔት ዘገበ። በእስልምና ሃይማኖት ላይ በማተኮር ለንደን ውስጥ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚታተመውና እዚህ አዲስ አበባም በኢራን ኤምባሲ አማካኝነት የሚሰራጨው አል–ቁዱስ (AL~QUDS) እንደገለፀው እስራኤል የኢትዮጰያን ተዋጊ ጄቶች ለማደስ 13 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልገኛል ማለቷን አሳውቋል። በእስራኤል የሚገኝ አንድ የግል ኩባንያ የኢትዮጰያን 11 ሚግ የአየር ኃይል ተዋጊ ጄቶችን ለማደስ ጨረታውን ማሸነፉን መጽሔቱ ገልጿል።መረጃዎች እንደሚጠቁሙት እስራኤል በኤርትራ የዳህላክ ደሴቶች ላይ ባላት የጦር ሠፈር በአካባቢው የሚገኙ የአረብ አገሮችን ለመሰለል እንዲያስችላት የሻዕቢያው መንግስት ለኢትዮጰያ የጄቶችን ዕድሳት ማድረግ እንደሌላባትና ምናልባት እድሳቱን ብታካሂድ የጦርነት ሚዛኑ ወደ አንድ ጐን ሊዛባ እንደሚችል ለእስራኤል በማስታወቋ እስራኤል ለኢትዮጰያ የገባችን ውል በማፍረስ የዕደሳ ጥያቄውን ሰርዛ እንደነበር ማስታወቋ አይዘነጋም። አሁን ኩባንያው ጨረታውን አሸንፎ ዕድሳቱን የሚያካሂደው 13 ሚሊዮን ዶላር ሲከፈል ብቻ እንደሆነ ታውቋል። የኢትዮጰያ መንግሥት በቀረበለት የድርድር ሐሳብ ይስማማ አይስማማ የታወቀ ነገር የለም።




# ሞናሊዛ የውበት ሳሎን
*Monaliza Hair Studio*

ውበትን በተመለከተ የተሟላና የተቀላጠፈ አገልግሎት እንሰጣለን።
ጥራት ያላቸው የውበት ምርቶችም አሉን።
አገልግሎታችን ሁሉንም ጾታ እንዲሁም ልጆችን ያጠቃልላል።

በሥራችን ጥራት፤
በቅልጥፍናችን ይኮራሉና ብቅ ይበሉ!!



አድራሻችን
ካሊፎርኒያ ማርት አጠገብ
2100 Cheshire Bridge Rd. Suite G
ስልክ ቁጥራችን
(404)486–7355



# የአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ፓትርያርኩ ካቴድራል ተባለች።



የኢትዮጵያ ኦርትዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. አትላንታ ከተማ ገብተዋል። ቅዱስ ፓትርያርኩ ወደ አትላንታ የመጡት የአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን 11ኛ ዓመት ክብረ በዓል ላይ ለመገኘት ነው። ቅዱስነታቸው አትላንታ አይሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ ሕፃናት እቅፍ አበባ ያበረከቱላቸው ሲሆን በስደት የሚገኙት ብፁአን ጳጳሳት፣ ካህናት አበው መነኮሳትና ዲያቆናት እንዲሁም የቤተክርስቲያኒቱ ቦርድ አባላትና ምዕመናን ታላቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል። ከዚያም ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ብዙ ኢትዮጵያውያን፣ መዘምራን በመዝሙር ሕዝቡ በእልልታ ተቀብለዋቸዋል። ቅዱስ ፓትርያርኩ ለ6 ዓመታት በስት ከቆዩበት ኬኒያ ወደ አሜሪካ የገቡት በቅርቡ ሲሆን አመጣጣቸውም ለጊዜው ቆይታ ካደረጉበት ሲያትል ከተማ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ለስት ያበቃቸውም በወቅቱ በኢትዮጵያ ያለው የጎሳ አርር ከቤተ ክህነቷ አመራርና ቀኖና ውጭ በህይወት እያሉ ሌላ ፓትርያር በመሾሙና ሕይወታቸው አሳሳቢ ደረጃ በመድረሱ መሆኑ የሚታወቅ ነው።



የአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ኦርትዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን 11ኛውን ዓመታዊ የንግሥ በዓል ቅዱስ ፓትርያርኩ፣ ብፁአን ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ፣ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስና ብፁዕ አቡነ መልፀዴቅ እንዲሁም ከየስቴቱ የመጡ ካህናትና ዲያቆናት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ምዕመናን በተገኙበት በታላቅ ድምቀት ተከበሯል። በዚሁ ወቅት የቅዱስ ሚካኤል ታቦት




በቤተክርስቲያኒቱ መግባቱ የተገለፀ ሲሆን ከቅዳሴው ስርዓት በኋላ ሁለቱ ታቦታት በክብር ወጥተው በምዕንን ታጅበው ከተዘጋጀው ሜዳ ላይ ካረፉ በኋላ ተመልሰው ወደ መቅደሱ ገብተዋል። በዚሁ ዕለት ቅዱስ ፓትርያርኩ ቤክርስቲያኒቱን ካቴድራል ብለው የሰየሙ ሲሆን በደብሩ አስተዳዳሪ መላከ ፀሐይ ገብረማርያም አያሌው አቅራቢነት ቀሲስ ኤፍሬም አ. ከበደ ሊቀ መዘምር ተብለው ተሹመዋል። የምዕመናኑን ጥያቄ በማስመርኮዝ የደብሩ አለቃ አትላንታ ርዕሰ ደብር ሆና የቅዱስነታቸው መንበረ ፓትርያርክ እንድትሆን የጠየቁ ሲሆን ቅዱስነታቸውም በቅርቡ አሃዮ በሚካሄደው የሲኖዶስ ጉባኤ ላይ ውሳኔ እንደሚሰጥ ገልፀዋል።



የቅድስት ማርያምና ቅዱስ ሚካኤል ታቦታት





የአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ቤተ ካቴድራል



# ብሔራዊ እርቅ

ከዮናታን ቡሬ

*«በመጀመሪያ ይሁዳዎች ለማጥፋት ሲመጡ ምንም አላልኩም ይሁዳዊ ስላልሆንኩ፣ ቀጥለውም ኮሚኒስቶችን ለማጥፋት ሲነሱ አሁንም ኮሚኒስት ስላልሆንኩ ዝም አልኩ፣ ከዛም የሠራተኛ ማህበር አባላት ላይ ተነሱ አሁንም እጄን አላነሳሁም። የሠራተኛ ማህል አባል አልነበርኩምና በመጨረሻም ወደ እኔ መጡ። ያኔ ሁሉም አልቆ ነበርና ማንም የሚረዳኝ ሰው አጣሁ።*

ይህ በ2ኛ የዓለም ጦርነት ወቅት ከጀርመን ናዚዎች ለጉድ የተረፈ አንዱ የገጠመውን ችግር በማስታወስ የተናገረው ቃል ነበር።

ዛሬ በአገራችን የተከሰተው ሁኔታ ከዛሬ 53 ዓመታት በፊት ይሁዳዊው የተናገረውን ቃል በጥሞና እንድንመረምር የሚገፋፋን ነው። እኔ ከሞትኩ በኋላ ሳር ቢበቅል ባይበቅል ግድየለኝም ያለችውን የአህያዋ ፈሊጥ የምንከተልበት ወቅት ውስጥ አይደለም ያለነው። ከርሱ ይልቅ «ነግ በእኔ» ብለን «ምን መደረግ አለበት?» የሚለውን ጥያቄ የጋራ ትኩረታችን ልናደርገው የሚያስገነዝበን ወቅት ውስጥ ነው ያለነው።

ሻዕቢያና ኢህአዴግ ገና በጨቅላ ዘመናቸው ዓይንና አፈር ሆነው ጦር ይማዘዛሉ ተብለው ፍጹም አልተጠበቁም ነበር። በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍጹም ያልተጠበቀ ሁኔታ ውስጥ ገብቷል።

ለነገሩማ የዛሬ ተፋላሚ ኃይሎች በድል ማግሥት የጋራ መከላከያ ኃይል ተፈራርመው አልነበረምን? አንዱ ወገን በሌላ የውጭ ኃይል ሲጠቃ ፈጥኖ እርዳታ ለመስጠት ነበር የስምምነቱ መሰረታዊ ዓላማ። ተፈራራሚዎቹ ራሳቸው ሲጋጩ ግን ሁኔታውን ከራስ ጋር እንደመጋጨት ከመቁጠር ሌላ ምን ሊባል ይቻላል? ችግሩና ጠንቁ ግን ለሰላማዊ ሰዎች ህይወት መጥፋት መትረፉ ነው።

የኢህአዴግም ሆነ የሻዕቢያ አጠቃላይ ፖሊሲና ፍላጐት የተለያዩ ናቸው ባይባልም በተለይ አቶ ኢሳይያስ ይህን የጦር ጫሪነት እርምጃ በአገራቸው በወንዛቸው ልጅ ላይ ለመውሰድ ምን አስገደዳቸው? የሚለው ጥያቄ በእኛ ግምት መነሳት ያለበት ጥያቄ ይመስለናል። በእነርሱ ትልምና ፍላጐት መሰረት ኤርትራ የዛሬ 6 ዓመት ከተገነጠለች በኋላ በአንዲት ጀንበር ራሷን እንደምትችል ተደርጐ ነበር በየአደባባዩ ሲነገር የተሰማው። ትንሿ ሮማም ትሆናለች ተብሎ ነበር። በአፍሪካ የዳቦ ቅርጫትም ተመስላ ነበር።

የፖለቲካ «ነፃነት» በኢኮኖሚ ነፃነት ካልተገዛ ውጤቱ ጦርነት ነው። በሰባት ዓመታት ሂደት ውስጥ ግን ይህ ሁሉ ከህልምነት ደረጃ ሊያልፍ አልቻለም። በተለይ ኢህአዴግ አንዳንድ የኢኮኖሚ እርምጃዎችን ከወሰደ በኋላ በኤርትራ ራስን የመቻል ሳይሆን የመኖር ጥያቄው ራሱ ችግር ውስጥ መግባት ጀመረ። ስሞኑን አቶ ኢሳይያስ «ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ላይ ያደረገችውን ማዕቀብ ካላነሳችና የኢትዮጵያ አየር መንገድም ወደ አሥመራ እንደገና እንዲበር ካላደረገች አይቀጡ ቅጣት ነው የምንቀጣት» ሲሉ ያሰሙት ድንፋታ የሚያመለክተው ይህንኑ ክልሉ የደረሰበትን የኢኮኖሚ ቀውስ ነው። ከዚህ በተጨማሪም አባባላቸው እብሪታቸው የደረሰበትን አፋፍ የሚያመለክትም ነው። የውድቀት አፋፍ!!!

ጥንትም ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ያለው ይህንኑ ነው። ኤርትራና የኤርትራ ህዝብ ከተቀረው ወንድሞቹና እህቶቹ ተለይቶ ሊኖር አይችልም። ይችላል የሚሉ ካሉ ግን እነዚያ የግል ፍላጐታቸውን ለማራመድ የሚሹ የገገር መደብ አባላት ብቻ ናቸው።

ፍላጐት ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ካልተገናዘበና ካልተጣጣመ ውጤቱ አያምርም። የፈለጉትንም ማግኘት አይቻልም። አቶ ኢሳይያስ የገጠማቸው የኢኮኖሚ ቀውስም ያስከተለው ውጤት ዳግም ለሰላማዊ ሰዎች ህይወት መጥፋት መንስዔ የሚሆን ጦርነትን ማካሄድ ነው።

በአምባገነን መሪዎች ግፊትና ተፅዕኖ ካልሆነ በስተቀር ህዝብ መፈቃቀርን ይፈልጋል፣ የጋራ ዕድገትና ብልፅግናን ይሻል፣ ሰላምን ይናፍቃል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት ስርዓቶች ላይ ተቃውሞውን ሲያሰማ የነበረው አንዱን አምባገነን መሪ አንስቶ በሌላ አምባገነን መሪ ለመተካት ወይም አንዱ ጦርነት አክትሞ ሌላ ጦርነት ለመጀመር አልነበረም።

ለዚህ ነው ይህ ወቅት አገራችን በረጅም ዘመን ታሪኳ ገብታበት የማታውቀው ልዩና ፈታኝ ወቅት ውስጥ ገብታለች ለማለት የምንደፍረው።

አገርንና ህዝብን ለማዳን ማናቸውንም ዓይነት መስዋዕትነት መክፈል አለበት የሚለውን መርህ ከልብ የምናምንና የምንከተል ከሆነ መጠነኛ መስዋዕት በማድረግ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ህዝብ ለማዳን ይቻላል።

ምንም እንኳን ወቅቱ አገራችንን አስከፊ ጦርነት ውስጥ የጨመራት መሆኑ ቢታወቅም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወቅቱ እንደመልካም አጋጣሚ ሊቆጠር የሚችል ነው። ይኸውም አቶ መለስና አስተዳደራቸው ከተቃዋሚ ቡድኖችና በተለይም ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እርቀ-ሰላም ሊያወርዱ የሚያስችላቸው ወቅት ነው፣ ካወቁበት። የህዝብን ጥያቄ በየደረጃው እየተመለከቱ ለመፍታት ተግባራዊ እርምጃ የተወሰደ እንደሆን በአንድ ኃይል ወራሪን ለመቋቋም ይቻላል፣ በቤት ውስጥ የአንድነት ስሜትን መፍጠር ይቻላል፣ መተማመንን ማዳበር ይቻላል።

አገርን አስተዳድራለሁ እያሉ ለአንድ የተለየ ጉሳ መቆም ዘረኛ እንጂ መልካም አስተዳዳሪ አያሰኝም። አንድን ጐሳ ለይቶ መጥቀም ይቻላል፣ አገርን ከጥቃት ለማዳን ግን አንድን ጐሳ ብቻ ይዞ ጦር ሜዳ መሰለፍ አይቻልም። አገር ለሁሉም ሁሉም ለአገር ነውና!! የወቅቱ መልካም አጋጣሚነት አንዱ ባህርይ ይኸው የኢትዮጵያን ህዝብ ይበልጥ ሊያቀራርብና በአንድ ስሜት ሊያገናኝ መቻሉ ነው።

ይሁን እንጂ ትክክለኛው ስልት ተቀይሶ ለበጐ አላማ እስካልተሰለፉ ድረስ የሚፈለገው የአንድነት መንፈስ፣ የጋራ አቋምና አስተሳሰብ ሁሉ በራሱ ዝም ብሎ የሚመጣ ነገር አይደለም። ለዚህ ነው ከፍ ሲል አቶ መለስና አስተዳደራቸው ቢያውቁበት ያልነው። በሌላ አነጋገር የራስን ቤት አስተካክሉ፣ ስምምነትን ፈጥሮ በአንድ ኃይል ጠላትን ለመቋቋም የሚያስችል ስልት መቀየስ ወሳኝ ነው። ይህም ስልት ብሔራዊ የእርቅ ጥሪ ነው።

## ብሔራዊ እርቅ ማለት ምን ማለት ነው?

እንዴትስ ይመጣል? የሚያመጣውስ ማነው? ከመጣስ በኋላ ምን መልክ ይኖረዋል? የሚሉትና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በማንሳት ጉዳዩን ዘለግ ብሎ መመርመር ያስፈልጋል።

በቅድሚያ ብሔራዊ እርቅ ማለት በሁለት ወይም ከዛ በላይ በሆኑ በተለያዩ ቡድኖችና መንግሥታት ወይም በመንግሥትና በህዝብ፣ ወይም ህዝቦች መካከል ያለውን ልዩነት አስወግዶ በህብረት ለመሰለፍ የሚያስችል የተግባር እርምጃ ነው።

በማናቸውም መልኩ የተከሰተውን ልዩነት ቢቻል አስወግዶ ካልተቻለም በሁለተኛ ደረጃ በመመልከት እገሌ ከእገሌ ሳይባል ሁሉም ተፋላሚ ኃይሎች ለብሔራዊ ጥቅምና ህልውና ሲሉ በአንድነት የሚገናኙበት መድረክ ነው።

በዚህ ትርጓሜ ከተስማማን ዘንዳ ተከታዩ ጥያቄ ይህ እርቅ በማንና እንዴት ሊመጣ ይችላል? የሚለው ይሆናል።

እርቁ ማንንም፣ በምንም መስፈርት ሳያገል፣ በእኩልነት ለተቃዋሚ ቡድኖችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ የሚቀርብ ነው። የኢህአዴግ አስተዳደር ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የአንድነት ስሜት ፈጥሮ ጠላትን ለመቋቋም እንዲቻል ይህን ብሔራዊ ጥሪ ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ማቅረብ አለበት። በዚህ መነሻነት ጥሪ የተደረገላቸው ወገኖችና ጥሪውን አቅራቢ አካል መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር አንድ ዓይነት ስምምነት ላይ መድረስ ይኖርባቸዋል። ከሁለቱም በኩል በሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ ሲደረግ ብቻ ነው ብሔራዊ እርቁ ትርጉም ኖሮት የተፈለገውን ግብ ሊመታ የሚችለው።

ለመሆኑ የዚህን ብሔራዊ እርቅ አቶ መለስ እንዴት ያዩታል? ሌላው ሊነሳ የሚችል ጥያቄ ይመስለናል። በእኛ ግምት የእርሳቸው መልስ በተለይ ባህርያቸውን በቅርብ ለተከታተለ ሰው እምብዛም አዳጋች ነው ብለን አንገምትም። «ምን መጣና ነው ብሔራዊ እርቅ የሚባለው? እርቁስ ከማን ጋር ነው?» ብለው ጥያቄውን በጥያቄ ለመመለስ ቢሞክሩ አይደንቀንም። «የሚፈልግ ቡድን እንደሌሎቹ ሁሉ አገር ቤት ገብቶ ለመስራት እድሉ ትላንትም ነበር፣ ዛሬም ነገም እንዲሁ ይኖራል» የሚል ምላሽ ሊሰነዝሩ ይችላሉ። በእርሳቸው እምነት የኢትዮጵያም ህዝብ ደልቶት የሚኖር ስለሆነ ፀብ ሳይኖር እርቅ መጥራት ያልበላውን የሰውነት አካል እንደማከክ ሊቆጥሩት ይችላሉ። በተለይ አቶ መለስ አሁን ያሉበት የፖለቲካ ሁኔታ ሚዛኑ ለእርሳቸው ያጋደለ ስለሆነ እርቁም ጠቡም ያለው ከሻዕቢያ ጋር ብቻ እንጂ ከሌላ አይደለም በሚል አመለካከት ሊመሩ ይችላሉ። የአሜሪካንን ድጋፍ በማግኘታቸው፣ ይነስም ይብዛ ከውስጥ ደጋፊዎቻቸው እየተጠናከሩ በመምጣታቸው፣ የጊዜው ጠላታቸው የኢኮኖሚ አዘቅት ውስጥ በመግባቱና በተለይም ፈርጠም ያለ ተቃዋሚ ቡድን ስለሌለ ለእርሳቸው የብሔራዊ እርቅን ጉዳይ በይደርም የሚመለከቱት አይመስልም።

ሁኔታው ይህን ሐቅ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ከተገኘ በተለይ ተቃዋሚ ቡድኖች ለወያኔ ኢህአዴግ አስተዳደር ስልታዊ ድጋፍ በመስጠት የጦርነቱን ሂደት በቅርብ መከታተል ይኖርባቸዋል። አንድነታቸውንና አለኝታነታቸውን በተለይ ለትግራይ፣ ለአፋርና ለወሎ ክፍላተ ሀገራት ህዝቦች በተግባር ማስመስከር ይጠበቅባቸዋል። ብሔራዊ እርቅ እንዲደረግ ግፊት ከማድረግ ባሻገር ዘሎ አንድም የሚያዝ፣ የሚጨበጥ ነገር ሳይኖር ከወያኔ ኢህአዴግ ጋር ወገንኩ ማለት ግን ጉዳት ሊያስከትል ይችላልና በጥንቃቄ መመልከቱ ይበጃል።

– ብሔራዊ እርቅ አገርን ከጥፋት ለማዳን የሚደረግ ጥሪ ነው።
– ብሔራዊ እርቅ የህዝብን ህልውና ለማስከበር ሲባል የሚወሰድ እርምጃ ነው።
– ብሔራዊ እርቅ ሰላምን ለማስፈን የሚረዳ ስልት ነው።
– ብሔራዊ እርቅ የእስከዛሬው ጥፋት ለታሪክ ተትቶ ለአዲስ ህይወት አዲስ ምዕራፍ የሚከፈትበት ወቅት ነው።

**ደርግ እስከሚወድቅ ድረስ ጠብቆ ካስተላለፈው ብሔራዊ እርቅ ጥሪ ትምህርት በመውሰድ አገርንና ህዝብን ማዳን ይቻላል።**

# ሻቢያ በኢትዮጵያ ላይ ስላደረገችው ወረራ ከተለያዩ ኢትዮጵያውያን ምሁራን፤ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች የተሰጡ አስተያየቶችና ግንዛቤዎች

**ሻቢያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገችውን ወረራ በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን፤ ሕዝባዊና የፖለቲካ ድርጅቶች ያቀረቡትን አስተያየቶች እናቀርባለን። እነኚህ አስተያየቶች በአብዛኛው አትላንታ በሚገኘው የማህደረ አንድነት ሬዲዮ ፕሮግራም ላይ የቀረቡ ሲሆኑ መሆናቸውን ለመግለጽ እንወዳለን።**

***ውድ አንባብያን፤ እነኚህ አስተያየቶች የተሰጡት ቀደም ሲል ጦርነቱ በተነሳበት ወቅት በመሆኑ መግለጫዎቹን አስተያየት ከተሰጠባቸው ጊዜ አንጻር እንድትመለከቱት።***

---


## ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው

ሚቺጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ


### 1. የግጭቱን መነሻ በተመለከተ

ይህ ልዩነት የሚባለው በምን ረገድ እንደሆነ ግልጽ መሆን የሚኖርብን ይመስለኛል። ኤርትራ ልዩ አገር ነን ብለው መዋጋት ከጀመሩ ረጅም ጊዜ ሲሆን፤ ማዕከላዊውን የኢትዮጵያውን መንግሥት ለመዋጋት ደግሞ ያስፈልገናል ብለው ከጀመሯቸው አንዳንድ የትግል ታክቲክና ስትራቴጂ አንፃር እንደ ወያኔ ያሉ ወይንም በብሔር ወይም የጐሳ ጥያቄ ላይ የተመሰረቱትን አንዳንድ ድርጅቶችን መኮትኮትና ማሳደግ ያስፈልጋል ብለው ወያኔን ፈጥረው አደራጅተው፣ አስታጥቀው በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም በትግራይ ክፍለ ሀገር ውስጥ እንድታተገል ለማድረግ ችለዋል። በዚያን ጊዜ በዚህ ድርጅት ላይ ሙሉ ቁጥጥር ነበራቸው። ያም ሆኖ ግን በወያኔ ውስጥ የተሰለፉት ሰዎች የትግራይ ብሔረተኛነት ወይም ጐሰኝነት ስሜት ነበራቸውና ያ ሁል ጊዜ ከኤርትራ ፍላጐት ጋር አንድ ይሆናል ማለት አይደለም። ሆኖም ግን ተጠጊዎች ስለነበሩ ሙሉ በሚሉ ፈጣሪያቸውና ደጋፊያቸው በነበረው ሻዕቢያ ፖሊሲ እየተገዙ ለረጅም ጊዜ ሄደዋል። የጦር ቃል ኪዳን ሰርተው ኢትዮጵያም ውስጥ ያሉን ኃይሎችን እና በኤርትራ ውስጥ ደግሞ ከሻዕቢያ ጋር የሚጋጨውን የELF ወይም የኤርትራ ሃርነት ግንባርን ወግተው የሻዕቢያ ተቀጢላ ሆነዋል ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ነው እንግዲህ እጅና ጓንት ሆነው ሲሰሩ ቆይተዋል የሚባለው።

ሆኖም ግን በሂደቱ ውስጥ ግጭት ብዙ ጊዜ ነበረባቸው። ካመሰራረታቸው፣ ከፍላጐታቸው፣ ከሚያራምዷቸው ፖሊሲ፣ ከሚከተሏቸው የትግል ስትራተጂዎች አንፃር ልዩነት አሏቸው። ለምሳሌ፣ በ1985 በፈረንጅ ወይም ደግሞ 1977/78 በኢትዮጵያ አቆጣጠር ትልቅ ረሃብ ትግራይ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ለጊዜው ብዙ ነገሮች ግልጽ ባልሆኑበት ምክንያት ኤርትራ ድንበር ዘግታ ምግቦች፣ ስንቆችና ትጥቆች ወደ ትግራይ እንዳይገቡ አድርጋ ስለነበር ያም ወደ ጦርነት የሚያመራበት ሁኔታ ሁሉ ተከስቶ እንደነበር ይታወቃል። በዚህ በዚህ እንግዲህ ልዩነቶችን ስንመለከት በዋናው ነገር ወያኔና ሻቢያ መሃል ያለው ልዩነት የሚከሰተው በሁለቱ ድርጅቶች መሃል ሳይሆን በትግራይ ህዝብ ፍላጐትና የኢትዮጵያ አንዳንድ ብሔራዊ ስሜት በሚሰማቸው የወያኔ አባላት በኩል በሚሰሙት ነገሮች ነው።

የትግራይ ሕዝብ በጣም ኢትዮጵያዊነት ይሰማዋል። ከዚያ በተረፈ በኤርትራ ውስጥ ደግሞ በትግራዮች ላይ የሚደርሰው ጭቆና፣ ጥላቻና ንቀት ሁሉ ልዩ ስሜትን ይፈጥራል። ይህ ይወርድና የወያኔ ፖሊሲ ወይም ደግሞ ወያኔ በኤርትራ በሚኖራት ግንኙነት ላይ ጫና ይኖረዋል። እና ይህ ጫና በንግድ ልውውጦች፣ በሚጓዙ ንብረቶች ላይ እንዲደረጉ ቢፈለጉም ማዕቀቦችም የትግራይ ሕዝብ የሚያቀርቧቸውና በየድንበሩ አካባቢ የተፈጠሩ ግጭቶች ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። አንድ ይሄ ነው። ሌላኛው ይኼ የድንበር ግጭት የሚባለው ረጅም ታሪክ አለው። አሁን ዛሬ ይኼ ጦርነት የተፈጠረበት ሁኔታ ቦታ ከአሁን በፊት ELF በትግሉ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ይቆጣጠረው የነበረው ቦታ ነበር።

ከወያኔ ጋር ግጭት ተፈጥሮ ወያኔ ከሻዕቢያ ጋር በመተባበር ELF ከቦታው ወግቶ አስወጥቶ ነበር። ከዚያ ሻዕቢያና ELF ደግሞ ተዋግተው በጠቅላላ ከኤርትር ሲባረር የELF ሙሉ ቁጥጥሩ ማለትም ቦታው ወደ ሕዝባዊ ግንባሩ ማለትም ወደ ሻቢያ ሲዘዋወር ወያኔ በቅሬታ መልክ እያሰማ ያ ቦታ ይገባኛል እያለ ሲጠይቅ ነበር። ግን ከደርግ ጋር በነበራቸው ዋና ጠብ ምክንያት ጥያቄውን ሳያነሱ ቆዩ። አሁን ደርግ ከወደቀና ወያኔ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረና ሻዕቢያ ደግሞ አስመራን ከተቆጣጠረ በኋላ ብዙ ጊዜ በዚያ ቦታ ላይ አነስተኛ የሆኑ ግጭቶች ነበሩ። ለዓለም ሕዝብ አልተገለፁም እንጂ የተደጋገሙ ጦርነቶች ነበሩ። በሁለቱ በኢሳያስና በመለስ ጣልቃ ገብነት ወይም ገላጋይነት እየቆሙ ነበር እንጂ የተደጋገሙ ግጭቶች ነበሩ። እነኚህ ሁሉ እንግዲህ የልዩነቱ መግለጫዎች ናቸው። ባጭሩ እንዳልኩት ነው በኤርትራ በኩል የኤርትራ ሃርነት ግንባር ወይም ከዚያ በኋላ ደግሞ ሻቢያ ሙሉ የኤርትራን ግዛት ከተቆጣጠረ በኋላ

ጥያቄው ተነስቷል። በግልፅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አልቀረበም፣ በግልፅ በዓለም አቀፍ ደረጃ አልታወቀም። የወሰን ግጭቶች፣ ሚሊሺያዎችና ወታደሮች መሃል ብዙ ጊዜ ተደርገዋል። ሆኖም ትልቁ በኤርትራ መንግሥት ደረጃና በኢትዮጵያ መንግሥት ደረጃ ተብሎ እንደዚህ አልታወቀም ነበር። ዛሬ ግን ይሄ የሆነበት ምክንያት አለ። ኤርትራ አስመራ ባለው የሻቢያ መንግስት ከባድ የኢኮኖሚ ችግሮች ተፈጥረዋል። ናቅፋ የሚባለው ገንዘብ ከታወጀ በኋላ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ በኩል ያለው መንግሥት ከእንግዲህ የሚኖረው ግንኙነት የንግድ ግንኙነት በዶላር ልውውጥ እንዲሆን በመደረጉ ኤርትራ ደግሞ ያንን ለመክፈል ስለማትችል በአብዛኛው ለኤርትራ የሚያስፈልጉት የግልጋሎት ዕቃዎች በሙሉ የሚሄዱት ከኢትዮጵያ በመሆኑ ብዙ foreign exchange ያስፈልጋታል። ኤርትራ ደግሞ ከውጭ አገር ለማስገባት አቅሟ አላስቻላትም። ያ ካልሆነ በኤርትራ ውስጥ ከባድ የኢኮኖሚ ችግር ይነሳል። ይኸንን ፖሊሲ ደግሞ በኢትዮጵያ በኩል እንዲከተል ወያኔን የሚያስገድዱት፤

1ኛ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስሜት የሚሰማቸው የራሱ የወያኔ አባላት

2) የትግራይ ሕዝብ፤ ይኼ ፖሊሲ ከመውጣቱም በፊት የኢትዮጵያ ንብረት ወደ ኤርትራ አይሻገርም ሲል የቆየው። 3) የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ይኸንን ፖሊሲ ስለሚገፋው ወያኔ የግል መቀበል አለበት። ወያኔ ይኸንን ከተቀበለው ደግሞ ከኤርትራ ብሔራዊ ጥቅም ጋር መጋጨት አለበት። ይህ እንግዲህ እውነታ ሆኗል። በኢሳያስ በኩል ደግሞ ለኤርትራ ሕዝብ እነዚህን ግልጋሎቶች ወይም ዕቃዎቹን ማቅረብ አለበት። አልተቻለም። ስለዚህ የሚሻለው ነገር ብሎ የወሰደው ቁማራዊ ጨዋታ ምንድነው? ይኼን ጦርነት ማስነሳት ከዚያ ቦታዎችን በመያዝ ስምምነቶች ላይ ለመድረስ መሞከር። የስምምነቶቹን ነጥቦች ደግሞ እነኚህን የኢኮኖሚ ግንኙነቶቹንም የሚያካትቱ እንዲሆኑ በራሱ እዚያ ኤርትራ ወይም አስመራ ሆኖ በመቀመር ያደረጉት ይመስለኛል። እና በአሁኑ ጊዜ ይኸንን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተገለፀውን ጦርነት ለማድረግ ያስገደዳቸው በዋና ነጥቡ የድንበሩ ሳይሆን የኢኮኖሚ ችግሩ ይመስለኛል።

## 3. ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ምን ይጠበቃል?

ይኼ መሠረታዊና ጥሩ ጥያቄ ነው። በአሁኑ ጊዜ ብዙዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶች በሰጧቸው መግለጫዎችም ሆነ ወይም አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖች የሚሰጧቸው መግለጫዎች ይህን ጦርነት የወሰን ግጭት ብለው በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን መካከል ማስቀመጥ ትክክል አይደለም ይላሉ። ከመጀመሪያውኑ ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተለየችበት ሁኔታ ሕጋዊና ትክክለኛ አይደለም እና እነዚህን ድንበሮች ማወቅም የለብንም። ስለዚህ እንደ ድንበር ችግሩን መመልከት የለብንም ይላሉ። በሌላ በኩል ግን ኤርትራ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተባበሩት መንግስታት፣ በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና ባተለያዩ ተቋሞች እንደ ነፃ አገር የታወቀችበት ሁኔታ አለ። እነዚህን ሁሉ ነገሮች ወደ ጐን ትተን ጥያቄውን መመልከት ያለብን ኢትዮጵያ በማንኛውም የውጪ ወራሪ ኃይል ዳር ድንበሯ ቢደፈር አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? የሚለውን ጥያቄ ብንመለከት እና ከዚያ በመነሳት ወደዚህ ለመጠቆም እንችላለን። በዚያ ደረጃ እንየው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያውያኖች የአገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበርና ለዚያም የሚያስፈልጉትን መስዋዕትነቶች ለማድረግ የሚያስችላቸው ሁኔታ፤ አንደኛ፣ ሰብአዊ መብታቸው ተከብሮ፣ ዲሞክራሲያዊ መብታቸው ተከብሮ፣ ኢትዮጵያዊነታቸው በውል ታውቆላቸው፣ ኢትዮጵያ ለሁሉም ዜጐቿ የምታቀርባቸውና የምታደርጋቸው እንክብካቤዎች ለሁሉም ለመድረስ ሲችሉ ነው። ይህም በሚባልበት ጊዜ በግለሰብ ደረጃ፣ በብዙኃን ማኅበር ደረጃ፣ በፖለቲካ ድርጅትነት ደረጃ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለመታወቅና ተቀባይትነን ለማግኘት መቻልና ለሃገሩ ያገባኛል የሚላቸው ሃሳቦቹን ለማቅረብና ለማዳመጥ በሚችልበት ሁኔታ ነው። ዛሬ ያለው ሁኔታ ይህንን አያስችልም። እና ዛሬ ያው ለምሳሌ አቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲደግፉቸው ጥሪ እንዳቀረቡ ይሰማል። ይኸን ለማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ አቶ መለስ ዜናዊ ማድረግ ያለባቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ሙሉ ኢትዮጵያዊነት ተሰምቷቸው ከዚህ መንግሥት ጋር በመተባበር የሚደርሱትን የውጪ ጥቃቶች ለመቋቋም እንዲችሉ ሰብአዊ መብታቸውን ማክበር፣ ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ፤ የታሰሩትን የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት፣ የታገዱትን የፖለቲካ ድርጅቶችን በሙሉ ማወቅ እና እነኚህ ሁሉ አካላት ለኢትዮጵያዊነታቸው ለመሞት እንዲችሉ ማብቃት ነው። ይህ በሌለበት ሁኔታና በተለይ ደግሞ የወያኔ ያለፉትን ታሪክ ከተመለከትን ወዶ፣ ፈቅዶ፣ ደግፎ ላስተናገደውና ላስገነጠለው አገር ዛሬ እንደ ጠላት መጥቶ ወረረኝ ብሎ በኢትዮጵያዊነት ለመቆምና ለኢትዮጵያ ልዑላዊነት ግዛታዊ አንድነት ቆሜያለሁ ቢሉ ብዙ ተደማጭነትን ለማግኘት አይችሉም። ስለዚህ ይህን ሁኔታ በመጠቀም የአቶ መለስ ዜናዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝቦች በኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች መሃል ብሔራዊ እርቅና አንድነት እንዲፈጠርና ለሃገራቸው ዳር ድንበርና አንድነት እንዲቆሙ ለማድረግ መጣር ያለባቸው ይመስለኛል።

# አቶ ማሃሙዳ ጋሃስ

የአፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር

## 1. የግጭትን መነሻ በተመለከተ

የዚህ ግጭት መነሻ በእኔ አስተያየት አጠር ባለ መልኩ ሳቀርበው የኤርትራ አካባቢ ወይም የኤርትራ መንግስት ተብሎ መንግሥት ያቋቋመው የሻዕቢያ አመራር የፖለቲካ ትምክህት የዚህ ግጭት መንስኤ ነው። አዲሳባ ላይ የኢትዮጵያን መንግሥት ሥልጣን ያስጨበጠውን የወያኔን አመራር ላይ ከፍተኛ የፖለቲካ ትምክህት ሲያሳይ ከርሞ ይኼ ምን አስከተለ? ወይም የፖለቲካ ትምክህት ምን አስከተለ የሚለው ጥያቄ ቢነሳ እንግዲህ ለሁሉም የኤርትራ መንግሥት እንደማንኛውም የባዕድ አገር ሁሉ በዛ ዐይን የማየት ሁኔታ በወያኔ አስተዳደር በኩልም በመከሰቱና እርምጃዎች መወሰድ ሲጀምር ያ የኢኮኖሚ ቀውስ በኤርትራ ማስከተሉ ነው። እና በዚህ የተነሳ ሰላማዊ መፍትሔ መፈለግ ወይም ትምክህቱን ቀዝቀዝ በማድረግና ወንድማዊ በሆነ መንገድ ማለትም የሁለቱም አገር ህዝብ አንድነት እና የታሪክ አንድነት የባህል አንድነት መሰረት አድርጐ መልካም ግኙኝነት ለመመስረት ከመፈለግ ሌላ ወደ ወታደራዊ መፍትሔ ያመራው የኤርትራ መንግስት ወይንም በሻዕቢያ የኤርትራ መንግስት ነው። እና እንግዲህ ይህ የሁለቱን መንግሥታት የሚያቀርቡት መረጃ አይደለም። እና መስከ ላይ ሜይ 30/31 የተደረጉት ግጭቶች የአፋር አካባቢ ወሳኝ የሆነ ክልል ነው። በተለይ ኢሮብ ተብሎ የሚታወቀው ትግራይ ውስጥ የአሊቴና ክልል ነው። በዚያ ክልል ላይ የእኛ ግልጽ ሆኖ የታየን ወራሪው የኤርትራ መንግሥት ነው። ስለዚህ ይኸንን የምናየው የሻዕቢያ መንግስት የትግራይን ግዛት መውረሩ ነው። እና ይህ ሁኔታ ከፍተኛ ጦርነት ውስጥ የመግባት ሁኔታ ይታያል፤ ስለዚህ ጦርነት በመግለጫችን እንደሰጠነው ሁሉ ዝሆኖች ሲራገጡ የሚጐዳው ሳሩ ነውና የዚህ ጦርነት ገፈት ቀማሽ የሆነው የትግራይ ሕዝብና የአፋር ሕዝብ መሆኑን ነው የምንመለከተው። ስለዚህ ወራሪውን ማውገዝ እንዳለብን ነው የሚታየን። ከዚሁ አኳያ ነው እኛ አቋም ወስደን ዛሬ የአፋር ሕዝብ ታሪክና አንድነት ያለው ከትግራይ ሕዝብ ነው። ስለዚህ ትግራይ በሚወረርበትም ጊዜ ራሱ የአፋር ሕዝብም በዚህ ጦር ቀማሽ በመሆኑ ይኸንን የሲቪል ያልሆነ ወይም የሰላማዊ ሰው ጉዳት ለማቃለል የሚያስችል እርምጃዎች ለመውሰድ እየተዘጋጀን ነን ያለነው።

በሁሉም ዘንድ የሚታወቀው ይኸንን ሁለት ኃይል የፀረ–ኢትዮጵያ ቃል ኪዳን ኃይሎች ተብለው የሚታወቁ ናቸው። ዛሬ እርስ በርሳቸው ደግሞ ፀብ ፈጥረዋል። በተለይ የአየር ድብደባውን በምናይበት ጊዜ የአዲስ አበባው መንግሥት ዒላማ የሚያደርገው ወታደራዊ ሠፈሮችን ነው፤ የሻዕቢያ መንግስት ጥቃቱን የሚያደርገው በሰላማዊ ሰዎች ላይና በህዝቡ ላይ ነው። የወደቀው ቦንብ የጨረሰው ከት/ቤት የሚወጣውን ተማሪ ነው። እናም ልጆቻቸውን ለማዳን ብለው ወይንም ለማሰባሰብ ብለው ከየቤቱ የሮጡት እናቶች ናቸው በአብዛኛው የተጐዱት፣ የቆሰሉትና የሞቱት። ይህ ጦርነት በአንድ ቦታ የተወሰነ ሳይሆን ከአሰብ 75 ኪሎ ሜትር አካባቢ ድረስ ባሉት ቦታዎች መሃል ጦርነት እየተካሄደ ነው ያለው።

እንግዲህ ይህ ሁኔታ ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ ከተለያዩ ተቃዋሚ ኃይሎች አመራሮች ጋርና ታዋቂ ግለሰቦች ጋር የተለያየ ግኙኝነት እያደረግን ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ የውጪ አገር ወራሪ ይሁን ወይንም የባዕድ አገር ወራሪ  ግን በማን አለብኝነት የተነሳ ኃይል በትግራይና በአፋር አካባቢ ኃይለኛ ጦርነት ከፍተዋል። ዛሬ የዚህ የጦርነት ጉዳተኛው ቀጥታ ሕዝቡ ነው። ስለዚህም የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ርህራሄና ትኩረት መዞር ያለበት ለዚህ ሕዝብና በነሱ መድፍና ቦምብ እየተጐዳ ከሚገኘው ሕዝብ ጋር መሆን እንዳለበት ነው። እርግጥ በእነሱ የጭቆና መሳሪያ የሆነውን ኃይል አካባቢ  አይመለከትም አይደለም። እነሱም ያው የዚህ ሕዝብ ወገኖች ናቸው። ለሆነ አመራር ምናልባት ቢገዙም እንኳ።

ዛሬ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በእኔ አስተያየት በመግለጫችን ያቀረብነውም ጥሪ  ነው መመልከት ያለብን የፖለቲካ ኃይሎች ይነሳሉ፤ ይከስማሉ፤ ግን ሕዝብና ታሪክ ሁልጊዜም ዘላቂ ነው። በመሆኑም ሕዝብና ታሪክ ምንጊዜም ዘላቂ እስከሆኑ ድረስ የታሪክ ባለቤቶች የሆኑት ሕዝቦች በዚህ ቀውጢ ጊዜ አብሮ በመሰለፍ የማቴሪያልም ሆነ የሞራል ድጋፍ የመስጠት ግዴታ እንዳለባቸው የታወቀ ነው። ግጭቱ የሻዕቢያና የወያኔ ግጭት ነው ብሎ እንዲያው ዝም ብሎ መታለፍ የሚገባው ነገር አይደለም። ሰው እየሞተ ነው ያለው። ኢትዮጵያዊ አካል የሆነው የትግራይና የአፋር ህዝብ በነሱ ቦምብ እያለቀ ነው ያለው። ስለዚህ ከዚሁ አኳያ ነገሮችን ተመልክተን ወራሪን ማውገዝና ዛሬ የዚህ ጦርነት ገፈት ቀማሽ የሆነው የትግራይንና የአፋር ሕዝብ ጋር መላው የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ሕዝብ ጀርባ ተሰልፎ ይህንን ወራሪ መመለስ እንዳለብን ነው። በዚህን ጊዜ ታሪክ የሚዘግበው አንድ ነገር ቢኖር የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግራይ ሕዝብ ሲረግፍ ምን አለ? ምን አቋም ወሰደ? ምን ድጋፍ ሰጠ? የሚለውን ነገር ነው። በኤርትራ በኩል ያለው ሕዝብ የዚህ ሕዝብ አካል አይደለም ማለቴ አይደለም።በዛ ሕዝብና በዚህ ሕዝብ መሃል ምንም ልዩነት የለም። በኢትዮጵያ የአንድ ሃገር ሕዝብ ነው። የጐጃም ህዝብ፣ የጐንደር ህዝብ፣ የወሎ ህዝብ፣ የአፋር ህዝብ፣ የሐረር ህዝብ ምንም ልዩነት የለውም የቦታ አከፋፈል ካልሆነ በስተቀር። ስለዚህ ዛሬ የዛንቢያን ህዝብ የሚጨቁነውና ዛሬ መልስ የበለጠ ኢትዮጵያን ለማቀራመት ያላቸው አስተሳሰብ በጣም አደገኛ ነው። ከዚያም አልፎ እነ ኢሳይያስ ትልቁ

ሴራ ወይንም ?? የሚባለውን ሰው ከሰሜን ተወላጆች ላይ ለማስነሳት የሚደረግ ሴራ አለ። በየአካባቢው ያሉ የእነሱ የስለላ መረብ በአካባቢው ግጭቶች ሊያስነሱ ይችላሉ። ይኼ እንዳይሆን በአንድ ድምፅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለመናገር መቻል አለብን። ማንም ከየትም ይወለድ የሰሜን አገር ተወላጅ ነህ ብዬ ነው በአጠቃላይ የምገልጸው። ነገር ግን ተከባብረን የምኖርበት፣ ተማምነን የምንኖርበት አገር ነው እንጂ የምንፈልገው አንዱ ለሌላው ጥቅም ወይንም ያንዱን ሥልጣን ለማጉበጥ ወይንም ለማወፈር ሲባል የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን መገፈፍ የለበትም። ስለዚህ ይኼ ዛሬ የተከሰተው ጉዳይ ታሪክ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ላይ ጣቱን የቀሰረበት ወይንም ያመለከተበት ሁኔታ ነው። እናም የኢትዮጵያ ሕዝብና አገር ወዳድ ኢትዮጵያ ሁሉ ከትግራይና ከአፋር ህዝብ ጐን መነሳት፣ መቆም፣ ማበረታትና ባለን አቅም የሻዕቢያን ወረራ ለመቋቋም የሚደረገውን ጥረት በሚገባ መደገፍ እንዳለብን ነው የሚታየኝ።

በተረፈ ከኢሕአዴግ ጋር ያለን ትግል ደግሞ ይህ ሁኔታ እንደ በረደ መቀጠሉ አይቀርም። በዕርቀ ሰላምም ይሁን ወይንም እስካሁን በተያያዝነው መልክ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን መተማመን በየአካባቢ እንዲኖር፤ ኢትዮጵያዊነት እንዲሰፍን የምናደርገውን ጥረት ይቀጥላል። ግን ማወቅ ያለብን ኢህአዴግ ነገ ለትግራይ ሕዝብ መልሶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአንተ ጋር አልቆመም የሚል መልእክት ለማስተላለፍ እንደሚችል ሁሉ ሰው መገንዘብ አለበት። ስለዚህ ከኢሕአዴግ ጋር ያለንን ቅራኔ ለጊዜው ጋብ አድርገን ሳንረሳ፤ መዘናጋት የለብንም። ግን ዛሬ ይኸንን የጦርነቱን ገፈት ቀማሽ የሆነውን ሕዝብ ማበረታታት፣ የሞራል ድጋፍ መስጠት ሁሉም በአቅሙ መሳተፍ በሚችለው ሁሉ በማድረግና ዋናው ከማንም በላይ በአንድ አንደበት መናገር መቻል አለበት ባይ ነኝ።

---

## ዶክተር ጌታቸው መታፈሪያ

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር

### የጠቡን መነሻ በተመለከተ፤

የሁለቱን አገሮች ችግሮችና ወደ አሁኑ የጠብ ጉዳና የወሰዳቸው ከሁለት አቅጣጫዎች የመነጨ ይመስለኛል።

አንደኛ፣ ከሁለቱ መሪዎች (ከአቶ መለሠና አቶ ኢሣያስ) የአሰራር ሁኔታና የግትርነት ባህሪ የመነጨ ሳይሆን አይቀርም። ምንም እንኳ ስለ ሁለቱ መሪዎች የተጠና ባይኖርም ሁለቱን ሰዎች ??? የተገነዘቡ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ ሁለቱ መሪዎች ዴሞክራሲያዊ የሆነ የአሠራር ሁኔታ የማይከተሉ ማለትም ግትር የሆነ የአምባገነን ጠባይ እንዳላቸው ነው። ለምሳሌ፣ የአቶ ኢሳያስ አንድ ወጥ የፖለቲካ ድርጅት በኤርትራ ማስፈናቸው፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች በኤርትራ አለመፈቀድና ልዩ ልዩ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ድምፃቸው እንዳይሰማ ማድረጉ ይህን የመሪውን አምባገነናዊ ፀባይና የአሠራር ዘዴ የሚያመለክቱ ናቸው።

በኢትዮጵያም አቶ መለስ የዚሁ የአምባገነን ጠባይ ስላላቸው የራሳቸውንና የድርጅታቸውን የበላይነት ለማረጋገጥ ሲሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች በአገራቸው የፖለቲካና የኤኮኖሚ ሂደት ላይ ሙሉ በሙሉ እንዳይሳተፉ ታግደዋል።

እንግዲህ የዚህ የሁለቱን ሰዎች ዓይነት ፀባይ ያለው መሪ ማንኛውንም ፖሊሲ ለማውጣትና ከፍጻሜ ለማድረስ ዲሞክራሲያዊ የሆነ የአመራር ዘዴ አይከተሉም። እንከተላለን ቢሉም በሰከነና የሰፌውን ህዝብ ተወካዮች በቅን መንፈስ በማነጋገር፣ በመምከር ሳይሆን ግልፃዊነት በጐደለውና በተምታታ ሁኔታ ነው። ከዚህ ማለትም በሁለቱ መሪዎች የአሰራር ሁኔታ በተያያዘ የሁለቱ አገሮች ችግሮች መንስዔያቸው በሁለቱ መሪዎችና በድርጅቶቻቸው መሐከል ቀደም ሲል የተዋዋሉትና ህዝብ ያላወቀው ውል ነው የሚባልም ሁኔታ አለ። ያንን ውል አንደኛው ድርጅት ወይም መሪ ሳያከብር እንደቀረ ሁኔታዎች ይጠቁማሉ።

እንግዲህ ከላይ ያስቀመጥኳቸውን ሁኔታዎችን ካመዛዘን፤ ጦርነቱ በኤርትራና በኢትዮጵያ ህዝብ መሐከል ሳይሆን ጦርነቱ በሁለቱ መሪዎችና ድርጅቶች መሐከል ነው ለማለት ይቻላል።

የሚያሳዝነው ግን በሁለቱ መንግሥታት ግፊት በሁለቱም አገሮች የህዝቡ አገራዊነት (Nationalism) እየተቀሰቀሰ ነው። በተለይም በኢትዮጵያ በኩል ይህን አገራዊነት (ኢትዮጵያዊነት) ያዳክም የነበረው ኢህአዴግ ራሱን ለማዳን ሲል ያንን ኢትዮጵያዊነት መቀስቀስ ጀምሯል። ለምሳሌ፣ ሽለላና ቀረርቶ የትምክህተኞች መሳሪያ ነው ተብሎ የነበረው አሁን በኢህአዴግ ሬዲዮ ይደመጣል።

የኢትዮጵያ አገራዊ ምልክቶች እንደ ሰንደቅ ዓላማ፣ ወይም የህዝቡ የአንድነት ታሪኩ ቀደም ሲል ተጠላልቶ የነበረው አሁን ኢህአዴግ ያንን ሐገራዊ ምልክትና ታሪክ ከፍ ሲያደርገው ይታያል።

ሁለተኛው ችግር፣ በኤርትራ ውስጥ የሚታየው የኢኮኖሚ ውጥረት ነው።

ኤርትራ የፖለቲካ ነፃነቷን አግኝታ፣ ባንዲራዋን አውለብልባ፣ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወንበሯን ይዛ፣ ኤንባሲዎችን ከፍታ ልትኖር ትችላለች። ነገር ግን የኤኮኖሚ ነፃነቷን አረጋግጣ መኖር አስቸጋሪ ሆኖባታል።

እንደ ኤርትራ ያሉ ትናንሽ አገሮች ባገራቸው ውስጥ ማምረት ቢያቅታቸው ባላቸው ጥሬ ሐብት (foreign exchange) ከሌላው ሸምተው ሊኖሩ ይችላሉ። ይህንን ለማድረግ ግን የሰው ኃይላቸውን ማሰባሰብ፣ የፖለቲካውን አቅጣጫ ማስተካከል፣ የኤኮኖሚ መሠረታቸውን ማጠናከር፣ የሰከነ አመራር በተለይም ከአጐራባች አገሮች ጋር ሠላምና

የጠበቀ ግኑኝነት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ኤርትራ ውስጥ እነኚህ ሁኔታዎች አልተከሰቱም። በተለይ ኤርትራ «ናቅፋ» የተባለውን ገንዘብ ማውጣት ከጀመረች በኋላና ከኢትዮጵያ ጋር እንደልብ መገበያየት ባለመቻሏ፤ ኢትዮጵያም የአሠብን ወደብ መጠቀም ማቆሟ የአቶ ኢሳይያስን መንግሥት ጐድቶታል።

የኤርትራ ህዝብም ከ5 ዓመት ነፃነት በኋላ ኑሮው እንዲሻሻልለት ይፈልጋል። ከኢትዮጵያ መገንጠል ትርፉ ዜሮ ከሆነ፣ የዕለት ኑሮም እየተወደደ ሲሄድና ተስፋው እየጨለመ ሲሄድ ኑሮ መረረኝ ብሎ ያ ህዝብ አንድ ቀን መነሳቱ አይቀርም። የአቶ ኢሣያስ ወደ ጦርነት ማድላታቸውም እነኚህን ውጥረቶች ለማዘናጋት ነው።

የኤርትራ ህዝብ ከማንኛውም የአፍሪካ አገሮች የተለየ ልዩ ልዩ አገዛዞችን አይቷል። ለምሳሌም፣

1) ከጣሊያን ቅኝ አገዛዝ በፊት የኢትዮጵያ አካል – የባህረ ነጋሽ አስተዳደር ነበር። እንደ ኢትዮጵያዊነቱ የውጪ ወራሪዎችን (ቱርክን፣ ግብፅን፣ ጣሊያንን) ሲታገል ኖሯል።

2) ከዚያም የጣሊያን ቅኝ አገዛዝ ሰለባ ሆኖ ነፃነቱን ተገፎ ኖሯል። በዚያም ስር የትምህርት ዕድሉ ከ4ኛ ክፍል እንዳያልፍ፣ የመኖሪያ ሰፈሩ ተከልሎ፣ የመሻሻል እድሉ ተገድቦ አይቶታል።

3) በእንግሊዝም የሞግዚት አስተዳደር ስር በመኖር ያው የአውሮፓውያንን እብሪተኝነት ተገንዝቦታል።

4) ከዚያም ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ለጥቂት ዓመታት በኋላም የኢትዮጵያ አካል በመሆን ኖሯል። የኢትዮጵያ አካል ሆኖ በኖረበትም ዘመን እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ክፉውንም ደጉንም አይቷል።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንግሥታትም ከሌላው ክፍለ ሀገሮችና ዜጐች የላቀ እንክብካቤ ለኤርትራና ለኤርትራውያን ሰጥተዋል። ነገር ግን የኤርትራ ነፃ አውጪ ድርጅቶች ይህንን እንክብካቤ ሳይገነዘቡ ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የረጅም ጊዜ ትግል አድርገው ነበር።በመጨረሻም ምንም እንኳ ከኢትዮጵያ የመገንጠሉ ሂደት ማለትም የኤርትራ ሬፈሬንደም አጠያያቂ የሆነ ልዩ ልዩ አስተያየት ያላቸው (ለምሳሌ፣ የመገንጠል፣ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን መኖር፣ ወይም የኢትዮጵያ ግዛት ሆኖ መቆየት) ኤርትራዊያንም ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ድምፃቸው እንዳይሰማ፣ ሃሳባቸው እንዳይንፀባረቅ ተደርጐ ኤርትራ ነፃነቷን አገኘች። ኢአህአዴግም ለዚህ ውጤት ትልቅ መሳሪያ በመሆን የኢትዮጵያን አገራዊ ጥቅም ሳይሆን የሻዕቢያን ፍላጐት በሚገባ አሟልቷል። በእነዚህ ሁሉ ታሪካዊ ሂደቶች ውስጥ የተጓዘው የኤርትራ ህዝብ የሚበጀውን ሁሉ በጽንሰ ሀሳብ (በቲዎሪ) ሳይሆን በእውን (ፕራክቲክል) አይቶታል። ችግሩ ምን እንደሆነና መፍትሔውስ ምን መሆን እንዳለበት ግንዛቤ ሊያደርግ ይችላል።

በተለይም ከቅርብ ቀናት ጀምሮ ኤርትራውያንን ከኢትዮጵያ የኢህአዴግ መንግስት እያስወጣቸው ነው። እንግዲህ ይህ ሁኔታ ኤርትራን ለበለጠ ችግር ይዳርጋታል ማለት ነው።

ከእነኚህ ከሁለት አምባገነኖች ባሻገር የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ በታሪክ፣ በባህል፣ በልምድ የተቆራኘና የተሳሰረ ከመሆኑም በላይ የወደፊት እድሉም በዓለም ፖለቲካል ኢኮኖሚና በአካባቢው ጂኦፖለቲክስ የተሳሰረ መሆኑን አውቆ መነጋገር መቻልና ለችግሩ ዘለቄታ ያለው መፍትሔ መሻትና ማግኘት አለበት። ያለበለዚያ ግን በዚያ አካባቢ ሠላም ይኖራል ማለት አጠራጣሪ ነው።

<u>2. ይህ ሁኔታ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል</u>

የወደፊቱን በእርግጥ ለማወቅ ባይቻልም አንዳንድ መላ ምቶች ማስቀመጥና በዚያ ላይ ልዩ ልዩ ሃሳቦችን መሰንዘር ይቻላል።

1) <u>ከኤርትራ በኩል</u>

ሀ) የአቶ ኢሳያስ መንግሥት የጦርነት ጉም በአገሪቷ ላይ እንዣብሏል በማለት በኤርትራ ህዝብ ላይ የበለጠና የጠነከረ ጭቆና ሊያካሂዱ ይችላሉ። የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመጠየቅ መብቶች ... ድጋፍ ከመስጠት በስተቀር ይከለከላሉ።

ለ) የአቶ ኢሳያስ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ መረጋጋት እንዳይኖርና የኢህአዴግ ወታደር ከሰሜን ትኩረቱን ወደ ሌሎች አቅጣጫዎች እንዲያዞር ለማድረግ ሙከራ ማድረጉ አይቀርም።

የፕሮፓጋንዳ ጦርነት በመክፈት (በሬዲዮ) በኢህአዴግ መሪዎች ላይ ፕሮፓጋንዳ መንዛት ወይም የትግራይን ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያውያን ለመለየት መሞከር፣ሌሎች የቀድሞ አጀንዳ ያላቸውን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ማስዘመት፣ከዚያም አልፎ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማዳከም ሙከራ ማድረጉ አይቀርም።

2) <u>ከኢትዮጵያ በኩል</u>

ሀ) የኢህአዴግ መንግስት በዚህ ጦርነት አሳቦ የበለጠውን የንግግር፣ የጽሑፍ ወዘተ እቀባ ማድረጉን ይቀጥላል።

ለ) በዚህ ጦርነት ላይ መንስዔውንም ሆነ ሂደቱን ከጥያቄ ላይ የሚያውሉ ወይም የሚተቹ ሁሉ ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊነታቸውን በጥያቄ ላይ በማስቀመጥ አገር ወዳድነታቸውን ህዝቡ እንዲጠራጠር ያደርጋል።

ሐ) በመጨረሻም ይህ የጦርነት ሁኔታ ካላቆመ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዕድገት ሊገታ ይችላል። ህዝቡ ኢኮኖሚውን ለማዳበርና ኑሮውን ለማሻሻል ዕድል ያጣል።

በተለይም የኢህአዴግ መንግሥት የህዝቡን ሃገራዊነት ስሜቱን በመቀስቀስ፣ የጦር ኦኮኖሚ በመፈጠር፣ ህዝቡ ለዴሞክራሲ፣ ለሠላምና ለልማት የሚያርገውን ትግል ሊያዳክም ብሎም ሊያዘናጋ ይችላል። ሁለቱም አገሮች የኢኮኖሚ ግንባታቸው ሊገታና የውጪ ኤንቨስተሮችን የመሳብ አቅማቸውን ያመነምነዋል። ለዚህ ሁሉ ሰለባ የሚሆነው የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ መሆኑ መታወቅ አለበት።

በተጨማሪም የዚያን አካባቢ አገሮች ፀጥታ ክፉኛ ሊያቃውስ ይችላል። የቅርብና የሩቅ አገሮችም በሁለቱ አገሮች ጋባዥነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁኔታውን ሊያፋፍሙት ይችላሉ።

ይህ ሁኔታ በአስቸኳይ በሠላም ካልተፈታ ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ቅራኔ በኤርትራና በኢትዮጵያ ህዝቦች መሐከል ይፈጠራል።

<u>3. በተቃዋሚ ድርጅቶች ሊያጋጥማቸው ይችላሉ የሚባሉ ጉዳዮች</u>

ተቃዋሚ ድርጅቶች በሁለቱ መሪዎች መሐከል የተከሰተው አለመግባባት ዱብ ዕዳ ሳይሆንባቸው አይቀርም። ሆኖም ተቃዋሚ ድርጅቶች በዚህ አጋጣሚ ትምህርት በመቅሰም የኢትዮጵያ ህዝብ ቋሚ ጥቅም የሚያስጠብቁበትን ሁኔታ በመከተል ጥቃቅን ልዩነታቸውን ማስወገድ አለባቸው።

በእርግጥ በሁለቱ አገሮች መሐከል የተከሰተው ሁኔታ ተቃዋሚ ኃይሎች በዓላማ ባይለያዩም በሥራ አፈጻጸምና በአመለካከት ያላቸውን ልዩነት ሊያጐላው ይችላል።

ኢትዮጵያን ከወራሪ ኃይል ለማዳን፣
– ከኢህአዴግ ጐን እንሰለፍ ወይስ አንሰለፍ?
– ቅድመ ሁኔታዎችን እናስቀምጥ ወይስ አናስቀምጥ?

የሚሉትን መሠረታዊ የአሰራርና የአመለካከት ሁኔታዎች ተቃዋሚ ኃይሎችን ሊያነጋግርና ሊከፋፍላቸው ይችላል።

እኔን እንደሚታየኝ ከሆነ ተቃዋሚ ድርጅቶች እርስ በርስ በመተባበር፣ ኢትዮጵያ ካሉት መሰል ድርጅቶችም ጋር በመተባበር ያለውን ሁኔታ በመተንተንና አማራጭ ሁኔታዎችን ለኢትዮጵያ ህዝብ በተጨበጠ ሁኔታ ማቅረብ ነው።

በዚህ መሐከል ከኢህአዴግ የሚጠበቁ ነገሮች አሉ። ሁሉም ድርጅቶች የፖለቲካም ሆኑ ህዝባዊ ድርጅቶች ያስቀመጡት ጥያቄዎች አሉ። ለምሳሌ የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ፤ የጉሳ ክልል እንዲፈርስ፤ በፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ምንም ዓይነት እቅባት እንዳይኖር፣ የመናገርና የመፃፍ መብት እንዲጠበቅ፣ የታሰሩት ጋዜጦች እንዲፈቱ የሚሉት ናቸው።

ለእነዚህና ለሌሎችም አንገብጋቢ ጥያቄዎች ኢህአዴግ አሉታዊ መልስ ባፋጣኝ ካልሰጠ አሁን በጦርነቱ ምክንያት ያገኘው ድጋፍ እስከ መቼ ድረስ እንደሚቀጥል አጠያያቂ ነው።

ይህንንም ድጋፍ የሰጡት ድርጅቶች የአገርን ህልውና ለማስጠበቅ ነው እንጂ የኢህአደግን ፖሊሲ ባለፉት 7 ዓመታት ሁሉ የተቃወሙና አሁንም የሚቃወሙ ናቸው።

ስለዚህም ኢህአዴግ ከተቃዋሚ ድርጅቶች የቀረቡትን ጥያቄዎች ቅድሚያና ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ግዴታውን የማሟላት ኃላፊነት አለበት።

በሁለተኛ ደረጃ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ በአገራቸው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሂደት ላይ ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ እንዲችሉ አገራዊ የእርቅ ስብሰባ ተጠርቶ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና ህዝባዊ ድርጅቶች በሚገኙበት ከኢህአደግ ጋር መነጋገር አንገብጋቢ የሆነ አገራዊ ጥያቄ ነው።

ይህ ካልሆነ ግን ኢህአዴግ አንባገነንነቱን እየቀጠለበት የኢትዮጵያን ህዝብ በልዩ ልዩ ምክንያት ለጦርነት ሲዳርግ ይኖራል።

የሰከነ አመራር ከሁሉ የፖለቲካ ሰዎችና ድርጅቶች የሚጠበቅ ነው።

---

<u>አቶ ኃይሉ መንገሻ</u>

## የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ትብብር (TAND) ሊቀመንበር

**1. <u>የግጭቱን መነሻ በተመለከተ</u>**

ይህን በሁለት ከፍዬ ለማየት እፈልጋለሁ። የሁለቱ ቁንጮ መሪዎች በአሁኑ ሰዓት ጦርነት ላይ መግባትና በዚያም የኢትዮጵያን ሕዝብ ጦርነት አዙሪት ውስጥ ለመጨመር የሚደርገውን መሯሯጥ በምን ታዩታላችሁ የሚለውና መነሻው ምንድነው የሚለው ነው። እንግዲህ እኔ መነሻው ምንድነው በሚለው ልጀምረውና ከዚያ ወደ ሁለተኛው እሄዳለሁ።

እንግዲህ መነሻው በመሰረቱ ብዙ ሰው እንደሚገምተው የድንበር ችግር ነው። የኤርትራ መንግስት ድንበሩን ማክበር ያስፈልጋል ብሎ በተነሳው መልክ እያየው የሚሄድ ይመስለኛል። ግን ችግሩን እኛ ከዚህ ለየት ባለ መንገድ ነው የምናየው፤ ችግሩ የኢኮኖሚ ችግር ነው። በአሁኑ ሰዓት በሶስት መንገዶች ላይ የተከፈለ የኢኮኖሚ ችግር አለ። 1ኛ) ከአሁን በፊት በኢትዮጵያ መንግሥትና አሁን ኤርትራ ጦርነቱን በማረው መንግሥት በኩል የኢኮኖሚ መረዳዳት ነበረ። በተለይም ወደብን በመጠቀም በዓመት ወደ 2 ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ገቢ ከኢትዮጵያ ብቻ ያገኝ ነበር። ያ አሁን በተከሰተው ልዩነት አልተገኘም። ሌላው በጋዝ ዲፖው ምክንያት ነው። ኤርትራ ብር ሲያስፈልጋት የኢትዮጵያን መንግስት 40% እንዲከፍል ጠየቀ። እነሱ ደግሞ ከለከሉ። በዚህ ምክንያት የመጀመሪያው ኩርፊያ ተጀመረ። 2ኛ) በኤርትራና በኢትዮጵያ የነበረው የሚሊተሪ ግኑኝነት ሳልቶ በሱዳን በኩል በነበረው ጦርነት ኢትዮጵያና ኤርትራ ወግነው ሲዋጉ ከቆዩ በኋላ የመለስ መንግሥት ፖሊሲውን ቀይሮ እንደገና በደቡቡና በሰሜኑ የሱዳን ጦርነት አስታራቂ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ሁለተኛው ኩርፊያ ተነሳ። 3ኛ) የኤርትራ መንግስት አዲሱን የናቅፋ ብር አዘጋጅቶ አንድ ናቅፋ በአንድ የኢትዮጵያ ብር ለመቀየር ሲዘጋጅ የመለስ ፖሊሲ ከዲሴምበር 1997 ስብሰባ በኋላ ፖሊሲውን በመቀየር በኢንተርናሽናል ከረንሲ ብቻ መቀየር እንደሚቻልና ዶላር እንደሚዲየም እንዲሆን በተደረገው ምክንያት ሦስተኛው ኩርፊያ ሆነ። በዚያም ምክንያት የኢኮኖሚ ውጥረት እየባሰ ሲሄድ የጠላት መንግሥት ነገሮችን ለመተንኮል ሲባል ከአሁን በፊት ሲነሳና ሲወድቅ የነበረውን የድንበር ጉዳይ አስነስቶ ያው የመጀመሪያውን የወረራ ክስተት ጀመረ። እንግዲህ ሁለቱም መሪዎች የሚጣጣሙና የሚተጋገዙ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሁለት በኩል እንደፈለጉት ሲያደርጉት የነበሩ ኃይሎች ናቸው። ግን የብር ነገር በሚነሳበት ጊዜና የኢኮኖሚ ውጥረት በሚበረታበት ጊዜ ሁለቱም የየራሳቸውን ጥቅም የማየት ሁኔታ ሲያደርጉ ያው ጦርነቱን ጀመሩት ማለት ነው።

ለነገሩ ይኸ የድንበር ጉዳይ ከአሁን በፊትም ሲነሳም ሲወድቅም የነበረ ነገር ነው። በተለይ ከ1975 በፈረንጅ ጀምሮ የትግራይ TPLF እንቅስቃሴ በሽሬ አካባቢ በሚጀምርበት ጊዜ በዚያን ጊዜ የነበረው ELF ድርጅት አንዳንድ ችግሮች TPLF ጋር በሚኖርበት ጊዜ ለምሳሌ TPLF ከኢህአፓ ጋር በሚያብርበት ጊዜ፣ TPLF ከEPLF በሚያብርበት ጊዜ ያን ቦታ ሲቆጣጠረው ስለነበር ብዙ ጊዜ የድንበርን ጉዳይ እያነሳ ነገር እንደመሣሪያ እያደረገ ይጠቀምበት ነበር። ስለዚህ ይኼ የድንበር ጉዳይ አሁንም እኛ የምናየው ጊዜያዊና የሌሎቹ ችግሮች መባባስ በታየበት ጊዜ እንደመነሻ የሚሆን እንጂ እውነተኛ የድንበር ጉዳይ ሆኖ አይደለም። አሁን ያለውን መሬት ከወላጆቻችንም አያቶቻችንም በፊት የትግራይ ግዛት አስተዳደር ነው የነበረው። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በነመለስና በነኤርትራ ሕዝብ በተደረገው የድንበር መከለል ደግሞ ምንም እንኳን ባይካለሉትም እንደ ትግራይ መሬት ሆኖ በኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ የነበረ ነው።

**<u>የሚመሩት ድርጅት (TAND) የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ትብብር ሊኖረው ስለሚችለው ሚና</u>**

እንግዲህ መቸም በእውነት ከተነጋገርን የኤርትራም ህዝብ ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈልጉትም ሆነ

ሳይፈልገውም የሚመጣ ጦርነት አይደለም። በሦስተኛው ዓለም መቸም አንድ ቁንጮ መሪ ካለ የፈለገውን ውሳኔ ያደርጋል። ሕዝቡ ሳይወድ እሳት ውስጥ ይማገዳል። አሁንም የተፈጠረው ሁኔታ ይኸ ነው። እርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመጀመሪያውም ቢሆን የኤርትራ መለየት ወይም ደግሞ የኤርትራ መገንጠል ጉዳይ ያልተካፈለበት ስለሆነ ከመጀመሪያውም ሲጠይቀው የነበረ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም የመለስ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ አላማከረም፣ ሪፈረንደም አላደረገም። ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ነገሮችን ሥራ ላይ ማዋል አልቻለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ ለዓመታት ለመቶ ዓመታት አብሮ የኖረ ነው። ፍላጐቱን እንኳ እንዲጠየቅ አልተደረገም። ስለዚህ የመለስ መንግሥት ራሱ ፈልጐ የፈረመው ስለነበር የኢትዮጵያ ሕዝብ አልተካፈለበትም። ሆኖም በአሁኑ ሰዓት የኤርትራ መንግሥት ሆኖ ከታወቀ በኋላ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቀረውን ሕዝብና መሬት ይዞ ደግሞ ያለውን ድንበር ማስከበር ደግሞ መብቱ ነው። ማስከበር ብቻ አይደለም ለድንበሩና ላገሩ መሞት ደግሞ የሚገባው ነው። ስለዚህም በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም የትግራይ ህዝብ፣ የአፋር ሕዝብ በድንበሩ አካባቢ እየተዋደቀ ነው። በዚህን ጊዜ የፖለቲካ ድርጅቶች ምንግዜም የፖለቲካ ልዩነት ቢኖራቸውም አሁን የአገር ማዳን ጉዳይ እስከሆነ ድረስ አብረው ተሰልፈው ወራሪን ኃይል መግታትና መቋቋም ያለባቸው ይመስለኛል። እንግዲህ ባለፉት ሰባት ዓመታት በተለይ የመለስ መንግሥት ከመጣ ወዲህ በክልል የተመሰረተ ፖሊሲ በማዋቀር የኢትዮጵያን ህዝብ ሲያተራምሰው መቆየቱ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ይህን ስል ግን ከአሁን በፊት ለ17 ዓመታት ሲገዛ የነበረው የፋሺሽት መንግስት ጥሩ ነበር ማለት አይደለም። ለ17 ዓመት ፋሺዝምን የኢትዮጵያ ሕዝብ በፈለገው መንገድ አብሮ ተሰልፎ እንደተቋቋመ ሁሉ ይኸንን በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጣውን የመለስን መንግሥትና ፖሊሲ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲቋቋም ቆይቷል። እንደ አሸን የፈሉ ድርጅቶችም በየጊዜው ተፈጥረው ሲታገሉ ቆይተዋል። አሁን ግን፣ ያለንበት ጊዜና ወቅት ድርጅቶች ተለያይተው የየራሳቸውን የፖለቲካ ሂደት ብቻ የሚያስፋፉበት ብቻ ሳይሆን አገርን የሚያዝሉበት ሁኔታ ስለሆነ ሁሉም ድርጅቶች በነመለስ ቋንቋ ትግሬ፣ አማራ፣ ምናምን ሳይባል ሁሉም አብሮ ተባብሮ አሁን ያለውን ወራሪ መጋፈጥ አለበት። በአገር ውስጥ የሚታገሉት የኢትዮጵያ ሠራዊትም ይህንን ተመልክተው የኢትዮጵያ ህዝብ ከጐናቸው እንደሆነ ማወቅ ይኖርባቸዋል። በሕሊና ሁሉም ከነሱ ጋር እንደሆነ እነሱም እንዲያውቁ ይገባል። ግን ያን ካደረጉ በኋላ ቤታቸውን ማፅዳት ደግሞ ይኖርባቸዋል። የመለስ መንግሥትና የመለስ ፖሊሲ ነው ይህን ሁሉ ችግር ያመጣብን የመለስ መንግሥት ደግሞ መወገድ ይኖርበታል ማለት ነው።

---

## ዶ/ር ሙሉጌታ ሥዩም

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት

### 1. የግጭትን መነሻ በተመለከተ

ይህንን ዕድል ስለሰጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ። ይህ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተው ግጭት ብቸኛ በተናጠል የደረሰ አይደለም። ባለፈው 7 ዓመታት ውስጥ በአገራችን ውስጥ የተከሰተው አጠቃላይ ችግር የሕወአት/የኢኅአደግ አመራር ያመጣው ችግር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚህ በፊት በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የፖለቲካ እስረኞች ሲታሰሩ ለምሳሌ፣ እንደ ፕሮፌሰር አሥራት፣ አቶ አበራ የማነአብ፣ ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት፣ ፊታውራሪ መኮንን ዶሪ የመሳሰሉትን የፖለቲካና የሲቪክ አሶስየሽን መሪዎች የታሰሩት በዚህ ፖሊሲ የተነሳ ነው። እነ አሰፋ ማሩ የተገደሉት በዚህ የተነሰ ነው። ከአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሥራ የሚባረረው፣ የሃይማኖት ቦታዎች የተደፈሩትና ምዕመናን የተገደሉት በዚህ የተነሳ ነው። ይህ በአጠቃላይ በአገራችን ውስጥ የደረሰው ችግር ዛሬ በሰሜን ኢትዮጵያ በሕወሐትና በሻቢያ ጦሮች መካከል የተደረገው ግጭት የዚያ ውጤት የዚያ አካል እንጂ ብቸኛ አይደለም። እና ይህን ነገር በዚህ መልኩ መልኩ የተከሰተው በተለይ ይህንን ብቻውን ስንመለከተው የሻዕቢያ የኤርትራን የተቆጣጠረው ኃይል እንደልቡ የኢትዮጵያን ማናቸውንም ሁኔታ በቁጥጥር ስር አድርጐ የራሱ ኢኮኖሚና የራሱን መንግሥት የሚያጠናክርበትን ሁኔታ በመጀመሪያ በሁለቱ ኃይሎች ስምምነት የተነሳ የነበረውን ዕድል – ያንን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ነገር እንዳይሆን ማድረግ ሲጀምር በራሱ መቆም ያልቻለው የሻዕቢያ ኃይል ያው ኢትዮጵን መውረር ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ የፈለገውን ማድረግ ተገደደ። እና ይህ ዛሬ የተከሰተው ችግር ብቸኛ አይደለም። በጠቅላላ አገራችን የደረሰው ችግር ውስጥ አንዱ አካል ግን መልኩ ደግሞ እጅግ የመረረና የከፋ መሆኑን ደግሞ የማይካድ ነው። እዚህ ላይ አንድ ነገር መጠቀስ ያለበት ይመስለኛል። የሻቢያ ጦር በሰላማዊ ሕዝብ ላይ፣ በት/ቤት ላይ፣ ስደተኞችና የተፈናቀሉ ሰዎች ባሉበት አካባቢ ቦምብ በመጣል በየትኛውም ክፍል አገር ደርሶ የማያውቅ እጅግ አሰቃቂ ጥፋት እያደረሰ ነው። ይኸንን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በየትኛውም ክፍል ያለ ሁሉ ሊቃወሙ የሚገባ ይመስለኛል።

በእኛ በኩል ይኼንን ችግር የምንመለከተው በአጠቃላይ ከአገሪቱ ላይ ከደረሰው ችግር ጋር አጣምረንና አያይዘን አንድ አካል አድርገን ስለምንመለከተው ለውጥ ሊመጣ ይችል ዘንድ መላው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያቅፍ፣ የሚያወያይ የሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶችን ተሳትፎ የሚጠይቅ ውይይት መደረግ አለበት ብለን እናስባለን። ይህ እውን ይሆን ዘንድ የሕወሐት ወያኔ መንግስት በሩን መክፈት አለበት። ከዚህ በፊት ያገዳቸውን የፖለቲካ ድርጅቶችን እገዳውን ማንሳት አለበት። እንደልባቸው አገራቸው ውስጥ ገብተው ሃሳባቸውን ሊያስተላልፉና ሊያሰራጩ የሚችሉበት ሁኔታ መክፈት አለበት ብለን እናምናለን። የፖለቲካ እስረኞች ከላይ የጠቀስኳቸውና ሌሎችም ሁሉ መፈታት አለባቸው ብለን እናምናለን። ጋዜጠኞች እንደልባቸው ሃሳባቸውን ለሕዝብ ማቅረብ፣ እውነቱን ለሕዝብ ማሳየት መቻል አለባቸው ብለን እናስባለን። ይህ ከሆነ የአገራችን ችግር ሊፈታ ይችላል ብለን ስለምናምን እንዲሁ ዛሬ በዚች ባጋጠመው ችግር በግጭቱ ላይ በጦርነቱ ላይ ብቻ ካተኮርን እንደገና ሌላ ችግር ውስጥ ሌላ ጣጣ ውስጥ የምንገባ ይመስለኛል። ይኸንን ችግር እንድንፈታ የሕወሐት/የወያኔ መንግስት በሩን ከፍቶ ሁሉንም ኢትዮጵያውያንን ሊያሳትፍ የሚችል ሃገራዊ ውይይት ሊደረግ የሚችል ሁኔታ መፈጠር አለበት ብለን እናምናለን። ያ ሲሆን ችግራችን በሙሉ ይፈታል። ያ ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ በፊት ያደረገውን

መስዋዕትነት ከፍሎ አገሩን ድንበሩን ያስከብራል፤ ክብሩን ያስጠብቃል፣ የተገፈፈው ነፃነቱንና ትልቅነቱን እንደገና ይላበሳል ብለን እናምናለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን ድንበሩን ነፃነቱንና ማንነቱን ለማስከበር ከመንግሥት በተጣለበት እገዳ መሰረት ተቸገረ እንጂ መቸውንም በታሪክ ያረጋገጠውን ጀግንነቱን ዛሬ ለማረጋገጥ የሚያስቸግረው ነው ብለን አናምንም።

በእኛ በኩል ይህ በአገራችን ላይ የደረሰው ካለፉት 7 ዓመታት እስካሁን ድረስ የሚታየው በደል አንድ መለኪያው ነው ብለን ስለምናምን፤ ይኸም ከላይ እንደጠቀስኩት በሕወሐት ፖሊሲ አመራር ጉድለት የመጣ ነው ብለን ስለምናምን ይኸን ነገር ልንፈታው የምንችለው ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን። ዛሬ አገራችን ውስጥ ደረሰው በደል ማናችንንም፣ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የምንኖር፣ በየትኛውም የሥራ መስክ የተሰማራን፤ በከተማም ሆነ በገጠር የምንኖር፣ ወጣቶችም ሆነ አበውን ሁሉ የሚነካ ነው። የትኛውንም የኃይማኖት ተከታይ የትኛውንም ቋንቋ ተናጋሪ የሚነካና የጉዳ ስለሆነ ሁላችንም መተባበር አለብን ብለን እናስባለን። እዚህ ላይ በተለይ በዚህ አካባቢ ከሁኔታው ራቅ ብለን ያለን ለጊዜው ማና የሌለብን የመንግስት ቁጣና ብትር የማይነካን ኃይሎች ደግሞ የተሻለ መስራት እንችላለን። ይኸውም አንድነታችንን፣ ሕብረታችንን አጠናክረን ባንድ ጥላ ሥር መጥተን አብረን ልንሰራ የምንችለውን ተነጋግረን የምንመራበት መመሪያ አውጥተን በአንድ ቃል ባንድ ድምፅ መናገርና መሥራት እንችላለን ብለን እናምናለን። እዚህ ላይ ይኼ አገራችን ሕልውናው እየተናጋ በተለያየ መንገድ እየተቦረቦረች ባለችበት ሰዓት ላይ በተለያዩ የአስተሳሰብና የፖለቲካ ልዩነቶች የተነሳ አብረን ልንሰራ ወደ ኋላ የምንል ካለን እጅግ ተሳስተናል። ተመክሮአችን እውቀታችን ንብረታችን ሁሉ ሳይቀር አቀናጅተን ባንድ ላይ ልንቆም ባንድ ቃል ልንናገር ይገባል። ያ ሲሆን ጠላቶቻችን ያዳምጡናል። ያ ሲሆን ሕዝባችን ያዳምጠናልና ይደግፈናል። ያ ሲሆን የውጪ አገር ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ የሚያደርጉት እነማን እንደሆኑ ያውቁናል ያዳምጡናል እና ሃሳባችንንም በአግባቡ ሚዛን ይሰጡታል።

ስለዚህ ዛሬ እኛ በውጪ ያለን ኃይሎች ከብዙ ችግር ወጣ ብለን ያለን በሰፊው ለመወያየት የሚበጀንን ፈልገን ለማግኘት የሚያስቸግረን አይደለም። ይህንን ግን በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ኋላ የምናደርግ ካለን እጅግ የተሳሳትን ብቻ ሳይሆን ላገራችን ጥፋትና ለወገናችን ድክመትና በደል አስተዋጽኦ እናደርጋለን፤ ባንወደውም ባናምንበትም ያንን እያደረግን ነው።

ስለዚህ የእኛ ጥሪ እባካችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን በያላችሁበት የሚቻላችሁን አድርጉና ኃይላችንን አስተባብረን ባንድ ላይ እንቁም ነው የምንለው።

---

# ኮማንደር አሰፋ ሰይፉ

## 1. የግጭትን መነሻ በተመለከተ

አሁን አገራችን ያለችበት ግጭት ላይ አይደለም፤ ጦርነት ላይ ነው። ሳይደግስ አይጣላም የሚባለውም ሆነ እግዚአብሔር መቸም ምንጊዜውም ኢትዮጵያን አይጥላትምና ደርሶላታል። ሊያስችል የሚችል ሁናቴ ተፈጥሯል ካወቅንበት። ካወቅንበት ለደኅንነታችን ዓይነተኛ ሁኔታ ተፈጥሮልናል፤ ካላወቅንበት ደግሞ ቂምና በቀልን ነቀርሳ አድርገን ሰውነታችንና አስተሳሰባችን ከመረዝን የጥፋታችን ሁኔታ ይቀጥልብናል። እኔ በአጭሩ የማየው ለደኅንነትም ለጥፋትም መሃል መንገድ ላይ ነን ያለነው።
እንዲያውም ቀጭን መንገድ ላይ ወደቀኝም ቢባል ገደል ወደ ግራም ቢባል ገደል ካወቅንበት ቀጥ ብለን አልፈን ደህንነታችንን ለራሳችንም ለወገናችንም ለትውልዳችንም በኩራት የምናስተላልፍበት ወቅት ነው።

በመጀመሪያ እስቲ አቶ መለስ ያስተላለፉትን መልእክት ነካ እናድርገው። ክተት ነው አይመስልም። ድረሱልኝ ነው አይመስልም። ወሬ ነው ያወሩት። ባሁኑ ጊዜ አገር ስትጠፋ በግራና በቀኝ ከኋላና ከፊት በውጥረት ባለችበት ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለበትን ሁናቴ አፍረጥርጠው እንዲህ ያለ አደጋ ላይ ነች ያለችውና ኢትዮጵያዊ የሆንክ ሁሉ ተነስ ታጠቅ እርዳ ደግፍ ማለት ሲገባ እንዲያውም ?? እንዲህ ሆነ ከእንዲህ ዓይነት ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ የአሰላለፋን ድክመት የሚያሳይ ይስለኛል። ሆኖም ጦርነቱ ላይም መለስ ብንል አይሮፕላን የመታው ባዶ አየር ማረፊያ ነው። የወታደር መኖሪያ ያለበት ግልጽ ነው። የአሜሪካን ቃኘው ሻለቃ የነበረበት ከዚያም አካባቢ ሁለት የታወቁ ቦታዎች አሉ። መጀመሪያ ቀን ምናልባት አንዳንድ መረጃ ኖሮት ወይም ከውጪ አይሮፕላን የሚመጣ መስሏቸው ከሆነ ያደረጉት የማላውቀው ነገር ነው። ግን እንደገና ድጋሚ ለማጥቃት ሲሄድ ለጠላት አስጠንቅቆ ጠብቁኝ ብሎ የወገንን ሃብትና ነጂና ሃብት አደጋ ላይ መጣል ነውና ስለዚህ በአመራሩ ላይ አዝናለሁ። ምንም እንኳ በአንዳንድ መልክ መለስ ስልጣኑን የነበረውን ያህል የሌለው መሆኑን ግልጽ ማስረጃዎች ብናይም ሊያጠፋ የሚችልበት ቦታ ላይ ስለሆነ እስባለሁ። እሰጋለሁ።

ቀደም ሲል የጥላቻና የቂም ነቀርሳ ካላጠቃን በስተቀር በምልበት ጊዜ አንድ ትውልድ በሕይወቱ ውስጥ 3 ጊዜ እንዳይሳሳት ለማለት ነው። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ ላይ ፍፁም ሥልጣንን ለምክር ቤት ይሰጥ የሚል ሃሳብ ስናቀርብ ብዙዎቹ አልመሰላቸውምና አልተቀበሉትም። በዚህም ምክንያት ለምን እንደተዳረግን ታውቃላችሁ። በደርግ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ ደግሞ ያንድ ሰው ጥላቻ አገሪቱን አጠፋ በማለት ስንወተውት አሁንም መንግሥቱን እንርዳ ነው የምትሉት? ደርግን እንደግፍ ነው የምትሉት? በሚል አስተሳሰብ የሚቀበለን ጠፍቶ አገራችን ይኸው ውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ ላይ ጥሏታል። እኛ በአሁኑ ጊዜ የምንረዳው የምናድነው ኢትዮጵያን ነው። ምክንያቱም በደቡብ እንገንጥል ባዮች ምን ያህል እንዳሉ እናውቃለን። በምሥራቅ እንገንጥል ባዮች ምን ያህል እንዳሉ እናውቃለን። በሰሜን ኢትዮጵያ የምትባል አገር ከአሥር ዓመት በኋላ አትኖርም የሚል ዛቻ እንዳለና በአሁኑም ጊዜ ደግሞ ያንን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ ይመስላል። በዚህን ጊዜ እኛ ልናተኩርባቸው የሚገባን ብዙ ነገሮች አሉ። ገንዘብ ለመስጠት አይደለም። ገንዘብ የሚሰጥበትና ገንዘብ የሚውልበት ብዙ ቦታ አለ። ሕዝባዊ ደጀን እንዲፈጠር ካልተደረገ ይህች አገር አደገኛ ሁኔታ ላይ ትወድቃለች። በግንባር ያሉት የአፋርና የትግራይ ወገኖቻችን በጥሩ ኢትዮጵያዊነት ጀግንነት ትግላቸውን ቀጥለዋል። ግን ባለው ሁናቴ ያ ግንባር ቢፈርስ ጠላት ዝም ብሎ በወሎም በሸዋም በጉጃምም በጎንደርም በኩል ሊገሰግስ ነው። እንዲህ እንዳይሆን ሕዝባዊ ደጀን እንዲፈጠር አስፈላጊውን ተፅእኖና አስፈላጊውን አስተዋጽኦ ለማደርግ የምንችለው የገንዘብ ኃይል ሲኖረን ነው። ይህን የወገን ኃይል ለማግኘት የምንችለው ከወገን ነው። ባለፈው የመረብ ምላሽ ተወላጆች ለንደን ተሰብስበው ባንድ ቀን ያውም ሁሉም

አይደሉም ጥቂቶቹ ተሰብስበው ወደ 15,000 ዶላር በላይ አዋጡ። አነስተኛ ያዋጡት ከ150 ዶላር በላይ ነው። ለምን አገራቸው እንድትስፋፋላቸው ፈልገው ይሆናል፤ እኛ ግን ያችን እናት ኢትዮጵያን ለማዳን የት ይሄዳል የት አይሄድም አይደለም ማለት ያለብን። ማንም ሰው ቢሆን አሁን ለኢትዮጵያ ሕልውና ለታሪካችን መቀጠል ለትውልድ ኃላፊነት ያለበት ሁሉ መረባረብ አለበት። ለዚህ ይውላል ለዚያ ይውላል ብዬ ዝርዝር ውስጥ ልገባ አልችልም። ምክንያቱም ያንን ነገር ማጨናገፍ ነው። ለጠላት ማስጠንቀቂያ መስጠት ነው። ስለዚህ ሁሉም ይተባበር፣ ሁሉም ያውጣ፣ ሁሉም ይርዳ። እስቲ አማራ በቀረው ግዛት ሲዋጋ አንድ ዶላር ሰጥቶ አምስት ዓመት ያግል አለ። ይኼ አይሁን። ስለዚህ በወንድሞቻችን፣ በእህቶቻችን በትግል ላይ በተሰማሩት እምነት ይኑረን ፤ ድጋፋችንን እንንሳ።

## ፕሮፌሰር ንጉሤ አየለ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሣይንስ ምሁር የነበሩ

ፕሮፌሰር ንጉሴ፣

እንግዲህ በመሰረቱ ከሁሉ በፊት አንድ ነገር ማለት አለብኝ። ይኸውም ምንድነው ይኸ አሁን ባለፉት ሁለት ወራት አካባቢ ሲካሄድ የቆየው ግጭት በኢትዮጵያና ኤርትራ ሕዝብ መሃል ያለ ግጭት አይደለም። በምንም በምንም መልኩ በሕዝቡ መሃል ያለ ግጭት አለመሆኑ መታወቅ አለበት። ኢትዮጵያ ኤርትሪያ እየተባለ ቢነገርም ይኼ በመሰረቱ በሻዕቢያ ኤርትሪያና በወያኔ ትግራይ ገዥዎች መካከል ያለ ግጭት መሆኑን ነው በመጀመሪያ መታወቅ ያለበት።

ይህንን በመጀመሪያ ካላወቅን ብዙ ስህተቶች ውስጥ መግባታችን አይቀርም። ይኸን ካልኩ በኋላ በሁለተኛ ደረጃ ይኼ ግጭት የወሰን ግጭት ነው እየተባለ ሲነገር ቆይቷል። ችግሩ እንግዲህ ወሰን የሚባለው ነገር ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ነው ይሄን የምልበት ምክንያት ምንድነው፤ አንድ ወገን ወደ 46,000 እስኩየር ማይልስ መሬት አንስቶ ለሌላው ወገን ከሰጠ በኋላ ወይም ያን እንዲያገኝ ወይም እንዲኖረው፤ ያለ ምንም ክርክር፣ ያለ ምንም ጭቅጭቅ፣ ያለ ምንም ንትርክ እንዲያገኝ ካደረገ በኋላ አሁን በአንድ መቶ ሃያ እስኩየር ማይልስ ላይ ግጭት መፍጠር ማለት ምን ማለት ነው? 46,000 እስኩየር ማይልስ ያገኘውስ አሁን ይህቺ አንድ መቶ ሃያ ማይልስ እስኩየር ቀረችብኝ ማለትስ ያዋጣዋል? ደግሞስ 46ሺ የሰጠው ወገን ይህቺን መቶ ሃያዋን ግን አትንካብኝ ማለቱስ ምን ይባላል? ይኼ መቸስ ትልቁ እንቆቅልሽ ነው። ስለዚህ ነው በእኔ ግምት የእኔ ብቻም አይደለም፤ ብዙ ነገሩን ጠለቅ አድርገው የሚያዩ ሰዎች በምንም ዓይነት የወሰን ግጭት ወይም ችግር ነው ተብሎ ሊወሰድ አይገባም የምንለው።

እንግዲህ ይህ የወሰን ወይም የመሬት ይኼ ይገባኛል፣ ይኼኛውን አልፈሃል የማለት ሳይሆን ይኸንን ጠብ የጫረው ሌላ ነገር መኖር አለበት ብሎ መጠየቅ መቼም ተገቢ ነው። ነገሩ ይህን ያመለክታልና። እንግዲህ በመጀመሪያ በጦር ኃይል ነገሩን የጫሩት የሻዕቢያ ኤርትሪያ ገዥዎች እንደመሆናቸው መጠን ሁኔታውን ለመመርመር ስንጀምር ለምን ይኸንን ጠብ በአሁኑ ጊዜ ጫሩት? ለምንስ በዚህ ቦታ ጫሩት? ብለን ስንጠይቅ እንዲያው አጠር አድርጐ ለመግለፅ አንድ ሦስት አራት ምክንያቶች ግልጽ የሆኑ ይመስለኛል።

አንደኛው፣ በዮሴፍ ጊዜ እንደነበረው ፈርዖን የሰባት ዓመት የጥጋብ ዘመን ሻዕቢያ ኤርትራውያኖች የኢትዮጵያን ሕዝብ አጥንት እየጋጡ ጊዜያቸውን ካሳለፉ ከሰባት ዓመታት በኋላ ይኼ ናቅፋ የሚባል የሞኖፖሊ ወረቀት ገንዘብ ዓይነት አውጥተው ልክ በብር ሲጫወቱ እንደነበረው አሁንም ቀጥለን እንጫወት ቢሉ ይኼ አገዛዝ ሳይሆን ሕዝቡ አመፀ፤ እንቢ አለ። በተለይ ትግራይ ውስጥ ያለው ሕዝብ አመፀ። በዚህ ምክንያት የሰባቱ ዓመት የጥጋብ ዘመን አበቃና አሁን ወደ ሰባት ዓመት ረሃብ ዘመን መተላለፍ እንደሚኖርባቸው እየተረዱ ሄዱ። ይኼንን ችግር፤ ይኼንን ነገር ለመሸፈን «ብልጥ ልጅ እየበላ ያለቅሳል» በሚለው መርሆ ችግር ያለባቸውና ችግራቸውን ኢትዮጵያ ወይም የኢትዮጵያ ወገኖች ከበረቱም ወዲህ ወደ ደቡብ ያለው ክፍል ችግር ውስጥ አስገባን ለማለት እንዲመቻቸው ብለው የጫሩት አንደኛው ምክንያት ይመስለኛል። ኢትዮጵያን መውቀስና በኢትዮጵያ ላይ ሁሉን ነገር ማማረር መቸም ላንዳንድ ወገኖች በጣም ጠቃሚ ስለሆነ ይሄ አንዱ ምክንያት ነው የሚል ነገር ነው።

ሁለተኛው፣ ቀደም ሲል የአንድ ተቃዋሚ ስብስብ እንዳለው «ሌቦች የሚጣሉት ሲሰርቁ ሳይሆን የሰረቁትን ሲካፈሉ ነው» እንደተባለው ሁለቱም የሚጣሉትና የሚጋጩት ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ሃብት ላይ ነው። አሁን እንግዲህ ምን የቀራቸው ነገር እንዳለ፤ ወይም ምናልባት ከዚህ ቀደም እንዳቸው ለአንዳቸው የገቡት ቃል ኪዳን እንዳለ አይታወቅም፤ ሊኖር ይችላል። ያኔ ስልጣን ስንይዝ ይኼ ላንተ ይኼ ለእኔ ይሆናል ያሉት ነገር ምናልባት ዛሬ ሳይሳካ ቀርቶ ያንን ለማሳካት ሲሉ የጫሩት ጠብ ሊሆን ይችላል።

ሌላው በእርግጥ የወያኔ ትግራይ ገዢዎች የሻዕቢያ ኤርትራን ወገኖች ብዙ አቀማጥለዋቸዋል፤ አማግጠዋቸዋል። ብዙ ብዙ ከሚያስፈልገው በላይ፤ ... እና እንደዚህ ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ ምናልባት አሁን ከዚህ ከናቅፋ ሁኔታ በኋላ እንቦጭ አደርጓቸው መስሏቸው ይሆናል። ወይ አለማቀማጠል ነበር ካቀማጠሉ ደግሞ መቀጠል ነበር። ሻዕቢያም እስካሁን ድረስ ሲደጉሙን ቆይተው አሁን በናቅፋው ጊዜ እንዴት ይከዱናል ብለው ይሆናል። ይኸ ደግሞ ሕዝቡ እንገፍግፎት በቃኝ ብሎት ያቆመው ነገር ነው። እንዲያውም አዲስ አበባ ያሉት ገገርዎች የሕዝቡን እሮሮ ተከተሉ እንጂ የመሩት ነገር የለም፤ በተለይ በዚህ ጉዳይ ላይ። እንግዲህ በሌላ በኩል ይኼ ግጭት ከተጫረ በኋላ ሁለቱም ወገኖች ለፖለቲካ ጥቅም የሚጠቅም ሆኖ አግኝተውታል። ሻዕቢያም በበኩሉ ብዙ ችግር አለው፤ ብዙ ተቃዋሚዎች አሁንም አሉበት። አዲስ አበባ ያለውም የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊነት ሁልጊዜ በጥርጣሬ ላይ እየወደቀ እንዳለ ሥሆኑ ግልፅ ነው። እንግዲህ ይህ ግጭት ለሁለቱም ገዢ ወገኖች ምናልባት ለራሳቸው የተደላደለ ሁኔታ ላይ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ይመስለኛል። እንግዲህ ዋናው ነጥቤ ምንድነው ጠቡም ከተጫረ በኋላ ያንን የተጫረውን ጠብ አያያዝ ላይ ሁለቱም ወገኖች ለተለያየ ምክንያት ለፖለቲካም ሆነ ለኢኮኖሚ ጠቀሜታ እንዲውል አድርገውታል ማለት ነው፤ «ስደት ለወሬ ያመቻል» እንደሚባለው መሆኑ ነው። ይኸን ነጥብ ከመዝጋቴ በፊት አንድ ነገር መጥቀስ

የምፈልገው፤ ዛሬ በአስር ላይ የሚገኙት ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ እንደሚታወቀው ባልሆነ መንገድ ተከሰው ቢታሰሩም ዋናው ምክንያት ግን እሳቸው የታሰሩበት በእኔ ግምት ከመጀመሪያው ጀምሮ የኤርትራን መገንጠል በከፍተኛ ደረጃና ጉልህ በሆነ መንገድ ሲቃወሙ በመቆየታቸው ነው። እሳቸውን ያነሳሁበት ምክንያት ይኼ ቻርተር ተብሎ የወጣው ለኤርትሪያ መገንጠል ሁኔታ የሚያመቻቸውን ሁኔታ ያኔ እሳቸው ብቻ ከነበረው ተስብሳቢ ሁሉ ብቻቸውን ነበር የተቃወሙት። ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ ሪቪው በፃፉት አርቲክል ላይ «ይኼ የኤርትራ መገንጠል ትዕይንት የአስቂኝ አሳዛኝ ትዕይንት የሚያስከትለውና መጨረሻው ምን እንደሚሆን ገና በደንብ አልተጤነም። ትዕይንቱ ተጀመረ እንጂ አላለቀም። የሚያስከትለው ነገር ግን በጣም አሳዛኝና ሰፊ መሆኑ የማይቀር ነው» ብለው ነበር። ይኸው እንግዲህ እንዳሉትም እየሆነ ነው።

ወሰንን በሚመለከት እንደሚታወቀው ሁሉ የአዲስ አበባው የወያኔ ትግራይ ገዢ አባላት በዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ነገሩ በሰላም እንዲፈታ እንስማማለን ይላሉ። ይህ እንዲሆንም መጀመሪያ ከያዙት ቦታ ሻዕቢያዎች ይውጡ እንጂ ብለዋል። ይኼ አባባል እንግዲህ የሚያነሳው የትኛው ዓለም አቀፍ ወሰን ስምምነት ነው በሃሳባቸው ውስጥ ያለው? ወይም የሚያውቁት ነገር ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ያነሳል። ቅድም እንዳልኩት ወሰኑ እንግዲህ የተገረሰሰው መጀመሪያ የ46 ሺህ እስኩየር ማይልስ የኢትዮጵያ አንጡራ መሬት ሲነጠቅ ወይም ሲሰጥ ነው። ያንጊዜ ነው ወሰን የተገረሰሰው። እንዲሁም ጣሊያኖች በአሁኑ ጊዜ በየጊዜው ሽር ጉድ እያሉ ካርታውንም ዶክሜንቱንም ምኑንም እናቀርባለንና በስምምነት እንዲፈጸም ይላሉ አሉ። በውነቱ ሃፍረተቢስነት ነው። መጠየቅ ያለብን፤ ጣሊያኖች አሁን የሚያቀርቡት ዶክሜንት የትኛውን ነው? የሚል ጥያቄ ነው። እንደሚታወቀው የውጫሌ ስምምነት የሚባለው በፈረንጆች አቆጣጠር በ1889 ወደ አድዋ ግጭት አደረሰ። የዛን ጊዜም ቢሆን የወሰን መጣስ ነገር ነበር ግን የወሰን መጣስ ቢባልም የዛን ጊዜ ወሰኑ በደንብ ተለይቶ በጽሑፍም ሆነ በመሬት ላይ በምልክት አልነበረውም። ይህም ለግጭት አመቺ ነበር። ከዛ በኋላ በአድዋ ጦርነት ደግሞ ያ ተዳፈነ፤ ተሰረዘ፣ ተሻረ፣ አለፈ። እንደገና ሌላ ስምምነት ተደርጐ በ1897 ወደፊት እንስማማለን ለጊዜው «በነበረው ይርጋ» ተባለ። «በነበረው ይርጋ» የሚባለው እንግዲህ ሁለቱም ወገን የመሰለውን በማለት ነው እንጂ የታወቀ በውል የለየለት ነገር አልነበረም። ከዚያም እንደገና በ1908 ወሰንን በሚመለከት በለስ ሙና እንደዚሁ መረብ ተብሎ ብቻ ታለፈ እንጂ አሁንም የተረጋገጠ ነገር አልነበረም። ሙሶሎኒ በመጣ ጊዜ ሁሉንም ሽሮ ወሰን የሚባለውንም በኢትዮጵያ ደም ለውሶ ቀብሮት በሙሉ አገሪቱን እንደገና የራሱን ኤምፓየር በመፍጠር ኤርትሪያን ታላቋ ኤርትሪያ ብሎ ትግራይንና ወሉን ጨምሮ አዲስ ወሰን ደግሞ እሱ ፈጠረ። ሙሶሎኒ(ጣሊያን) ደግሞ ሲባረር እንግሊዞች በሞግዚትነት በያዙ ጊዜ ስለወሰኑ ምንም የተባለ፣ የተደረገ፣ የተረጋገጠ ወይንም እንደገና ተመልሶ በተግባር ላይ የዋለ ነገር ምንም አልነበረም። የተባበሩት መንግሥታትም የኤርትሪያን ጉዳይ ሲከተልና በመጨረሻም ኤርትሪያ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትዋሃድ ሲደረግ ስለወሰን ማንም ያነሳ የለም። እንግዲህ እዚህ ላይ እናስታውስ። ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ ሲባረሩ ሙሉ መብታቸውና ማንኛውንም በአፍሪካም ሆነ በሌላ ኮሉኒ ቦታ ያላቸውን ነገር ሁሉ ነው ጥለው ለቀው የወጡት። እነሱን ሪኮግናይዝ የሚያደርግ ምንም ዓይነት ኢንተርናሽናል ህግ አልነበረም። ስለዚህ ኢትዮጵያ ተጠቂ እንደመሆኗ መልሳ ደግሞ እነሱ ያቀረቡትን ወሰን ወይም ይሸ ነበር ይኼናው ነው የሚሉትን ለመቀበል አትገደድም። እና ኢትዮጵያና ኤርትሪያ በ1962 ሲዋሃዱ እንዴት እንደተዋሃዱ ሌላው ጥያቄ ነው። ግን የዛን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ መረብን ሲያቋርጡ ሪቫን ቆርጠው በቃ ከእንግዲህ ወዲህ ይኼ ወሰን የለም እንደማለት ምልክት አሳይተው ነበር ያደረጉት። ከዛ በቅርቡም በ1987 እንደገና የዚያ አካባቢም ሆነ የኢትዮጵያ ወሰን ጉዳይ የውስጥ ጉዳይ እንደመሆናቸው እንደገና ተዋቅረው ተሰርተው ነበር።

ስለዚህ የእኔ ነጥብ ምንድነው በኢንተርናሽናል ስምምነቶች መሰረት እንስማማለን ሲባል የትኛው ኢተርናሽናል ስምምነት ነው የሚል ጥያቄ ነው የሚነሳው። ይኸ ሁኔታ በጣም ቀላል አይደለም። እንደገና የኢትዮጵያን ሕዝብ መልሶ ለሌላ ዓይነት ችግር ለማጋለጥ ካልሆነ በቀር የኢንተርናሽናል ስምምነት የሚባል ነገር የለም። እንግዲህ እነዚህ ሰዎች ሁለቱም ወገኖች በኃይል ሥልጣን የያዙ እንደመሆናቸው ማንኛውንም ነገር በዚህም በዛም ብለው በዛው በነፍጥ ያደርጉት እንደሆን ነው እንጂ የኢትዮጵያን ሕዝብ ኢንተርናሽናል ስምምነት አለ ብለው መደለል የለባቸውም ። እና በውነቱ በአንድ በኩል የሻዕቢያው ወገን መሬቱን በኃይል ጨብጦ በሉ አስወጡኝ ማለቱ ምናልባት ይኸንን በመረዳት ይሆናል። ሌላው ወገን ማለትም ወያኔ አይ እኔ በኃይል አላስወጣውም ግን በስምምነት ነገሩ ይፈታ የሚለው ነገር፤ እንደገና ደግሞ ጣሊያኖች በዚህ በኩል እንደገና መጥተው በነገሩ እንዲፈተፍቱና ሌላ ችግር እንዲያመጡ የሚፈለግ ካልሆነ በቀር፤ እኔ በእውነቱ ሕጋዊ የሆነ፣ የማያሻማ፣ የማያጣላ ግልፅ የሆነ የወሰን ስምምነትና የወሰን ምልክት፣ ወሰን አቅጣጫ አለ ለማለት ስልችልም። የኔ ፈንዳሜንታል ጥያቄ ምንድነው የኢትዮጵያ ወሰን የት ነው? የሚለው ነው። የመረቡ ... ሰከንደሪ ነው።

ሶስተኛ፣ መቸም ይኼ ከባድ ጥያቄ ነው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ፣ ኤርትራዊ፣ ሳገሩ ለወገኑ - በእውነት የሚያስብ ሁሉ ሊያስብበት የሚገባና ሊተክዝበት የሚገባ፤ መፍትሔ ሃሳቦችን እያፈለቀ ለሌሎች ለማካፈል የሚችልበት ነገር ነው። በመሰረቱ ቀደም ብዬ እንዳልኩት ይኼ ግጭት የኢትዮጵያ ሕዝብና የኤርትሪያ ሕዝብ አይደለም ብያለሁ። ትልቁና ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ይህ ግጭት ተዛምቶ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእርስ በእርስ ግጭት እንዳይሆን እስካሁንም አልሆነም፣ አልነበረም፣ ወደፊት እንዳይሆን ግን በጣም ጥንቃቄ ይጠይቃል። እነዚህ አሁን በነፍጥ ኃይል ሥልጣን ጨብጠው የያዙ ወይም ኰርቻ ላይ ወጥተው የተቀመጡ ወገኖች ይኸንን የሥልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም እና ማናቸውንም ጥፋት፤ ማንኛውንም አክል፣ ማንኛውንም ችግር በሕዝቡ ላይ ቢደርስ ግድ የላቸውም። ወደ ኋላም አይሉም።

ስለዚህ ትግሉ ሁለት መልክ አለው። አንደኛው፣ ይኸንን ነገር በእንጭጩ ወደማይረባና ወደማይሆን ነገር ሳይሄድ የሚቆምበት መንገድ መፈለግ ነው። ሁለተኛው በምንም ዓይነት ይኼ ነገር ተዛምቶ ከሻዕቢያ ኤርትሪያና ከወያኔ ትግራይ ገዢዎች የእርስ በእርስ አወቅሁሽ ናቅሁሽ ግጭት አልፎ የሕዝብ እንዳይሆን በጣም በጣም ብዙ መከራና ብዙ ጥረት መደረግ አለበት። እንግዲህ

ይህ መቸስ እንዴት እንዲህ ይሆናል ለሚለው ብዙ ዓይነት መንገድ አለ። በመሰረቱ ኢትዮጵያኖች አሁን ማድረግ ያለብን፤ ይኸንን ሁኔታ በጥሞና በመከታተል ይኼ አዲሳ አበባ ያለው ገዢ ወገን እውነት ለኢትዮጵያ የቆመ መሆኑን ማስመስከር ያስፈልጋል። ማስመስከረ ከፈለገ አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች ማመቻቸት ይኖርበታል። የፖለቲካ እስረኞች መለቀቅ አለባቸው፤ ጋዜጠኞችም ጭምር። ሌሎችም ከሥራ የተባረሩ ንፁሕ ኢትዮጵያውያን ቤተሰባቸው ሁሉ በችግር ላይ የሚጉላላው መልሰው ስራ መግባትና ቤተሰባቸውን መልሰው ማቋቋም አለባቸው። ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር የብልጣ ብልጥ ነገር ሳይሆን ቅን ውይይት መከፈት አለበት። ሲሆን ሲሆን እንደውም አገር አቀፍ የሆነ የእርቅ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ያስፈልጋል፤ ገቨርንመንት ኦፍ ናሺናል ሪኮንስልየሽን ወይም አብረን እንገዛም ከሌላ ጋር ካሉ ወያኔ/ ኢሕአዲጉች ወይም ወያኔ ትግራዮች ቦታውን መልቀቅና ለሚመለከተው ቅንብር ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል። ሻዕቢያ ኤርትራውያን በኢትዮጵያ መንደላቀቅና መሟላቀቅ መግታት አለባቸው። የነፍጥ አገዛዝ አክትሞ፤ የነፍጥ ትምክህተኝነት አገዛዝ አክትሞ እውነተኛ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ሁኔታውን ለማመቻቸት አንዳንድ አስፈላጊ የዲሞክራሲ ፈለጉችን በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

በመጨረሻም የሻዕቢያ/ኤርትሪያንም ወገን ሆነ ጠቅላላ የኤርትሪያንና የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ መሰረት ለመጣል ለወደፊቱ ግንኙነት በመመስረት አንዳንድ ፕሪንስፕሎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋል። ይኸውም የሚደረገው ግንኙነት ሁሉ በኢኮኖሚም፤ በፖለቲካም፤ በሕዝባዊ፤ በሶሺያሉም፤ በባሕሉ በማንኛውም መስክ በቅንነት የተመሰረተና ይህን የቅንነትን ፕሪንስፕል የሚከተል፤ በጨዋነት ላይ የተገነባ፤ በሕዝባዊነት ላይ የተመረኮዘ፤ በእኩልነት ላይ የሚያተኩር፤ እንደዚህ እንደዚህ የመሰሉ ለሁሉ የሚጠቅሙ ማንንም የማይጉዱ ግን እኔ እበልጣለሁ እኔ እበልጣለሁ ሳይሆን ለሁሉ የሚበጀው ዓይነት መሰረቶች የተጣሉበት ዓይነት ግኑኝነት መፈጠር፤ ፈለጉ መደረግ አለበት እላለሁ። ግን አንድ ነገር ማወቅ የምንችለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ትግራይ አገዛዝ ምንም ዕዳ የለበትም። የወያኔ አገዛዝ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕዳ አለበት። እንደዚሁም በሻዕቢያ በኩል ለኤርትራ ሕዝብ ትልቅ ዕዳ አለበት። በመደለልና በማታተል በብልጣብልጥነት የተወሰነ ደረጃ ሄዷል። ይህ ሁሉ ተለውጦ ትራንስፓረንሲ እንደሚሉት ግልፅ በሆነ መንገድ ሁሉን ነገር የሚያደርገው የሚታይበትና እነዚህ ሰባት ዓመታት ሙሉ እላዩ ላይ ሲፈነጩበት የቆዩ ወገኖች አሁን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተቻለ መጠን የሚከፍሉትን ዕዳ መክፈል አለባቸው። ይኸንን ለማመቻቸት የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግም በተለመደ ብስለትና በተለመደ ሚዛናዊ አስተሳሰቡ ምን እንደሚደግፍ፤ ምን እንደሚቃወም፤ መቼ ምንን እንደሚደግፍ፤ መቼ ምንን እንደሚቃወም እየገመተና እያሰላ እንቅስቃሴውን ማድረግና ነገሩን በጥሞና መከታተልና ወደባሰ ነገር ሁሉ እንዳይሄድ አስተዋጽኦውን ሁሉ ማከል የሚያስፈልገው ይመስለኛል።


# እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደራችሁ!!

| | |
|---|---|
| ሙክት በግ | $39.99 |
| ዶሮ | $ 5.99 |
| ውስኪ | $29.99 |
| ሻምፓኝ | $19.99 |
| ኬክ | $15.99 |
| አበባ ቡኬ | $10.99 |

አዲስ አበባ ለቤተሰባችሁ በር ድረስ እናደርሳለን። ለስልክ ገንዘብ ከማባከን፤ በባህላዊ ሥነሥርዓት ቤተሰባችሁንና ዘመዶቻችሁን አስደስቱ። የዚህ ሺያጭ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ለሚከፈተው ቤተ መጽሐፍት ውላል።

እናመሰግናለን!!

ስልክ (310)532–4177

የጽሑፍ መልዕክት ቁጥር

(FAX ) (310)532–4619

## የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች
## ጉባኤ መግለጫ
## የኤርትራ መንግሥት ወረራ
## ያስከተለው የሰብአዊ መብት ረገጣ

**ልዩ መግለጫ ቁጥር 22**

**ነሐሴ 18 ቀን 1990 ዓ.ም**

1ኛ. የኤርትራ መንግሥት ከግንቦት 4 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያን መሬት በጦር ኃይሉ ወርሮ ይዟል። በባድመ በኩል በጀመረው ወረራ ባድመንና ከፊል ሽራሮን ተቆጣጥሮ ሰላማዊ ሰዎችን ገድሏል፣ ትምህርት ቤቶችና የጤና ተቋማትን አፈራርሷል፣ የአካባቢውን ነዋሪዎች ከቀያቸው አፈናቅሏል። በዛላንበሳ በኩል በከፈተው ወረራም የዛለንበሳን ከተማ በከባድ መሳሪያ አውድሟል፣ የከተማውንና የአካባቢውን ነዋሪዎችም አፈናቅሏል።

ግንቦት 28 ቀን 1990 ዓ.ም መቀሌ ያለውን የአይደር 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአውሮፕላን ደብድቦ የትምህርት ቤቱን ሕፃናትና በቦታው የነበሩ ሰላማዊ ሰዎችን ገድሏል፣ አቁስሏል፣ አካለ ጉደሉ አድርጓል። በአዲግራት ከተማም ወታደራዊ ያልሆኑ ኢላማዎችን በአውሮፕላን ደብድቦ በሰለማዊ ሰዎች ላይ ተመሳሳይ ጉዳት አድርሷል። በመጋዘን የተከማቸ የዕርዳታ እህልና ዘይትም ከነመጋዘኑ አቃጥሏል።

እንዲሁም በኤርትራ እየሰሩ የሚኖሩ ብዙ ኢትዮጵያውያንን ከሥራ አስወጥቷል፣ ንብረታቸውን ሳይዙ ካገር አባርሯል። ወረራው በተጀመረ ዕለት ከሥራ የተባረሩት አሰብ በሚገኘው አየር መንገድ መ/ቤት በዕቃ ተሸካሚነት ይሰሩ የነበሩት ናቸው። የአሰብ ወደብ ከግንቦት 10 ቀን 1990 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ስላቆመ በወደቡ ይሰራ የነበሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከሥራ ተሰናብተዋል። ኢትዮጵያውያን መውጣትም ሆነ መግባት እንደማይችሉ አሰብ ባሉ የኤርትራ ባለሥልጣኖች ግንቦት 19 ቀን ተነግሯል። ከዚህ በኋላ የኤርትራ ወታደሮች ኢትዮጵያውያንን እየያዙ በተለያዩ እስር ቤቶች አጉረዋል። አንዳንዶቹንም እየደበደቡ አሰቃይተዋል። ከማጎሪያና ከማሰቃያ ቦታዎቹ መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ዞባ 2 መምህዳር 06 ክልል የሚገኘው ካምቦ ሱዳን ፖሊስ ጣቢያ፣ — ዞባ 2 መምህዳር 02 ክልል የሚገኘው የአሰብ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ፣ — ዞባ 1 መምህዳር 01 ክልል የሚገኘው የአሰብ ወህኒ ቤት፣ ዞባ መምህዳር 01 ክልል አሰብ ሰቂር በሚባል ቦታ የሚገኘው የቀድሞ ወንጀል ምርመራ፣ — በምፅዋ መንገድ ከአሰብ 5 ኪሎ ሜትር የሚርቀውና አሰብ ኤርፖርት ፊት ለፊት ልዩ ስሙ ቀይ ጉራ በሚባለው ቦታ የሚገኘው የቀድሞ 30ኛ ክፍለ ጦር ካምፕ

ከአሰብ ወደብ ወደ ቡሬ በሚወስደው መንገድ 7 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ አዲ ንፋስ በሚባለው ቦታ የሚገኘው የቀድሞ የዓለም የምግብ ድርጅት መጋዘን፣ በጂቡቲ መስመር 55 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ እነዚህ የሚገኘው አይሉ የሚባለው እስር ቤት፣ እዚህ የሚታሰሩት ኢትዮጵያውያን በግዳጅ ጨው ያመርታሉ።

ከሰኔ 18 እስከ ነሐሴ 2 ቀን 1990 ዓ.ም ድረስ 548 ኢትዮጵያውያን ከአሰብ ተፈናቅለው ወደ አዲስ አበባ መጥተዋል። ከነዚህ መካከል 346 የሚሆኑት በዓሣ ማጥመጃ ጀልባ ከአሰብ ወደ ጅቡቲ ከተወሰዱ በኋላ ከጅቡቲ በባቡር ወደ አዲስ አበባ መጥተዋል። በጀልባ ወደ ጅቡቲ የተወሰዱት ሁሉም ኢትዮጵያውያን ዕዳ የሌለባቸው መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከውሀ፣ከመብራት ከቴሌ፣ ከባንክ፣ ከኪራይ ቤቶች ድርጅትና ከንግድ ቢሮ እንዲያመጡ ታዘው ለእያንዳንዱ መ/ቤት 50 ናቅፋ ከፍለዋል። እንዲሁም ለኢሚግሬሽን መ/ቤት 150 ናቅፋ ለወደብ ታክስ 12 ናቅፋ፣ ለጀልባ 300 ናቅፋ፣ በድምሩ 762 ናቅፋ እያንዳንዳቸው ተገድደው ከፍለዋል። መክፈል ያልቻሉ ከአሰብ እንዲወጡ አልተፈቀደላቸውም። ዕዳ ያለባቸው እንዳይወጡ ተከልክለዋል። ከነዚህ ተፈናቃዮች መካከል አብዛኞቹ እዚያው አሰብ ተወልደው ያደጉ፣ ለረዥም ጊዜ የሰሩና ንብረት ያፈሩ ናቸው። አንዳንዶቹ በመምህርነት፣ አንዳንዶቹ በኮንስትራክሽን ሠራተኛነት፣ ሌሎቹ ደግሞ በንግድና በዝቅተኛ ሥራ የተሰማሩ ነበሩ። የአሰብ ተፈናቃዮች በአሁኑ ጊዜ ሸጎሌ በሚገኘው ፖሊስ ካምፕ፣ልዕለ ግቢና ወረዳ 13 ቀበሌ 09 ክልል በተጨናነቀና በተጉሳቆለ ሁኔታ ይኖራሉ። የተወሰኑ ተፈናቃዮችም በየዘመዶቻቸው ተጠግተው ይኖራሉ። እንዲሁም ከቀረው የኤርትራ ግዛት የተፈናቀሉና የኤርትራ ወታደሮች በድብደባ ከፍተኛ የአካል ጉዳት አደረሱብን ያሉ ሰዎች የደረሰባቸውን ስቃይ ለጋዜጠኞች ሲያስረዱ በቴሌቪዥን ተከታትለናል።

የኤርትራ መሪዎች የኢትዮጵያን ዜጎች ሰብአዊ መብቶች ሲረግጡ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያቸው አይደለም። የዛሬ ሰባት ዓመትም በኤርትራ ይኖሩ የነበሩ ብዙ ሺህ ኢትዮጵያውያንን ንብረታቸውንና ገንዘባቸውን ሳይዙ ከኤርትራ አስወጥተዋል። ከኢትዮጵያን ባሎቻቸው ልጆች የወለዱ የኤርትራ ሴቶችንም ከነልጆቻቸው ከኤርትራ አባርረዋል። ከእነዚህ ከኤርትራ ከተባረሩ ኢትዮጵያውያን መካከል በየጉዳናው እየተንከራተቱና እየለመኑ በላስቲክ ዳስ የሚኖሩ ብዙ ናቸው። ስለእነዚህ ተፈናቃዮች በኢሰመጉ 3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛና 6ኛ መግለጫዎች የተዘገበ ቢሆንም የኢትዮጵያ መንግሥት መብታቸውን ለማስከበር የወሰደው ርምጃ የለም።

2ኛ – የኤርትራ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ከፈፀመና በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ካደረሰ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት ለብሔራዊ ፀጥታ ያሰጋሉ ያላቸውን ኤርትራውያን ካገር አባርሯል፣ በወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፖችም አግቷል። በዚህ ርምጃ ባል ከሚስቱ፣ ወላጆች ከልጆቻቸው የተለያዩባቸው ሁኔታዎች አጋጥመዋል። በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ከሚሰሩ የኤርትራ ተወላጆች መካከልም አንዳንዶቹ ከሥራ ተባረዋል፣ ብዙዎቹ ደግሞ ደመወዝ እየተከፈላቸው እረፍት እንዲወስዱ ተደረገዋል። ለብሔራዊ ፀጥታ ያሰጋሉ የተባሉት በርካታዎቹ በአዲስ አበባ የሚኖሩት የኤርትራ ተወላጆች በፀጥታ ኃይሎች የተያዙት ሌሊት ነው። ወደ ኤርትራ የተወሰዱትም ወደ ሌላ አገር መሄድ ይፈልጉ እንደሆነ

ምርጫ ሳይሰጣቸው ነው። እነዚህ ካገር የተባረሩት ኤርትራውያን ለንብረታቸው ሰው እንዲወክሉና ቤተሰቦቻቸውም ከፈለጉ እዚሁ መኖር እንደሚችሉ ተገልጾ ነበር። በኋላ ግን የቀሩት ቤተሰቦቻቸውም ንብረታቸውን እየሸጡ ካገር እንዲወጡ በየወረዳዎቹ መስተዳድሮች ታዘዋል።

3ኛ – በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀፅ 4(1)ና 13 እንደተደነገገው በመንግሥት በይፋ የተገለፀ የአገርን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲፈጠር አግባብ ያላቸው ያገሩ ባለሥልጣኖች በሕግ ላይ ተመስርተውና ሕጋዊ ሥርዓትን ተከትለው በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት የውጭ አገር ዜጎች ካገር እንዲወጡ ሊደረግ ይችላል። በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል በመንግሥት በይፋ የተገለፀ ጦርነት ተጀምሯል። በዜጎችና በንብረት ላይም ብዙ ጉዳት ደርሷል። የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል የአገሪቱን ዳር ድንበር ለማስከበርና የኤርትራ መንግሥት የከፈተውን ወረራ ለማክሸፍ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘውን ርምጃ ሁሉ እንዲወስድ ታዟል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ከመከላከያ ሠራዊቱ ጐን እንዲሰለፍና የአገርን ዳር ድንበር ለማስከበር የሚያስችሉ ርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ ጥሪ ተደርጎለታል። ስለዚህ ወረራው ያገርን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ መንግሥት ለብሔራዊ ፀጥታ ያሰጋሉ ያላቸውን የውጭ አገር ዜጎች ካገር ማስወጣት ይችላል።

4ኛ – ነገር ግን ፣ ንፁሐን ሰዎች እንዳይበደሉ አሰራሩ ሕጋዊ ሥርዓትን የተከተለና ግልፅ መሆን አለበት። አሰራሩ ሕጋዊ ሥርዓትን ካልተከተለና ግልፅ ካልሆነ እንደ ዘመነ ቀይ ሽብር "ከሚደርስብህ ችግር እንዳድንህ ይህን አድርግልኝ፣ ይህን ያህል ገንዘብ ስጠኝ" ለሚል የሕገ ወጥ መጠቃቀም (Corruption) በር ይከፍታል። ስለዚህ የንፁሐን ሰዎች ሰብአዊ መብት እንዳይረገጥና ለሕገ ወጥ መጠቃቀም አመቺ ሁኔታ እንዳይፈጠር፣ የኢትዮጵያ ዜጎች የሆኑ የኤርትራ ተወላጆችም ስጋት ላይ እንዳይወድቁ ካገር የሚባረሩትን የውጭ አገር ዜጎች ጉዳይ የሚያይና ውሳኔ የሚሰጥ አንድ አካል መፈጠር አለበት፣ ሕግም መውጣት አለበት። ምክንያቱም የውጭ አገር ዜጋ ካገር መውጣት ያለበት አግባብ ያላቸው ያገሩ ባለሥልጣኖች በሕግ ላይ ተመስረተው በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት ብቻ ነው።

5ኛ – የሚያሳዝነው የኤርትራ ተወላጆች ከኢትዮጵያ የተባረሩት የዜግነታቸው ጉዳይ እንኳን በወጉ ውሳኔ ሳያገኝ መሆኑ ነው። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነፃ አገር ስትሆን በኢትዮጵያ የሚኖሩ የኤርትራ ተወላጆች የኤርትራን ዜግነት ይምረጡ ወይም የኢትዮጵያን ዜግነት እንደይዙ ይቆዩ እንደሆነ አልተጠየቁም። ስለዚህ፣ አሁን ድንገት የተፈጠረው ሁኔታ የኢትዮጵያ ዜጎች የሆኑትን የኤርትራ ተወላጆች ጭምር ስጋት ላይ ጥሏል።

ኤርትራ ነፃ አገር ከመሆኗ በፊት ሁሉም የኤርትራ ተወላጆች የኢትዮጵያ ዜጎች ነበሩ። የኤርትራ ዜግነት የተፈጠረው ከሚያዝያ 15 እስከ 17 ቀን 1985 ዓ.ም በተደረገው ሪፈረንደም ውጤት መሰረት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነፃ አገር ስትሆን ነው። ኤርትራውያን በዚህ ሪፈረንደም ድምፅ የሰጡት በኤርትራ ተወላጅነታቸው እንጂ በኤርትራ ዜግነታቸው አይደለም። በኢትዮጵያ የሚኖሩ የኤርትራ ተወላጆች ኤርትራ ነፃ አገር ከሆነች በኋላ የኢትዮጵያ ዜግነታቸውን ለውጠው የኤርትራን ዜግነት መቀበላቸው ሳይረጋገጥ በሪፈረንደሙ ድምፅ ስለሰጡ ብቻ የኢትዮጵያ ዜግነታቸው ሊገፈፍ አይችልም። የኢትዮጵያ ዜጋ የነበረ ሰወ የኢትዮጵያ ዜግነቱን የሚያጣው ዜግነቱን በፈቃዱ ለውጦ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን ብቻ ነው።

6ኛ. የኤርትራ ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበረው እንደ ኢትዮጵያ ዜጎች ነበር። እንዲያውም መንግሥት ለእነሱ ከራሱም ዜጎች የተሻለ በጐ አመለካከት ነበረው። ይሁን እንጂ፣ የእነዚህ ኤርትራውያን ጉዳይ ሕጋዊ ሥርዓት እንዲይዝ ብዙ ሰዎች በተለያየ ጊዜ ወትውተው ነበር። ለምሳሌ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ክቡር አቶ ስዩም መስፍን ስለ መ/ቤታቸው የሥራ አፈፃፀም ሚያዝያ 22 ቀን 1988 ዓ.ም ለተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ባቀረቡበት ጊዜ ሁለት የምክር ቤት አባላት ይህን ጉዳይ አንስተውባቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል።

የኤርትራ ሉዐላዊነት በሕዝቡ ትግል የተገኘ ቢሆንም ወዲያው በሰላም አብሮ መኖር ይመጣል ብሎ መደምደም አይቻልም ነበር። ነገር ግን በኤርትራና በኢትዮጵያ መንግሥታት የተመረጠው መንገድ የሰላምና የጨዋ ሕዝብ ነው። ያለፈው አልፏል። ደም መፋሰስ በቃ። ሽኩቻ ይቁም። ከእንግዲህ በኋላ የፈረሰ ቤታችንን አብረን በሰላምና በእኩልነት እንገነባለን ነበር እኛ ያልነው። ለዚህ ሂደት ትልቅ ዋጋ የማንሰጠው ከሆን ይህ ትውልድ ትልቅ ስሕተት የሚሰራ ይመስለኛል። ስለዚህ፣ ማንኛውም የኤርትራ ዜጋ ከኢትዮጵያ ጋር ጐን ለጐን በመሥራት ራሱንና የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ መጥቀም የለበትም የሚባል ከሆን ያለፈውን ስሕተት መድገም ይመስለኛል። በኢትዮጵያውያንና በኤርትራውያን መካከል ብዙ ትስስር አለ። ማን ያውቃል፣ በኢኮኖሚ ወይም እንዲያውም በፖለቲካ በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ውሕደት አንድ ቀን ይመሰርቱ ይሆናል።

የቀድሞው ም/ጠቅላይ ሚኒስትርና የመከላከያ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔም ጋዜጠኞች ላቀረቡላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥተው ነበር።

"ኢትዮጵያውያን እያሉ ኤርትራውያን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል የሚለው በደረጃ መታየት ያለበት ይመስለኛል፣... ይኼን ጉዳይ መንግሥት የሚመለከተው በአንድ በኩል መሰረታዊ በሆኑ መንግሥታዊ ተቋሞች ውስጥና መንግሥታዊ የሆኑ የአመራር ቦታዎች ላይ አሁን ያሉት ኢትዮጵያውያን ዜጎች መሆናቸውን ነው። ኢትዮጵያውያን ዜጎች በምንልበት ጊዜ በትውልድ ኤርትራዊ ሆነው ነገር ግን በዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ መሆን የፈለጉና ይህንንም ያረጋገጡ ጭምር ማለታችን ነው። ኤርትራዊ በትውልድ ሆነው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ኖሯቸው በማንኛውም ቦታ ላይ ሊሰሩ መብት ስላላቸው ነው። መሰረታዊና ቁልፍ በሆኑ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ አሁንም የዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው ያለው፣... በትውልድም በዜግነትም ኤርትራውያን የሆኑ በተለያየ መስሪያ ቤት ውስጥ ይኖራሉ። እነዚህን ደረጃ በደረጃ ልናያቸው እንደሚገባ

ከኤርትራ መንግሥት ጋርም ተነጋግረን ባለፈው ሁለት ዓመት አካባቢ በኤርትራና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል በነበረው የጋራ የሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ይኼ ጉዳይ ተነስቶ ውይይት ተካሂዶበታል። በዚያ ስብሰባ ላይ በዜግነትም ኤርትራውያን የሆኑ እንደ ማንኛውም የውጪ ዜጋ ሁሉ የሚታዩበትና የሚያዙበት ተግባር ምን መሆን አለበት የሚል ውይይት ኀበር ያደረግነው። እዚያው ውይይት ላይ በመሰረቱ ሁለቱ መንግሥቶች በዜግነት ኤርትራውያን የሆኑ ሁሉ እንደ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ መታየትና ከዚያም አንፃር ዕድገታቸውም ኃላፊነታቸውም መወሰን እንደሚኖርበት ስምምነት ላይ ተደርሷል። በዚህ ላይ ምንም ዓይነት የመርህ ልዩነት የለም፣ ሊኖርም አይችልም። አፈፃፀሙን በሚመለከት ግን ደረጃ በደረጃ መደረግ እንዳለበት ነው የተስማማነው። ለምሳሌ ኤርትራዊ ዜጋ የሆኑ ተማሪዎች አሉ። የውጪ አገር ዜጋ እዚህ አገር በሚማርበት ጊዜ መክፈል ያለበት ከሆነ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሕግ እነሱም መክፈል አለባቸው ማለት ነው። ነገር ግን የኤርትራ መንግሥት በመጀመሪያ ላይ የዝግጅት ጊዜ እንዲኖረን ለሰዎቹ ለራሳቸው ተነግሯቸው ይኼ ነገር ምን መደረግ እንዳለበት ተዘጋጅተው እንዲገቡበት፣... ከዚያ በኋላ በአግባቡ እንዲፈፀም በሚል ነው የተስማማነው። ይኼ የዝግጅት ጊዜ በስምምነታችን መሰረት ምናልባት በዚህ ዓመት መጨረሻ ገደማ ይጠናቀቅ ይሆናል። ከዚያ በኋላ እንደ ማንኛውም የውጪ ዜጋ ማድረግ ያለባቸውን ሁሉ የሚያደርጉበት ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው። ይሄን ለማድረግ ግን አብሮ የኢትዮጵያ መንግሥትም መመሪያዎችና አሰራሮችን ማዘጋጀትና ማሳወቅ ይኖርበታል። ይኼንንም እያደረገ ነው። ይሄ እንዳለ ሆኖ ግን የኤርትራ ዜጎች ይሰራሉ በሚባሉበት ሊሰሩ በሚገባቸውና በሙያም በብቃትም በመሳሰሉት መንገዶች ሁሉ ሊሰሩ የሚችሉ መሆናቸው መታወቅ ይኖርበታል። እንደማንኛውም የውጪ አገር ዜጋ ግዴታዎቻቸውን አሟልተው የመንግሥትን ፖሊሲና አሰራር አሟልተው በማንኛውም የሥራ መስክ መሥራት መቻል ይኖርባቸዋል።"

ክቡርጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም የገንዘብ ለውጥ ከተደረገ በኋላ እንዲህ ብለዋል፣

"በሁለቱም አገሮች የሚኖሩ የሁለቱ አገሮች ዜጎች የሚኖሩበትን ሁኔታ በተመለከተ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ከዚህ በፊት ከነበረው ፖሊሲ የተለወጠ የለም። ለወደፊትም አይኖርም። በኤርትራ መንግሥት በኩል ከፖሊሲ አኳያ እስካሁን ድረስ እኔ የማውቀው የተለወጠ ፖሊሲ የለም። ስለሆነም በሕዝቦች እንቅስቃሴና ኑሮ ላይ እንቅፋት የሚፈጥር የፖሊሲ ለውጥ አለ ብዬ አላምንም።"

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች መግለጫዎች በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኤርትራውያን እንደ ኢትዮጵያ ዜጎች ለመኖር እንችላለን የሚል ግምት እንዲያድርባቸውና እንዲዘናጉ አድርገዋቸዋል። የክቡር አቶ ስዩም መስፍን ማንኛውም የኤርትራ ዜጋ ከኢትዮጵያዊ ጋር ጐን ለጐን በመሥራት ራሱንና የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ መጥቀም የለበትም የሚባል ከሆነ ያለፈውን ስሕተት መድገም ይመስለኛል የሚለው አነጋገር ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የኤርትራ ተወላጆች ምንም ዓይነት ችግር ሳይገጥማቸው እንደቀድሞው ለመሥራትና ለመኖር የሚችሉ መሆኑን ያረጋግጥላቸዋል።

"የኤርትራ መንግሥት በመጀመሪያ ላይ የዝግጅት ጊዜ እንዲኖረን፣ ለሰዎቹ ለራሳቸው ተነግሯቸው ተዘጋጅተው እንዲገቡበት፣ ... ከዚያ በኋላ በአግባቡ እንዲፈፀም ነው የተስማማነው። ይኼ የዝግጅት ጊዜ በስምምነታችን መሰረት ምናልባት በዚህ ዓመት መጨረሻ ገደማ ይጠናቀቅ ይሆናል። ከዚያ በኋላ እንደ ማንኛውም የውጪ ዜጋ ማድረግ ያለባቸውን ሁሉ የሚያደርጉበትም ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው። ይሄን ለማድረግ ግን አብሮ የኢትዮጵያ መንግሥትም መመሪያዎችንና አሰራሮችን ማዘጋጀትና ማሳወቅ ይኖርበታል፣" የሚለው የአቶ ታምራት ላይኔ መግለጫም እነዚህ የኤርትራ ተወላጆች የኢትዮጵያ መንግሥት ገና መመሪያዎችንና ደንቦችን አውጥቶ ምን ማድረግ እንዳለብን ያሳውቀናል ብለው እንዲጠብቁ አድርጓቸዋል።

"በሁለቱም አገሮች የሚኖሩ የሁለቱ አገሮች ዜጎች የሚኖሩበትን ሁኔታ በተመለከተ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ከዚህ በፊት ከነበረው ፖሊሲ ያተለወጠ የለም፣ ለወደፊትም አይኖርም፣" የሚለው የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ቃለ ምልልስም የኤርትራ ዜጎች በኢትዮጵያ የሚኖርበት ሁኔታ እንደማይለወጥ ስለሚያረጋግጥ የኤርትራ ዜጎች እንደውጭ አገር ዜጎች ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ ዜጎች እንኖራለን ብለው እንዲያምኑ አድርጓቸዋል።

ነገር ግን፣ የኤርትራ መንግሥት የኢትዮጵያን መሬት በጦር ኃይል ወርሮ በመያዙ፣ በኤርትራ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ከፍተኛ ግፍ በመፈፀሙና የሀገርን ሕልውናና የሕዝብን ደኅንነት አደጋ ላይ በመጣሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሀገር ደኅንነት ያሰጋሉ ያላቸውን ኤርትራውያን ሕጋዊ ሥርዓትን ሳይከተል ወደ ኤርትራ አባርሯል፣ በወታደር ማሰልጠኛ ካምፖችም አግቶ አስቀምጧል። ወደ ኤርትራ የተባረሩት ወደ ሌላ አገር ለመሄድ ይፈልጉ እንደሆነ ምርጫ አልተሰጣቸውም። ያፈሩትን ንብረት ይዘው ወይም ሸጠው እንዲሄዱም በቂ ጊዜ አልተሰጣቸውም። በአንዳንድ ሁኔታዎችም ባል ከሚስቱ፣ ወላጆች ከልጆቻቸው ተለያይተዋል። ይህ ድርጊት ሰብአዊ መብትን የሚፃረር ነው። ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የኤርትራ መንግሥት ከተከተለው ሕገ ወጥ አሰራር ራሱን አቅቦ፣ ለብሔራዊ ፀጥታና ለሀገር ደኅንነት ያሰጋሉ የሚባሉ የኤርትራ ዜጎችን በሚያስወጣበት ወይም በሚያግትበት ጊዜ ሕጋዊ ሥርዓትን (due process of the law) እንዲከተል ኢሰመጉ ይጠይቃል። እንዲሁም ለሰብአዊ መብቶች መከበር የቆማችሁ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ ቷቋማት ሁሉ፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ መንግሥታት የውጭ አገር ዜጎችና ከየአገሮቻቸው በሚያስወጡበትና በሚያግቱበት ጊዜ ሕጋዊ ሥርዓትን እንዲከተሉና ሰብአዊ መብቶችን እንዲያከብሩ የበኩላችሁን ግፊት እንድታደርጉ ኢሰመጉ ጥሪ ያቀርባል።

# የዘር ታሪክ ብክለት
# መርሆዎቻችሁን አንሱልን

ከአድዋ ታደገኝ (ከምጥዋ)

ለዘር የሚበቃ ወንጀል
አንድን ዜጋ መከፋፈል
በጐጥ፣ በጐሳ በኃይማኖት መከፋፈል
ለትውልድ የሚደርስ አንድነትን
የሚያጠፋ ወንጀል
በዲሞክራሲ ስም ነግዶ አንድነትን ማፍረስ
የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክን በመቶ ዓመት መቀነስ
የምን ታሪክ እያሉ የሌለን ታሪክ እያወሩ መበከል
ጀግኖችን እያኮሰሱ የሌለ ጀግንነትን መትከል
በዘር ማጥፋት ወንጀል እየከሰሱ ለፍርድ
ለዘር የሚበቃ! ትውልድ የሚያጠቃ!
ሰደድ እሳት ማንደድ
ይህ ነው የዴሞክራሲ ትርጉም?
ለመከፋፈል ነው ለአገር መቆም?

በመርዘኛ ፖሊሲ ዜጋን ማስለቀስ
በዲሞክራሲ ስም የአገርን ሀብት
ወደ ውጭ ማፍሰስ
በሽፍትነት የአገር መሪ መሆን አንሶ
የአገርን ታሪክ አጣጥሎ አንኳሶ
ይህ ኦሮሞ – ውራጌ፣ ያ ትግሬ– አማራ
ይህ ደሞ ሀደሬ–አፋር፣ ያኛውን ስልጤ – ጊሚራ
እየተባለ 'የራስን መብት በራስ መወሰን' ፍልስፍና
አትወቅብን እንጂ እናውቅልሃለን እያሉ ና
... የወደቀ ኢኮኖሚያችንን አንስቶ
አገራችንን ለማልማት
ከሰለጠኑ አገሮችና ባለሀብቶች ነፃ ገበያን መዘርጋት
ይሉናል ሲጀምሩ የሀብት ማጋበሻቸውን ተረት
ይሞክራሉ ሊያስረዱን ካንዱ ወደ አንዱ
የሚያገላብጣቸውን ወረት
ከዚያ ኢንቬስተር ወደ ክልል ገብቶ ያልማ ይላሉ
በእናውቅልሃለን ስም ሀብቱን
ወደ ውጭ ሲያስኮበልሉ
በከፋፍለህ ግዛ መርሆዋቸው
የግል ሀብት ሲያከማቹ የአንድነት ታሪክ ጥለው
ጐሰኝነትን ለዘር የሚያበቃ ወንጀል ተክለው
ዴሞክራሲ የሚለውን የእንቶኔ ቃል
ሽቀጥ አድርገው
ላይጠቅሙን ራስ ጠቅመው፤ ዓመታት አስቆጠሩ
በዘር ብክለት ታሪክንና ምሁሩን እየቀበሩ።
የምን ዴሞክራሲ የምን ብልፅግና የምን እኩልነት
የሌለን አለ እያሉ በባዶ ቤት መወትወት
የትኛውን ጀግንነት ሊነግሩን ነው ደሞ
በስማ በለው የሚዶልቱት አታሞ
ታሪክ አናውቅ ሲሉ ከርመው እስከዛሬ
ስሙ መሰል ገበና ከሸጠ ምሁር ነኝ ባይ ወሬ
በዘር ብክለት ከተሳተፈ ባንዳቸው
ባንዲራችንን ጨርቅ ነው ብሎ ካበራቸው
እኛ የማናውቀውን እነሱ የሚያውቁልንን
ምን ሊነግሩን
የጥንቱን ጀግና አጥንት አውጥተው
አዲስ ጀግና ሊተኩልን?
ወይስ የተጠናወታቸውን የጐሳ ፍልስፍና ሊነዙልን
በአድዋ ስም ነግደው ሊነግዱብን

ይህኛው ደግሞ አልገባንም ትርጉሙ ዘዬው
ማንና ምን ምኑና ማን ነው ጨዋታው
ብቻ እንዳይሰማ ያ ጀግና የጥንቱ
የአድዋ ታሪክ ባለሀብቱ
እንዳይሰማና ይህንን ጨዋ እንቶ–ፈንቶ
እንዳይነሳ አፈሩን አራግፎ ተቆጥቶ
እሱ እንደውም ሽፍታ አይወድም ከቶ
እንኳን ዘር በክለው በታሪክ ተጫውተው ቀርቶ
ያ የጥንቱ ባለታሪክ የአድዋ ሰው
ሀገሩን በደሙና በአጥንቱ የቀለሰው
እምዬ! የአገሩን አንድነት ለትውልድ ያወረሰው
እንዳይሰማችሁ፤ ከጀግና ጉራ ከሙት
መንደር ያለው
ከተቆጣ አይመለስም 'አራስ ነብር' ነው።

ዛሬ አታውቁልንም፤ ገብቶናል፣ አውቀናል
የእናንተንም ዲስኩር የቃላት ብቱቶ ይበቃናል

የዘር ብክለት መርዛችሁን አርክሱልን
ታሪካችንን ባንዲራችንን አድሱልን
ይሄን ዴሞክራሲ የሚል ፈሊጥ ተዉን
እውን ዴሞክራሲያዊ ነፃነት መስርቱልን
አንድነታችንን መልሱልን።

## የቤት ነገር

በሰይፉ ኣዳነች ብሻው
(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፺ ዓመት
SAEFU © Copyright 1998

የእግዜር ስህተቱ በአንዲት ሲል ኑሩ
የወንድ ድክመቱ ለሱስ መፈጠሩ
የቤቷ ጉልበቷ በፍቅር መጫወቷ
ባልመሰላት ወንድ ሲነካባት መብቷ
ወንድ አያርፍ ግድ የለሽ ያበዛል ማሽሞንሞን
እስኪሸከም ቅሌት እንደ ቢል ክሊንተን
የአርካንሳስ ወጣቶች ከክሊንተን አገር
መልሳቸው ጥይት ነው ሲነሳ የቤት ነገር

## እንዴት አላዝን እኔ

በሰይፉ ኣዳነች ብሻው

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፺ ዓመት
Saefu © Copyright 1998

ምስጢራዊት ይሏት የነበረች - ታሪካዊ አገር
በዓለም የነበራት ሥልጣኔ - ሃይማኖትና ምግባር
ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ አንድነቷን - ቅርሷን ማሰባሰብ
የራስ ጥቅምና ዝና ብቻ - ቢበዛ መስገብገብ
መሸጥ፣ መለወጥ፣ መከፋፈል ሲሆን - ደካማው ጥበብ
ክብሯ መብቷ ሲገፈፍ ሳይ - ለምን አልንገበገብ

ለሺህ ዘመናት አስደንቃ - እንዴት አላዝን እኔ
በስምንተኛው ሺህ ስትሆን ዕቃ - እንዴት አላዝን እኔ
አንድነቷ ጠፍቶ ሲከፋፈል - እንዴት አላዝን እኔ
ውስጧን ተመዝብራ ስትዋልል - እንዴት አላዝን እኔ
ሲጠፋ አብሮ የ'ኔ ክብር - እንዴት አላዝን እኔ
ለጥቁር ዕንቁዋ አገሬ - እንዴት አላዝን እኔ

ምሳሌ የነበረች በዓለም ፊት - በክብር በነፃነት
የእግዚአብሄር ምርጫ የሆነች - የዓለም ገነት
አሁንም ቀርባለች ለምሳሌ - በርሃብና ሞት
የአገር ፍቅሯን አደፍርሳ - በ'ርስ በ'ርስ ግጭት
አደራው ተረስቶን ሃላፊነት - ከጀግኖች አባት
የተሰጠንን ጥለን በጥላቻ - አስፈለገን ምግዚት

ግርማና ሞገሷን እንዲያስነሳ - ወኔአችን ይላወስ
ጥንታዊ ታሪክ፣ አንድነት፣ ቅርሷ - በክብር እንዲታደስ
የጀግኖቹ ደምና ታሪክ - ይመለስ በደማችን
የወደፊቱ አዲሲቱን ኢትዮጵያችን - አድርገን ዓላማችን
ለአንድነት፣ ነፃነት፣ ሥልጣኔ - ይሁነው ትግላችን
ሃይማኖት፣ እኩልነት፣ መብት ሆኖ - የኢትዮጵያ ግባችን

## ወዮ!!

ከአምሀ አስፋው

ላባቶቻችን፣
ርህራሄ ነበር፣ የጀግንነት ምልክቱ፣
ድል ለሆነው ሰራዊት፣
የልባቸውን ሰፊነት ማሳየቱ።
የዘመኑ አድራጊዎች፣ ድል፣
እንኳዋንስ ኖሮ የተፈፀመ በደል፣
ያልነበረም ቢሆን እየፈጠሩ፣
ያሳዝናል ማየቱ፣ ሲገሉ፣ ሲበቀሉ።

ድል ይሆናል፣ ድል አድራጊ፣
ያሸንፋል መልሶ፣ ተሸናፊ።

የሚያሳዝነኝ መጥፋቱ፣
የሚያስፈራኝ ሳስበው መቅረቱ፣
ከድል በሁዋላ በቀል፣ የፈሪ ጠባይ መሆኑ፣
ያባቶቻችን ደግነት ነው፣
ላሸነፉት ህዝብ መራራቱ፣
ይሄ ነው 'ሚያሳዝነኝ፣ መጥፋቱ መረሳቱ።

ትውልድ፣ ከቀደመው ነውና የሚማር፣
መሀሪነት ከሆን ነውር፣
በቀል ከሆን የድል መከር፣
ወዮላቸው ለባንዶች አገራቸውን ለሸጡ፣
ወዮላቸው ለነዚያ ከእንግዴህ ድል ለሚሆኑ።
ወዮላቸው!!

---

## "ኅብረ-ቀለም ፈጥራ"

በሰይፉ ኣዳነች ብሻው

ለውባየሁ ወርወር

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፹፱ ዓመት
Saefu © Copyright 1997

በብርሃን ተጥለቅልቃ፣
ከጨለማው ውስጥ አሾልቀን አየናት
በአንድነት ሕብረት፣
በኢትዮጵያዊነት ስሜት
አስጓዘችን በሃሳብ ትዝታ፣
ከኅጣችን ከመንደራችን
ያወቅነውን የረሳነውን ሁሉ፣
እንድንጎበኝ ባህላችን
ከራር አክረው አጀቧት፣
ሌላው ማሲንቆውን ቃኘላት
ሆ! ብለው እሸኼ፣
በየባህሉ ጥረዛውን ገጠሟት።
* * *
እንገቷን ብትሰብቀው፣
ትከሻዋን ብታወልቀው
ደረቷን ብታስፈንጥረው፣
ዳሌዋን ብታራግበው
እየኀላች እየፈነጠቀች፣
እያበበች እየተወደደች
በኅብረ-ትርኢት በአጀብ ታጅባ፣
በስብስብ ትንግርት ፈጠረች።
* * *
አካሏ እንደ ማዕበል ተናውጦ፣
ተመልካች ትንግርት ሆነችው
ዘር ሳትለይ ኀላዎችን በውስጧ አሰባስባ፣
ኢትዮጵያን ደምራ አሳየችው
አንድነቷን በውስጧ ፈጥራ፣
የአንድ አገር ፍቅርን ፈነጠቀችው
በብርሃን ተጥለቅልቃ፣
በሎጋ አካሏ ውበቷን ገለፀችው
ኅብረ-ቀለም ፈጥራ፣
ቀሰተ ደመናውን አበራችው
አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀዩን፣
ኢትዮጵያዊነትን ገለፀችው።

# ያንድነት ሸማ

ከልሣኑ ስምረት

እንደዚህ ነበር አባቴ ... ማወታውን ሲለግሱኝ
«ቁስልም ሊድን ሲል ለራሱ» ... ብለው ያኔ ያወጉኝ
<u>በወዳጄ ልቤ</u> ያለውን ... በትምሳሌ የገለጡልኝ።

የተሐድሶ ነገር ምስጢር ... ጭቅቅቱ ሲገፈፍ
የአሙካው መርዝ ነገር ... የቁስሉ መርዝ ሲቀረፍ
ዕገፉ ሲያመረቅዝ ... መዳን መዳን ብሎት ሲጠፍ፤
እንደገናም ይቆጠቁጣል ... የውነት ግኝት
ሲንጠባጠብ
ስንኮፉ ሊነቀል ሲል ... ሕዋስ ሲድን ሲጠረብ።

አፍረን እንኳ ባንመልሰው ... ተለያይተን
ስንተራመስ
ባደረብን የዘር ሥራይ ... ተፈንግለን ስንተራረስ
ባይገባንም ቁምነገሩ ... በኛ ብሂል ማይታመስ
ባልተረዳው ታሪካችን ... ለ«ጣራችን» የማይመልስ
የባዕድ ፃፊ የለም ... ድራችንን የማይከልስ።

አውቀን ብንከላልሰው ... ድርማጋችን ቢዘረዘር
ፈረንጆች «ጂን» የሚሉት ... ጣራ ሐረጉ ቢጣመር
ዮሐንስን አከበርን እንጂ ...የምንሊክንም
ስነምግባር
የዘራይደረስን ቁጭት ... የባልቻ እባነፍሶን ምክር
የነፃነትን ቀናዒነት ... የኢትዮጵያዊነትን
ሥንክሣር።

የፍኩይ አበባ ዕድገት ... በፀሐይ እንደሚበራ
አንድነትም እንዲያው ነው ... የድል ዋስትናን
የሚጠራ።
የትብብር ጥርጊያ መንገድ ... ካወቅንበት
ሊፈጠር ነው
ለሥልጣን ያሉት ማራራቅ ... ከንግዲህ ደረሰ
ማብቂያው።

ያደዋ ግርማ ያለበት ... የድል ድል አጋራችን
የቆምስና የባህታዊ ... የደናግላን ዕፁብ ብርሃን
እንደተቀሰቀሰ ንብ ... የአትንኩኝ ባይ ጩኸታችን!!
ባገር ፍቅር ተቃጥለው ... ትቢያ ሆነው ለረገፉት
በኦሮሞነታቸው ሳይሆን ... በአንድነት ለተሰዉት
በትግሬነታቸው ሳይሆን ... በኢትዮጵያዊነት
ለታገሉት
ባማርነታቸውም ብቻ ሳይሆን ... አጥንትን
ለከሰከሱት

በደማቸው የድል ምግብ ... ነፃነትን ባለሙት
በነርሱ ይሁንባችሁ ... እባካችሁ መርዙን አጥፉት፤
በስማቸው የድል ቤዛ ... ትናንት እንደሆነው ደግሞ
ለወዲሁም ዘመነኛ ... ለዛሬው ይሁን ለከርሞ
ኢትዮጵያዊነት አይሞትም...ይተምማል እንጂ ቆሞ።

ላንድነት ቀን ተሃድሶ ... ለተስፋ ቀን ለድል በዐል
ያለፈው ተረት ሆኖን ... የእኛ ታሪክ እንዲቀጥል
ዳቦና ዴሞክራሲ ... እገበታችን እንዲሞሉ
ረሃብና ድህነት ... ከስር እንዲመነገሉ
ዘረኝነትን ማጥፋት ነው ...የእኛ ልፋት የእኛ
ትግሉ።

ለጥላቻ ተዳርጎ ... ዚቅ ለወረደ ወገን
ዘር ይጠግብ ይመስል ... የሚበላ ጎጠኝነትን
መውደቂያው ሩቅ አይደለም ... መሞቻው
የጥፋቱ ቀን።

ግናስ የኛ መሰላል ... የስልጣኔያችን ማማ
የክብር ልብሳችን ኩታ ... የኢትዮጵያዊነት ሸማ
በቸነፈር የማይገታ ... በደለል ውሃ የማይሟሟ
በባህር ማዶ ሸቀጥ ... በግለኝነት ማይግማማ
ኢትዮጵያዊነታችን ነው ... ያንድነታችን ሁሉ
ካስማ።
ተሰብቆ ሳይነቀንቅ ... የጦር ቀስትም ያዳክማል።
በወል ካልተበራታ ... ዒላማውንም ይስታል።

የሕልም ቅዠት የሌለበት ... ኢትዮጵያዊነት ነው
ስሙር
«የተጋሩ የአማሃራይ» ... የኦሮሞውና የአፋር
የሌላውም የሌላውም ... ቢሆን እንኳ ንዑስ ብሄር
በትንኮል መሰሪነት ... በመለየት ያልተሰራ
በጥላቻ ያልተፋቀ ... ታሪኩ ሁሉ የጠራ
ለልዩነታችን ልዩነት ... ለስቃያችን ስቅላት
ለጥላቻ መፍትሔ ... ለብቸኝነት ሥቅዛት
ለሉጥ መሰል የእምባ ልቅሶ ... «አባሽ» ነው የእኛ
አንድነት

እንደነብር ዥጉርጉርነት ... የመልካችን ከተማ
ልዩም ሆነን «ሌላም» ሆነን ... ለሁላችን የሚስማማ
የክብር ልብሳችን ኩታ ... የኢትዮጵያዊነት ሸማ
በቸነፈር የማይገታ ... በደለል ውሃ የማይሟሟ
በባህር ማዶ ሸቀጥ ... በግለኝነት የማይግማማ
ኢትዮጵያዊነታችን ነው ... ያንድነታችን ካስማ
ከዘፍጥረት ጀምሮ ... የተላበስነው አርማ።

# ጥንቅር ከዚህም ከዚያም

## (በሀገር ውስጥ ከሚታተሙ የግል ጋዜጦች የተጠናቀረ)

• አሜሪካ ሁለቱም አገሮች የአየር ውጊያ እንዲያቆሙ ትዕዛዝ ማስተላለፏ እውነተኛ ሰላም ሊያሰፍን ይችላል የሚል እምነት ኖሯት ነው ወይስ?
☺ የአየር ውጊያ የማስቆሙ ፊሽካ በእርሷ እጅ ከሆነ የምድሩም በርሷው የማይሆንበት ምንም ምክንያት አለው?

***

• በሻዕቢያና በወያኔ መካከል ያለው ጋብቻ ፈረሰ ማለት ነው?
☺ ዘረኝነትን የመሰለ ልጅ በመሃል እያላቸው ይለያያሉ ብለህ አትጠብቅ።

***

• ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ በቴሌቪዥን አይቻቸው ቁርጥ ሣዳም ሁሴንን መሰሉኝ።
☺ የትግል አበቃቀል ዝርያቸው ከወደዚያው ስለሆነ በመልክ ብቻ ሳይሆን በድርጊትም ወደዚያው ወሰድ እንደሚያደርጋቸው ለማረጋገጥ ለርሳቸው ሽራሮንና ባድማን ለሳዳም ኩዌትን መጥቀሱ ብቻ በቂ ማረጋገጫ ይመስለኛል።

***

• ይህን ሰሞን ደግሞ ወትሮ የሌለባቸውን «የእናት ሀገር ፍቅር» የሚል አባዜ ይዟቸዋል።
☺ «ኢምዬ ኢትዮጵያ...» የምትለው ዘፈንና ሬዲዮ ጣውላና ሚስማር የሆኑትም በዚችው ምክንያት ነው በለኛ!

***

• ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ «ካሁን በኋላ የመጨረሻው ትዕግስታችን ስለተሟጠጠ ኃይላችንን አሰባስበን የኤርትራን መንግስት ይቅር በጦርነት ሊደፍረን የኢትዮጵያን ስም እንዳያነሳ እናደርገዋለን ማለታቸውን ሰምተሃል?
☺ ያየሁት ወይም የሰማሁት ድርጊት የለም እንጂ ከሰማሁስ በጣም ሰንበትኩ። ተወው አባክህ ነገሩ «ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ» ነው።

***

• ደህን ሰሞን የሚሸጥ የቤት እቃና መኪና በሽ የሆነው ለምንድነው?
☺ የ7 ዓመታት ቅምጥሎቻችን ግሪን ካርድ (የመኖሪያ ፈቃድ) ኤክስፓየር ስላደረገ ነው የሚል ሹክሹክታ አለ።

***

• ከጠቅላይ ሚኒስትርና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን ማንኛቸው ለኢትዮጵያ የሚያስቡ ይመስልሃል?
☺ ሁለቱም ቢሆኑ እናት ሀገር የሚለው ቋንቋ ትዝ ያላቸው ከሰሞኑ ወረራ ማግስት ስለሆነ እገሌ ማለቱ ይከብደኛል።

***

• የኢህአዴግ መንግስት ይህን ሁሉ መደበኛና ሚሊሽያ ሰራዊት በገፍ እያዘመተ ከመከላከል ደረጃ ከፍ የማይለው ለምንድነው?
☺ የትግራይና የኢትዮጵያ ህዝብ ግምባር ፈጥሮ ያምፅብኛል ከሚል ፍርሃቻ እንጂ እንደ አብርሃም ያየህ «ታላቁ ሴራ» መጽሃፍ ከሆነ ገና ግራር ስር ሳሉ ነው አሁን የተወረሩትን ወረዳዎች በፊርማቸው ያስረከቡት።

***

• ይህ የሻዕቢያ መንግስት ከአማራው ብሔር ጋር ፍቅር የያዘው ምክንያቱ ምን እንደሆነ ገብቶሃል?
☺ የሆድ! የጉሮሮ! ነገር ሆኖበት ነው ወንድሜ።

***

• ሻዕቢያና ድልድይ አይዋደዱም ስለሚባል ነው ፖሊሶቻችን ሰሞኑን የድልድይ ጥበቃውን በስፋት የተያያዙት?
☺ አዎ ለበሬም ዊዱን ለድመትም አይጥ መከልከል እንደማለት ነው።

***

• ታምራት ላይኔ ለመለስ ዜናዊ በቅርቡ ደብዳቤ ላኩላቸው የተባለው ለመሆኑ ምን የሚል ነው?
☺ «ምነው ዘገየህ?» ይሆን?

***

• የኢህአዴግ መንግስት ቀደም ሲል በደህናው ጊዜ ከሠራዊቱ ያሰናበታቸውን ታጋዮች በዚህ ባሁኑ ቀውጢ ሰዓት ያቀረበላቸውን ጥሪ አሜን ብለው ሊቀበሉት የሚችሉ ይመስልሃል?
☺ አሁን ከሀገር በላይ ምንም ስለሌለ የሆደን በሆደ ብለው ሊቀበሉት ይችሉ ይሆናል። ከድል በኋላ ግን የሚጠያይቃቸው ጉዳይ ሊኖር ይችላል ባይ ነኝ።

***

• ጦርነቱ ከመቼውም ጊዜ እየተፋፋመ በመጣበት ወቅት የመከላከያ ሚኒስትሩ የአቶ ተፈራ ዋልዋ ድምፅ መጥፋት ሁኔታ በጤና ነው ወይስ ሌላ ምክንያት ይኖረዋል ብለህ ትገምታለህ?
☺ ለቀይ ካርድ ያሰቡትን ባለስልጣን በቅድሚያ

ከሬዲዮና ጋዜጣ ያርቁታል ሲባል ሰምቻለሁ።

***

• የአፈ ጉባዔ ዳዊት ዮሐንስ የድንፋታ አነጋገር ቀዝ ቀዝ እያለ የመጣ አይመስልህም?
☺ ስልጣናቸው ፊት ቀይ መብራት እየበራባቸው ይሆናላ!

***

• «ኢትዮጵያ» የሚለው የጥላሁን ገሠሠ ዘፈን ዛሬ ወያኔ ሳይቀር ይዘምረው ጀመር?
☺ ኢትዮጵያን የፈጠረ አምላክ የት ሄዶ!

***

• ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሊኮበልሉ ሲሉ ተያዙ የሚል ወሬ አልሰማችሁም?
☺ ለመሆኑ በዚህ በከፋ ሰዓት የሚኮበልሉት ወደ ኤርትራ ነው ወይስ አሜሪካ!! ይሄ የጠላት ወሬ ነው።

***

• የኤርትራው ናቅፋ አሁን ባለበት የግሽበት ጉዳና ከቀጠለ የወደፊት እጣ ፈንታው ምን ሊሆን ይቻላል ብለህ ትገምታለህ?
☺ በሺህ ናቅፋ አንድ ዶሮ ወደ መግዛቱ ያዘነብላል እላለሁ።

***

• እፎይታ ጋዜጣ ባለ 40 ገፅ ሲያሳትም እናንተ ከ8 ገፅ የማታልፉት ለምንድነው?
☺ ሠርቶ አደር ጋዜጣም በዘመኑ ልክ እንደርሱ ነበር።

***

• ሰሞኑን አቶ መለስ ቃለ ምልልስ ሲደረግላቸው ከበረሃ መጣች የተባለችው ጋዜጠኛ ትኩር ብላ ስታያቸው አልገረመህም?
☺ ከተማ ሲገቡ ጠፍተውባት «እሳቸው ናቸው አይደሉም?» ብላ እየተጠራጠረች ይሆናላ!

***

• ኤርትራ ውስጥ «ጤፍ የአሀያ ቀለብ ነው» እየተባለ እንደሚወራ ሰምተሃል?
☺ ያጣ ወሬ ነው ባክህ።

***

• በግንቦት 20 ዋዜማ ዕለት የዘመነ ደርግን ቀረርቶና ሽለላ ማስደመጣቸው ዳር ዳሩ ምን ይመስልሃል?
☺ የሬሳ ሳጥን ሻጮችን ሆድ ማስሞሀ ካማረህ አንተው ጨርሰው።

***

• ባለፈው ሰሞን የሌላው ክልል ገበሬ ዱላ ይዞ ለሰልፍ ሲወጣ የትግራይ ገበሬ ጠመንጃ ይዞ የወጣው ለምንድነው?
☺ ጠመንጃ ስላለው።

***

• ይኼን ደም መጠጣት የለመደውን የሰሜን ኢትዮጵያ አጋንንት ለምን አንዘምትበትም?
☺ መጀመሪያ ደቀመዝሙሮቹን ብናስቀድም አይሻልም?

***

• አፈ ጉባኤ ዳዊት ዮሐንስ ለስልጣናው የምንቀበለው የፍርድ ቤት ዝባዝንኬ ክስ የሌለባቸውን ጋዜጠኞች ብቻ ነው ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው?
☺ የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ እንዲሉ ሆኖ እንጂ በግልፅ የምንፈልገው የእፎይታን፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ የፋና ... ጋዜጠኞችን ነው ቢሉ ማን ይጠይቃቸዋል!

***

• ከዘጋችን ስንት ዓመት የሆናት ጉረቤታችን ሰሞኑን ምን አግኝታ ነው በግድ እየጠራች ሠላም የምትለኝ?
☺ ኤርትራዊት ነኝ?

***

• ወያኔ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታጥቆ እንዲነሳ እየጠየቀ ነው። ይኼ ሁሉ ሕዝብ ታጥቆ ተነስቶ በማን ሊዘምት ነው?
☺ መታጠቁ ይኑር እንጂ የሚዘመትበት መች ይጠፋል?

***

• የእኛ ሠፈር ልጆች «አይባባ አይባባ ሆዴ፣ ሸራሮን ማን ባሻገረኝ አሥመራ ጉዳይ ነበረኝ» ይላሉ አሥመራ ምን አለ?
☺ ቢጫ ወባና፣ ችግር።

***

• ቴሌኮሙኒኬሽን ለውጭ ሀገር ቱጃር ሊሸጥ ነው መባሉን ሰምተሃል?
☺ ስምንት ዓመት ተራ ከመጠበቅ ተገላገልን በለኛ!

***

• ይሄ ልጅ አዋቂ ሳይል በሀገሩ የተለቀቀው ጉንፋን ከየት የመጣ ይመስልሃል?
☺ ኢሳይያስ አፈወርቂን ጠርጥር።

***

# ከአበው

## ትምህርት በምሳሌ

### በተከፈተ አፍ ባዶ ራስ ሲታይ

ከመጋቤ አዕላፍ መኩብብ አጥናው

በዚህ ርእስ ለመጻፍ የፈለግሁት አጭር መዘክር የቀድሞ ኢትዮጵያውያን አበው ከትውልድ ትውልድ ያስተላለፉትና ጠብቀው በማቆየት ያስረከቡን ታላቅ የጨዋነትና ትሕትና የተሞላበት የንግግር ጥበብ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ታላቅ ቅርስ መሆኑን ለማመልከት ነው።

በጥሩ ቤተሰብ መሐል ያደጉ ኢትዮጵያውያን የንግግር ጥበብ ትሕትናቸውንና ለሰው ሁሉ ያላቸው አክብሮት በዋጋ ሊተመን የማይችል ትምህርታዊ መልካም ሥነ ምግባር ተደግፎበት የሚኖር ዓምደ ወርቅ ነው ማለት ይቻላል።

ዕውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ለንግግር አይቸኩሉም፤ መናገር በሚፈልጉበትም ጊዜ ሰውን የሚያሳዝን (ቅር የሚያሰኝ) አስጸያፊ ቃል ከአንደበታቸው እንዳይወጣ ብርቱ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ለንግግራቸው ማጣፈጫ የሚሆኑ ታሪክና ምሳሌዎችን እንደ ቅኔ ቆጥረው፤ ቃላትን መርጠው በሚናገሩበት ጊዜ የሚያመነጩት አሳብ ይበል የሚያሰኝና ፍጹም ተደማጭነትና ተቀባይነትም ያለው ይሆናል። የንግግር ለዛ ነበራቸው ማለት ነው። በተለይ የአገር ቤት ነዋሪው ሕዝብ ያለው የንግግር ለዛ፤ ጨዋነትና ትሕትናው አክብሮቱም እንደተጠበቀ ሆኖ ሳለ በአንዳንድ ታላላቅ ከተሞች የሚገኘው ግን የአባቶቹን የንግግር ጥበብ ቸል በማለት ከምዕራቡም ሆነ ከምሥራቁ ዓለም የተዘራውን ባዕድ ልማድና ባህል በማዳበር የንግግር ፈሊጡ (ስልቱ) የተለየ መልክ መያዝ ከጀመረ ውሎ አድሯል። ከዚህም የተነሳ ያ ሁሉ ጨዋነት ጭምትነትና ትህትና እየተረሳ ችኩልነት፣ ጀብደኛነትና ድፍረት፣ አውቃለሁ ባይነት፣ የማን አለብኝነት መንፈስ፣ ዓይን አውጣነት፣ ግብዝነትና ሌሎችም ከዚህ በፊት በሀገራችን ያልተለመዱ ባሕርያት በመስፋፋትና በመንሰራፋት ላይ ይገኛሉ።

ከዚህም የተነሳ ከአንዳንድ ልጆች አንደበት የሚፈልቁ አስጸያፊ ቃላት የስድቡ ጋጋታ፣ የትችቱ ቱማታ ገደብ የለሽ ሆኖ በተከፈተ አፍ ባዶ ራስ እየታየ ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን «የሰነፍ ሰው መታወቂያ ምልክቱ ያልታወቀ ንግግር ማብዛት ነው» ይላል። ሌላውም ባለ ቅኔ «ቢቆስልም ይድናል የተደበደበ ምላስ ግን ይናራል እንዳንገበገበ» ይለናል።

የተምሳሌቱም ንግግር «በአፍ ይጠፋ በለፈለፉ» የሚል ሲሆን ጠቢቡ ሰሎሞን ሕ□ይወትም ሞትም በአንደበት እጅ ናቸው» ሲል ከተናገረው ቃል ጋር ፍጹም ተመሳሳይነት አለው።

በአንድ ወቅት ሁለት ሴቶች ጥሩ ጎብረት መስርተው በእህትማማችነት መንፈስ ተሳስረው በአንድ ቤት ይኖሩ ነበር። ከረጅም ጊዜ በኋላ አምባጓሮ ፈጥረው ሁለቱም ይለዋወጡት የነበረውን ፍጹም አስጸያፊ የሆነ ቃል በጽሑፍ ለመግለጥ ያስቅቃል። የሁለቱም ወናፍ ተከፈተ፣ ጉረቤቶች ተሸበሩ፤ በስድብ ሲጓጓኑ ከቆዩ በኋላ ትግል ገጥመው በንክሻና በሾለ ጥፍራቸው ተዘላዘሉ። አንደኛዋ ስትጥል ሌላዋ ስትገለብጥ ለገላጋይ አስቸገሩ። መቸም ድል ለሁለት አይሆንምና አንደኛዋ አሸንፋ በሌላይቱ ላይ ተከመረችባት፤ በቦክስ እንደ እርጥብ ስልቻ ስታለፋት ቆይታ እንደ አጋጣሚ አንድ የሸንኩርት መክተፊያ ቢላዋ እጁዋ ስለገባ «አንቺ አስኮናኝ» ሕግን በመፍራት ነው እንጂ ላርድሽ እችል ነበር ካለች በኋላ በስለቱ ሳይሆን በቢላዋው ደንደስ አንገትዋንና ያንን መርዘኛ ምላስዋን ገዝግዛ ተወቻት።

በመጨረሻም ሰዎች ገላግለዋቸው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዱ፤ በቢላዋ ደንደስ የተገዘገዘችው ቀባጣሪ (ለፍላፊ) የመሰረተችው ክስ «በቢላዋ ገዝግዛ የተወችኝ ልትገድለኝ አስባ ስለነበር በሞት ትቀጣልኝ» የሚል ነበር። ዳኞች ግን የመግደል ሙከራን የሚያመለክት የሕግ አንቀጽ ጠቅሰው የገንዘብና የእስራት ቅጣት በተከሳሽ ላይ ወሰኑ። በዚህም ጊዜ ከሳሽ በተለመደው የድፍረት ንግግሯ ዳኞችንም ጭምር ፍርድ አዳልታችኋል፤ በሞት እንድትቀጣ ካልፈረዳችሁ አልቀበለውም በማለት አደባባዩን በጩኸት ሞላችው።

በዚህም ጊዜ ከዳኞቹ አንዱ ረጋ ባለ መንፈስ ያቀረበላት ምርጫ እንዲህ የሚል ነበር፦

«ስሚ እንግዲህ ከሣሽ
ተከሳሽ ተሰቅላ በሞት ትቀጣ ካልሽ
እንደገና ይምጣ የሽንኩርት መክተፊያሽ
የሰላ ቢላዋው ይሰጥ ለተከሳሽ
ታዲያ እንደገመትነው ከመሰረትሽው ክስ
ሙያ አልሰራምና የቢላዋው ደንደስ
ስለቱን አዙራ አንገት በመቀንጠስ
ተከሳሽ በቅድሚያ ጅምርዋን ትጨርስ
ከዚያ በኋላ ነው የምንፈርደው በነፍስ
ብለው ሲጠይቋት ከሣሽ ይኸን ጊዜ
መገላገል ቻለች ከያዛት አባዜ"

እንግዲህ ይህ የጥንት አበው ታሪክና ምሳሌ ለዚህ ጽሑፍ መደምደሚይ ሆኖ ሲቀርብ አንደበታችን መልካም የንግግር ጥበብ የሚፈልቅበት እንጂ የክፉ ቃላትና የከንቱ ስድብ የአሉባልታም መውረጃ ቦይ ሆኖ እንዳይቀር የሚመክረን ይመስላል።

ስለዚህ ከሳሽ ነገርን ሁሉ ለመለፍለፍ የሚከፍትና ስድ የሚለቀቅ አንደበት ሁሉ መጨረሻው ራስን አለማወቅና የመንፈስን ድህነት አጉልቶ የሚያሳይ መሆኑን ተገንዝበን ለሰው ዘር ሁሉ አክብሮትና ትህትና የሞላበትን የጥንት አባቶቻችንን የንግግር ጥበብ ከታሪክና ምሳሌያቸው ጋር እያገናዘቡ በፍጹም ጨዋነትና በጭምትነት ረጋ ብሎ እያሰቡ፤ ቃላትን እንደ እሸት በመምረጥ መናገር ታላቅ የባህል ቅርሳችን መሆኑን እንርሳ።

የጥንት አባቶች ሲናገሩም ሆነ ሲዘምሩ አፍን ሰፋ አድርጎ መክፈት ምን ያህል ጸያፍ እንደሆነ ያስተምሩ ነበርና ዛሬም ያ ሥርዓተ አበው ጸንቶ እንዲኖርና በተከፈተ አፍ ባዶ ራስ እንዳይታይ ማድረጉ ታላቅ ጥበብ መሆኑን ብናስተውል መልካም ነው።

—— // ——

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

**የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።**

| | 12 ISSUES | | 6 ISSUES | |
|---|---|---|---|---|
| U.S | $30.00 | ☐ | $16.00 | ☐ |
| Canada | $40.00 | ☐ | $22.00 | ☐ |
| Europe | $56.00 | ☐ | $30.00 | ☐ |
| Asia | $70.00 | ☐ | $38.00 | ☐ |
| Institutions | $80.00 | ☐ | $40.00 | ☐ |

*Please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ____________________

*Address:* ____________________

*City:* ____________________

*St.* ________ *Zip* ________ *Phone: (     )* ____________________

==========================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ____________________

*Address:* ____________________

*City:* ____________________

*St.* ________ *Zip* ________ *Phone: (     )* ____________________

==========================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED: $* ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*

# አበባ ግሮሰሪ

## ABEBA GROCERY
## ENJERA & SPICES

10230 E. Northwest Hwy.
Dallas, Texas 75238
(214)340-6100
(214)503-0613

Old Town
Fast Stop Food Store
6119 Greenville Avenue
To Pick Up Enjera

መላ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን
እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን በሰላምና በጤና አሸጋገራችሁ!!
መጪው ዘመን የሰላም፤ የጤናና የብልፅግና እንዲሆንላችሁ
መልካም ምኞታችንን እንልፃለን።

ዝነኛ እንጀራችንን
ዳቦአችንን፤ቅመማ ቅመም
ሽሮና በርበሬ
ከአገር ቤት የመጡ ጌጣጌጦችና የባህል ልብሶችን አዳዲስ ካሴት፤ ሲዲና
ቪድዮ እንዲሁም መጽሐፍቶችና መጽሔቶችን
ከመልካም መስተንግዶ ጋር ያገኛሉ።



# ሀናና ብንያም ሱቅ

*H & B Shop*
*431 N. Indian Creek, Suite E*
*(404)296-2766*

ከአገር ቤት የመጡ
ጌጣጌጦችና የባህል
ልብሶች፤ አዳዲስ ካሴቶችና
ሲዲዎች፤ ቪድዮ
እንዲሁም መጽሐፍቶችና
መጽሔቶችን
ከመልካም መስተንግዶ ጋር
ያገኛሉ።



ብንያምና ሀና ነን

መላ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን
እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን በሰላምና በጤና
አሸጋገራችሁ እንላለን!!
መጪው ዘመን የሰላም፤ የጤናና የብልፅግና
እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞታችንን
እንልፃለን!!

ለኢትዮጵያውያን አስፈላጊ የሆኑ
ዕቃዎችን በሙሉ እናቀርባለን።

# MRA'G TRAVEL, Inc.

## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*

92 Piedmont Ave. NE - Atlanta, GA 30303



ለዓለም አቀፍና
ለአገር ውስጥ ጉዞዎ አለንልዎ!!

EXCELLENT SERVICE - SPECIAL FARE - GROUP FARE

ገነት ፈቀደ – ፕሬዚዳንት
GENET FEKEDE
PRESIDENT

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቀጥታ በረራ**
**ከአዲስ አበባ — ዋሽንግተን ዲ.ሲ.**
**ከJune 4, 1998 ቀን ጀምሮ**
**ዘወትር ሐሙስና ቅዳሜ**
**በረራውን ለማስተዋወቅ**
**ልዩ ታላቅ ቅናሽ**

SPECIAL INTRODUCTORY FARE

**Please, call** (404) 577-4404
(404) 577-4682
(404) 577-4889
**Fax:** (404) 222-9305

Cerified Agent for:
ARC - IATA - CLIA

**Also Call:**
**San Fransisco Area**
**Aderaw Yeshiwas**
**Selam Fekede**
**Phone: (510)829-0529**
**Fax: (510)829-0529**

የኢትዮጵያ አየር መንገድ
***ETHIOPIAN AIRLINES***

*Fly ETHIOPIAN*

የኢትዮጵያ አየር መንገድ
ልዩ ወኪል
CONSOLIDATOR FOR
*ETHIOPIAN AIRLINES*

# Allstate®

**You are in good hands.**

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)508-8978 - Fax: (404)299-6266



Theodros Hailegiorgis
*Exclusive Agent*

- ⇨ **AUTO**
- ⇨ **HOME OWNER'S**
- ⇨ **RENTERS**
- ⇨ **LIFE**
- ⇨ **BUSINESS**
- ⇨ **COMMERCIAL AUTO**

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indemnity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

**You're in good hands.**